# መሠረተ ሕይወት

## በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የልጆች መማሪያ መጽሐፍ

## አምስተኛ ክፍል

www.zeorthodox.org

አዘጋጅ - ቀሲስ ሰሎሞን መሉጌታ

ነሐሴ ፳፻፮ ዓ.ም

© ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ ዘውዴ ፳፻፮ ዓ.ም

መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው
ALL RIGHTS RESERVED

**የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን እምነት ሥርዓት እና ትውፊት መሠረት በማድረግ የተዘጋጀ ሥርዓተ ትምህርት**

አድራሻ፦
**ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ ዘውዴ**

ፖ.ሳ.ቁ 43200
**አዲስ አበባ**
**ኢትዮጵያ**

**Email:- kesisolomon@gmail.com**
**Website;-www.zeorthodox.org**

www.zeorthodox.org

**የኮምፒውተር ሌይ አውት ዲዛይን**
**ልደት አስፋው**

## ማሳሰቢያ

ይህ መጽሐፍ ተሰራጭቶ የሚገኘው ገቢ በቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም፣ በቦሌ ደብረ ምሕረት ቅዱስ ሚካኤል፣ በቦሌ ሰሚት መካነ ሰላም መድኃኔዓለም እና ወደ ፊትም በተለያዩ አጥቢያዎች ለሚከናወኑ የሕፃናት፣ አዳጊዎች፣ ወጣቶችና ወላጆች ኦርቶዶክሳዊ ትምህርትና ተመሳሳይ አገልግሎቶች የሚውል ይሆናል፡፡

## መታሰቢያነቱ

ላለፉት ስድሳና ሰባ ዓመታት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሰንበት ት/ቤቶች በእውነትና በቅንነት አብዝተው በማገልገል ለደከሙ ሁሉ ይሁንልኝ።

## ምስጋና

ይህ የመማሪያ መጽሐፍ ሲዘጋጅ በቀጥተኛ ተሳታፊነት የተሰለፉትን ዲ. ዘላለም ረድኤትና ዲ. ዮናታን ኢያሱን፣ መጽሐፉን በማረም የተባበሩትን መጋቤ ብሉይ አእመረ አሸብርን፣ መምህር ካሕሳይ ገብረ እግዚአብሔርን፣ ዲያቆን ዳንኤል ክብረትን፣ እና አቶ አስራት ከበደን እንዲሁም በኮምፒዩተር የለቀማ ሥራ ያገለገሉትን ልደት አስፋውን፤ መጻሕፍቱን ለማጠናቀቅ ሳደርግ በነበረው ጥረት ውድ ባለቤቴና ልጆቼ የእንቅልፍና የእረፍት ሰዓታቸውን ሳይቀር መሥዋዕት በማድረግ ስላሳለፉ ስለ ከፈሉት መሥዋዕትነት እግዚአብሔር ዋጋ ከፋይ ነውና ዋጋቸውን ይክፈላቸው እላለሁ። በመጨረሻም የሚያስፈልገውን ሁሉ የሚያከናውኑ የመርሐ ግብራችን አስተባባሪ የጻድቁ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ሰንበቴ የሥራ አስፈጻሚ አባላትን እግዚአብሔር በቸርነቱ ይጠብቅልኝ ሳልል አላልፍም።

www.zeorthodox.org

# ማውጫ


| ተ. ቁ. | አርእስት | ገጽ | ወር | ሳምንት | ልዩ በዓል |
|---|---|---|---|---|---|
| | መቅድም | I | | | |
| | መግቢያ | III | | | |
| 1. | ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ | 1 | | አንደኛ | |
| 2. | አልዓዛር እና ባለጠጋው ሰው | 4 | | ሁለተኛ | |
| 3. | የማታው ተማሪ | 6 | | ሦስተኛ | |
| 4. | ልደታ ለማርያም | 9 | | አራተኛ | |
| 5. | የድንግል ማርያም ክብር | 11 | | አምስተኛ | |
| 6. | ቅዱስ ያሬድ | 14 | | ስድስተኛ | |
| 7. | አክዓብ እና ናቡቴ | 16 | | ሰባተኛ | |
| 8. | ቅዱስ ቂርቆስ እና ቅድስት ኢየሉጣ | 19 | | ስምንተኛ | |
| 9. | ነቢያት እና የተመረዘው ምግብ | 21 | | ዘጠነኛ | |
| 10 | የኤማሁስ መንገደኞች | 23 | | ዐሥረኛ | |
| 11. | ጻድቁ አቡነ ተክለሃይማኖት | 25 | | ዐሥራ አንደኛ | |
| 12. | ነቢዩ ኤልሳዕ መራራውን ውኃ አጣፈጠ | 28 | | ዐሥራ ሁለተኛ | |
| 13. | ታላቋ ሴት | 30 | | ዐሥራ ሦስተኛ | |
| 14. | ጌታ ኢየሱስ እና ዘኬዎስ | 33 | | ዐሥራ አራተኛ | |
| 15. | የነሐሱ እባብ | 35 | | ዐሥራ አምስተኛ | |
| 16. | ዐሥሩ ደናግል | 37 | | ዐሥራ ስድስተኛ | |
| 17. | ጌታ ኢየሱስ የከነናዊቷን ሴት ልጅ ፈወሰ | 39 | | ዐሥራ ሰባተኛ | |
| 18. | ጌታ ኢየሱስ የመበለቲቱን ልጅ አስነሣ | 41 | | ዐሥራ ስምንተኛ | |
| 19. | ባሕራን | 43 | | ዐሥራ ዘጠነኛ | |
| 20. | አስቴር (ክፍል አንድ) | 46 | | ሃያኛ | |
| 21. | አስቴር (ክፍል ሁለት) | 48 | | ሃያ አንደኛ | |
| 22. | ገብር ሔር | 50 | | ሃያ ሁለተኛ | |
| 23. | ኢያሱ | 52 | | ሃያ ሦስተኛ | |
| 24. | ቅዱስ እስጢፋኖስ | 54 | | ሃያ አራተኛ | |
| 25. | ዲቦራ | 56 | | ሃያ አምስተኛ | |
| 26. | ጌታ ኢየሱስ የደቀመዛሙርቱን እግር አጠበ | 58 | | ሃያ ስድስተኛ | |
| 27. | ሳውል በደማስቆ | 60 | | ሃያ ሰባተኛ | |


www.zeorthodox.org

## መሠረተ ሕይወት አምስተኛ ክፍል

| ተ.ቁ. | አርእስት | ገጽ | ወር | ሳምንት | ልዩ በዓል |
| --- | --- | --- | --- | --- | --- |
| 28. | ቅዱስ ጳውሎስ በልስጥራ ተአምር አደረገ | 63 | | ሃያ ስምንተኛ | |
| 29. | ገድለ ሰማዕታት | 65 | | ሃያ ዘጠነኛ | |
| 30. | ቅዱስ ጳውሎስ በድንጋይ ተወገረ | 67 | | ሠላሳኛ | |
| 31. | የነቢዩ ዳንኤል ጾም | 69 | | ሠላሳ አንደኛ | |
| 32. | ጸሎተ ሐና | 71 | | ሠላሳ ሁለተኛ | |
| 33. | የረዓብ እምነት | 74 | | ሠላሳ ሦስተኛ | |
| 34. | የንጉሥ ሕዝቅያስ ጸሎት | 76 | | ሠላሳ አራተኛ | |
| 35. | ካህኑ ዔሊና ልጆቹ | 78 | | ሠላሳ አምስተኛ | |
| 36. | መጥምቁ ዮሐንስ | 80 | | ሠላሳ ስድስተኛ | |
| 37. | እስራኤል ከነዓንን ሰለሉ | 82 | | ሠላሳ ሰባተኛ | |
| 38. | የቴሌቪዥንና የኢንተርኔር(የመረጃ መረብ) ተጽእኖ | 84 | | ሠላሳ ስምንተኛ | |
| 39. | የመጥምቁ ዮሐንስ አገልግሎት | 87 | | ሠላሳ ዘጠነኛ | |
| 40. | ወዳጅነት | 90 | | ዐርባኛ | |
| 41. | አባትህንና እናትህን አክብር | 93 | | ዐርባ አንደኛ | |
| 42. | የጠፋው ልጅ | 96 | | ዐርባ ሁለተኛ | |
| 43. | የፋሲካው በግ | 99 | | ዐርባ ሦስተኛ | |
| 44. | ንዕማን ተፈወሰ | 101 | | ዐርባ አራተኛ | |
| 45. | ቤተ ክርስቲያን | 103 | | ዐርባ አምስተኛ | |
| 46. | የጌታ ቀን | 105 | | ዐርባ ስድስተኛ | |
| 47. | ነቢዩ ሐጌ | 107 | | ዐርባ ሰባተኛ | |
| 48. | ማርያም | 109 | | ዐርባ ስምንተኛ | |

www.zeorthodox.org

# መቅድም

በአሁኑ ወቅት በአገር ውስጥም ሆነ ከአገር ውጪ የሚገኙ ኦርቶዶክሳውያን ሕፃናት፣ አዳጊዎችና ወጣቶች ቤተ ክርስቲያናቸውን እያወቁ በመልካም ሥነ ምግባር ታንጸው እንዲያድጉ የሚያደርግ፣ ጥያቄዎቻቸውን የሚመልስ ብሎም ችግሮቻቸውን የሚፈታ መንፈሳዊ ሥርዓተ ትምህርት የመኖሩ አስፈላጊነት በብዙዎቻችን ዘንድ ይታመንበታል፡፡ ቤተ ክርስቲያናችንም በዚሁ ዙሪያ በርካታ ተግባራትን እንደምታከናውን እምነቴ ነው፡፡

ወላጆች ልጆቻቸውን ወደ ቤተ ክርስቲያን በመላክ ለተስተካከለ ዕድገታቸው አስተዋጽዖ በማድረግ የወላጅነት ሓላፊነታቸውን ለመወጣት ፍላጎቱ አላቸው፡፡ ሆኖም በአንዳንድ ሁኔታዎች አለመመቻቸት የተነሣም ይሁን በሌላ ምክንያት ከሕፃንነታቸው ጀምሮ እንዲማሩላቸው ወደ ቤተ ክርስቲያን የሚያቀርቡ ምእመናን እጅግ ጥቂቶች መሆናቸውን የተለያዩ አጋጣሚዎች ማሳያዎች ሆነውኛል፡፡

ከዛሬ ሰባት ዓመት በፊት በእግዚአብሔር ፈቃድ በምሥራብት መሥሪያ ቤት በኩል ለተዘጋጀ ሙያዊ ሥልጠና ከአገር ውጪ ባደረግሁት ጉዞ ዘወትር አብረውኝ የሚቆሙ ቤተሰቦቼ ምክንያት ሆነው ግብጽንና ገዳማቱን የመጐብኘት ዕድል አገኘሁ፡፡ ይህም የተቀደሰ አጋጣሚ ስለ ልጆች፣ በቅድመ ጋብቻ ስላሉ ወጣቶችና በትዳር ስለሚኖሩ ኦርቶዶክሳዊያን የተናጠል መርሐ ግብር እንዳስብ አደረገኝ፡፡ በእግዚአብሔር ፈቃድም በኅዳር ወር ፲፱፻፺፱ ዓ.ም. በቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም መጥምቀ ዮሐንስና አቡነ አረጋዊ ቤተክርስቲያን የልጆች መርሐ ግብር በሃያ አራት ልጆች ተጀመረ፡፡ አሁን ከሙዓለ ሕፃናት እስከ አሥራ ሁለተኛ ክፍል የሆኑ ከሦስት ሺህ በላይ የሚሆኑ ልጆች፤ በየሳምንቱ ቅዳሜና እሑድ ቀን ከአራት እስከ ስድስት ሰዓት በአማርኛና በእንግሊዝኛ ቋንቋ የሚሰጠውን መንፈሳዊ ትምህርት ይከታተላሉ፡፡ በርካታ ምእመናንም በየሳምንቱ ረቡዕ ከምሽቱ አሥራ ሁለት እስከ ሁለት ሰዓት ለአዋቂዎች በተዘጋጀው የትምህርት መርሐ ግብር ተሳታፊዎች ናቸው፡፡

www.zeorthodox.org

ይሁን እንጂ ሁሉንም ልጆች በየትምህርት ደረጃቸው በመመደብ ማስተማር የሚያስችል መንፈሳዊ ሥርዓተ ትምህርት ማዘጋጀቱ አስፈላጊ ነበር፡፡ በመሆኑም ቀድመው የተዘጋጁትን ትምህርቶች ተካተውበት ለዚሁ ሥራ እገዛ የሚያደርጉ ወንድሞች ጋር በመመካከር ዲያቆን ዮናታን ኢያሱ እና ዲያቆን ዘላለም ረድኤት ተገኝተውበት ለትምህርቱ አጋዥ የሆኑ መጻሕፍትን ለማዘጋጀት ጥረት ተጀመረ፡፡ እግዚአብሔር ፈቃዱ ሆኖ ከአራት ዓመታት ጥረት በኋላ፤ ለሥርዓተ ትምህርቱ አጋዥ የሆኑ ከሙዓለ ሕፃናት እስከ አሥራ በኋላ አጋዥ የሆኑ ከሙዓለ ሕፃናት እስከ አሥራ ሁለተኛ ክፍል ድረስ የሆኑ አሥራ ሦስት ጥራዝ የማስተማርያ መጻሕፍት ዝግጅት ተጠናቅቆ ለኅትመት እንዲበቁ ለማድረግ ወደ ማተሚያ ቤት ገብተዋል፡፡

በማስተማርያ መጻሕፍቱ ዝግጅት፤ ለመረጃ የምንገለገልባቸው ምንጮች፣ የምእመናን የኑሮና የትምህርት ደረጃ፣ የመኖሪያ ሥፍራዎችና የባህል ልዩነቶች፣ እንዲሁም በአገር ውስጥ እና ከሀገር ዉጪ በሚገኙ ኢትዮጵያዊያን መካከል ያሉ የአኗኗርና የሥራ ሁኔታዎችና አካባቢያዊ ልዩነቶችን ታሳቢ በማድረግ ከግንዛቤ ውስጥ እንዲገቡ ተሞክሮአል። በዚህ ሥራ ቀጥተኛ ተሳትፎ ላደረጉት ለዲያቆን ዮናታን ኢያሱ እና ለዲያቆን ዘላለም ረድኤት፤ እግዚአብሔር በቸርነቱ ጠብቆ ረጅም ዕድሜ ይስጥልን እላለሁ።

ይኸው የእግዚአብሔር ፈቃድ ሆኖ ከሙዓለ ሕፃናት እስከ ዐሥራ ሁለተኛ ክፍል ድረስ ላሉ ወጣቶች ለሚሰጠዉ ‹‹መሠረተ ሕይወት›› መንፈሳዊ ሥርዓተ ትምህርት ማስተማሪያ የሚሆኑ መጻሕፍት ለንትመት በቀተዉ ለአገልግሎት የተዘጋጁ መሆናቸውን በታላቅ ደስታ እገልጻለሁ።

***“እስከ አሁን ድረስ እግዚአብሔር ረድቶናል።” ፩ኛ ሳሙኤል ፯ ፥ ፲፪***

www.zeorthodox.org

# መግቢያ

የዚህ መንፈሳዊ ሥርዓተ ትምህርት ምንጭ መጽሐፍ ቅዱስ፣ ሌሎችም የቤተ ክርስቲያን መጻሕፍትና ትውፊተ ቤተክርስቲያን ናቸው። በዚህም መሠረተ ጥርት ያለውን የቅድስት ቤተ ክርስቲንን ትምህርተ ሃይማኖት፣ ሥርዓትና ታሪክ ከመልካም ሥነ ምግባር ጋር፤ በዓለማዊ ትምህርት ቤት ለሚማሩ ሕፃናት፣ አዳጊዎችና ወጣቶች እንዲደርስ ለማድረግ፤ በየትምህርት ደረጃቸው እና ዕድሜአቸው እንዲመጥን ሆኖ የሥርዓተ ትምህርት አዘገጃጀትን ስልት በመከተል ለማዘጋጀት ተሞክሮአል። አንዳንዶቹ ትምህርቶች ልጆች ትምህርቱን በሚገባ ተረድተዉ ማስታወስ እንዲችሉ በየደረጃዉ በሚገኙ የተለያዩ ክፍሎች ሥርዓተ ትምህርት ውስጥ በድጋሚ ተካትተዋል።

ትምህርቶቹ በየወሩ ተከፋፍለው በቤተ ክርስቲያን ከሚከበሩ በዓላትም ጋር እየተቀራረቡ እንዲዘጋጁ ጥረት ተደርጎአል። በየመካከሉ ለሚኖሩ ክፍተቶች በሁሉም አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት በቅደም ተከተል አገልግሎት ላይ እንዲውል ሆኖ የማሟያ ትምህርቶቹ ተወስደው ተካትተዋል። ያም ሆኖ እንደየ ጊዜው ሁኔታ ዘመኑን እንዲዋጅ መሻሻልና መዳበር ያለበት መሆኑ ግን የማይዘነጋ ነው።

በሙዓለ ሕፃናት የሚገኙ ልጆች በጣም አጫጭር ታሪኮችን ብቻ ሰምተው ጥቂቶቹን ብቻ ማስታወስ የሚችሉ ናቸው። ረጅም ጽሑፍና ሐሳብ በትኩረት አንብበዉ በቀላሉ ለመረዳትም ሆነ ለማስታወስ ስለማይችሉ ወይም ስለሚቸገሩ በመምህራን እንዲሁም በወላጆች መታገዝ ያስፈልጋቸዋል። በተረት፣ በታሪክ፣ በሕልምና በእውነታ መካከል ያለውን ልዩነት አገናዝቦ ለመረዳት ይቸገራሉ። በጣም ፈጠራ የታከለባቸው የማስተማሪያ መርጃ መሣሪያዎች የሚያስፈልጓቸው ቢሆኑም መምህራ ኖቻቸው የሚዘምሩላቸዉን መዝሙሮች ማስታወስና በአእምሮአቸው መያዝ፣ በትምህርታዊ ጨዋታዎቻቸውም ሆነ በማንኛውም ሁኔታ መምሰልና ማስመሰል ይችላሉ። በዚህ ደረጃ የሚገኙ ልጆች የሚንቀሳቀሱና የተለያዩ ድምፆች ያሉባቸውን ነገሮች እንዲሁም ከሌሎች ጋር መጫወትንና ያዩትን በተግባር ማሳየትን ይወዳሉ።

www.zeorthodox.org

ልጆች ቤተ ክርስቲያን መምጣታቸው ደስታን እንዲፈጥርላቸውና ፈጽመውም የሚወደዱ መሆናቸውን እንዲሰማቸው ማድረግ እንጂ ቶሎ ሊያስደነግጣቸው ወደ ሚችል አቀራረብና ቅጣት ማዘንበል አይገባም። በየደረጃው የሚገኙ ልጆችን የሚያስተምሩ መምህራን በተፈጥሮ ለልጆች ፍቅር ያላቸውና ፍቅራቸውንም መግለጽ የሚችሉ መሆን ይገባቸዋል። በዚህ ትምህርት የሚጠበቁ መልካም ውጤቶችም በሚቀርቡላቸው መርጃዎችና በመምህራኑ ጥረት ላይ የተመረኮዙ ናቸው። መምህራኑ ልጆችን ለመሳብ ብሩህ ፈገግታና ፍቅር ያለው አቀራረብ እንዲሁም፤ ደመቅ ያሉ ቀለማትን፣

ድምፅና ተንቀሳቃሽ ምስሎችን ቢጠቀሙ መዝሙራትንም ቢያዘምሩላቸው ለትምህርቱ ታላቅ ኃይል ይሆናል፡፡ ከሥርዓተ ትምህርቱ ጋር መምህራን ልጆቹን በየዕለቱ የትምህርት መርሐ ግብሮች መዝሙራትን ሊዘምሩላቸውና ሊያስጠኑአቸው ያስፈልጋል፡፡ አንዳንድ ጊዜም ከትምህርቱ ጋር ተዛማጅ የሆኑ ሥዕላትን ቢያሳዩአቸዉ፣ ቢሰጡአቸው የተማሩትን ትምህርት በቀላሉ ለማስታወስና ለሌሎችም ለማስረዳት የበለጠ ዕድል ይፈጥርላቸዋል፡፡ አንዳንድ ጊዜ ቤተሰቡ ሁሉ ወደ ቤተክርስቲያን እንዲመጣ ልጆች ምክንያት ሊሆኑ ይችላሉና፡፡ ይህንኑ ለማገዝም በቀለም የሚቀቡ ሥዕሎችና የመዝሙር ጥራዞችን ዝግጅት አጠናቀናል፡፡ በሙዓለ ሕፃናት ደረጃ የሚገኙ ልጆች ከትምህርታቸዉ ጋር ተያያዥነት ያለውን ርእሰ ጉዳይ ሥዕሉን ቀለም በመቀባት የሚቀስሙት ትምህርት የበለጠ ስለሚሆን የተዘጋጁትን ሥዕሎች በአግባቡ ቀለም እንዲቀቡአቸው የወላጆች እገዛ እጅግ አስፈላጊ ነው፡፡

በዓመቱ ውስጥ ባልተካተቱት ሁለት ሳምንታትም ገዳማትንና አብያተ ክርስቲያናትን መጐብኘታቸውና ክትትል ባለበት ሁኔታ በማኀበራዊ ነገሮች ተሳታፊ መሆናቸውም እጅግ ጠቃሚ ነው፡፡ ከሁሉም በላይ ግን መምህራን ለዚህ አገልግሎት በትጋት መጸለይና በየመካከሉ የሚቀሩ ወይም ጨርሰው ያልመጡ ልጆችንም መጐብኘት ይጠበቅባቸዋል፡፡ መምህራንን ማግኘት በማይቻልባቸው ሥፍራዎች ወላጆች በሥርዓተ ትምህርቱ በመመራት ልጆችን ማስተማር ይችላሉ፡፡ ልጆች በመንፈሳዊው ትምህርት እስከአሁን ድረስ ያደጉበት ሁኔታ ያልተመጣጠነ ስለሆነ የክፍል ደረጃቸው ከፍ ቢልም ከሙዓለ ሕፃናት መጽሐፍ ደረጃ ጀምረው መማራቸው ለመንፈሳዊዉ ዕዉቀታቸዉ መሠረት ስለሆነ ከፍተኛ ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡ በዚህ አጋጣሚም በየአብያተ ክርስቲያናቱ የተከፈቱ ትምህርት ቤቶችም ይህንን ሥርዓተ ትምህርት መጠቀማቸው ልጆች በየደረጃው ቤተ ክርስቲያናችንን እያወቁ፣ ሃይማኖታቸውን ተረድተውና በበጐ ሥነ ምግባር ታንጸው እንዲያድጉ የሚረዳቸው ይሆናል ብዬ አምናለሁ፡፡

በመጨረሻም ይኽን ዝግጅት የበለጠ ለማሻሻል የሁሉም አስተያየትና ምክር በጣም አስፈላጊ ስለሆነ እገዛችሁ እንዳይለየኝ እያልኩ አስቀድሞ በተጠቀሱት አድራሻዎች አስተያየቶቻችሁን እንድትልኩልኝ ስል በታላቅ ትሕትና እጠይቃለሁ፡፡

www.zeorthodox.org

# ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** **ልጆች እንደ ጃንደረባው ቅዱሳት መጻሕፍትን የማንበብ ልምድ እንዲያዳብሩ እና የመጻሕፍትን ምስጢር** የሚተረጉምላቸው ሰው አስፈላጊ መሆኑን እንዲገነዘቡ ማስተማር፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** “**ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር** ልጅ እንደሆነ አምናለሁ፡፡” ሐዋ.፰÷፴፯

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ሐዋ. ፰÷፳፮-፵፣ ሮሜ. ፲÷፲፬-፲፯፣ ማቴ. ፲፮÷፲፮-፲፱፣ ፪ጴጥ.፩÷፳-፳፩፣ ፳፩ ኢሳ. ፶፫÷፩-፲፪

## መግቢያ

- መምህሩ ያለፈውን ሳምንት ትምህርት ይከልስላቸው፡፡
- ልጆች ጃንደረባ ማለት ምን ማለት ነው?
- መጽሐፍ ቅዱስን የማንበብ ልምድ አላችሁ?
- መጽሐፍ ቅዱስን ስታነቡ ያልገባችሁ ነገር ሲኖር ምን ታደርጋላችሁ?

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

ቅዱስ ፊሊጶስ ከቤተ ክርስቲያን አባቶች መካከል አንዱ ሲሆን በኢየሩሳሌም አካባቢ በሚገኙ ከተሞች ከክርስቶስ ትንሣኤና ከበዓለ ሃምሳ በኋላ ወንጌልን ይሰብክ ነበር፡፡ ፊልጶስ ወደ ሰማርያ ከተማ ገብቶ ክርስቶስን ከሰበከላቸው በኋላ በጌታ መልአክ ለፊልጶስ ታየው “ተነሥተህ በደቡብ በኩል ከኢየሩሳሌም ወደ ጋዛ ወደሚያወርደው ምድረ በዳ ወደ ሆነ መንገድ ሂድ” አለው፡፡ ሐዋርያው ፊልጶስ የጌታ መልአክ እንደነገረው ተነሥቶ ሄደ፡፡ በምድረ በዳውም የኢትዮጵያ ንግሥት የህንደኬ አዛዥና ጃንደረባ የሆነው ኢትዮጵያዊ ሰው በሰረገላ ሲጓዝ ተመለከተ፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ጃንደረባ የሚለው ቃል ሁለት ነገሮችን ያመለክታል፡፡ የመጀመሪያው ከፍ ባለ ማዕርግ የሚሠራ ጠባቂ ሰውን የሚያመለክት ሲሆን ሁለተኛው ስልብ ሰውን ያመለክታል፡፡ ጃንደረቦች በድሮ ዘመን ታማኞች ሆነው ይቆጠሩ ስለነበር በቤተመንግሥት ይገኙ ነበር፡፡ በሐዲስ ኪዳን ከእናታቸው ማሕፀን ጀምሮ ጃንደረቦች የሚሆኑ እንዳሉ ክርስቶስ አስተምሯል፡፡ በዚህ ምክንያት ስለ ወንጌል ሚስት ያላገባ እና ሌላውንም የተፈቀደውን ምኞት የተወ ጃንደረባ ይባላል፡፡ (ማቴ.፲፱÷፲፩-፲፪) ኢትዮጵያውያን ከክርስትናው በፊት ወደ ኢየሩሳሌም እየሔዱ ለእግዚአብሔር ይሰግዱ ስለነበር በ፴፬ ዓ.ም የንግሥት ህንደኬ ጃንደረባ ለእግዚአብሔር ሊሰግድ ከኢትዮጵያ ወደ ኢየሩሳሌም ተጉዞ ነበር፡፡ በኢየሩሳሌም ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ እግዚአብሔርን አምልኮ ስለነበር በመንፈስ ቅዱስ መሪነት ሐዋርያው ፊልጶስ አገኘው፡፡

www.zoorthodox.org

ሐዋርያው ፊልጶስ ኢትዮጵያዊውን ጃንደረባ የነቢዩ የኢሳያስን መጽሐፍ እያነበበ በሰረገላ ሲጓዝ አገኘውና “የምታነበውን ታስተውለዋለህን?” ሲል ጃንደረባውን ጠየቀው፡፡ ጃንደረባውም “የሚመራኝ ሳይኖር እንዴት ላስተውልና ልረዳ እችላለሁ” ሲል መለሰለት፡፡ ሐዋርያው ፊልጶስ ሰረገላው ላይ ወጥቶ ከእርሱ ጋር እንዲቀመጥ፣ የነቢዩ የኢሳያስን ትንቢት እንዲተረጎምለት እና እንዲያስረዳው ጃንደረባው ለመነው፡፡ ሐዋርያው ፊልጶስም ለጃንደረባው ያነበው የነበረውን መጽሐፍ ትርጉም ነገረው፤ ስለ ክርስቶስ ወንጌልን ሰበከለት፡፡ ክርስቶስ ዓለምን ሊያድን እንደመጣ፣ ስለ ሰው ልጆች ኃጢአት እንደተሰቀለ፣ እንደሞተና በሦስተኛው ቀን እንደተነሣ ሐዋርያው ፊሊጶስ ሲሰብከው ጃንደረባው በክርስቶስ አመነ፡፡

በመንገድም ሲሔድ ውሃ ወዳለበት ስፍራ ደረሱ፣ በዚህ ጊዜ ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ ሐዋርያው ፊልጶስ እንዲያጠምቀው ለመነው፡፡ ፊልጶስም በፍጹም ልብህ ብታምን እንድትጠመቅ ተፈቅዶአል ሲለው ጃንደረባው “ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአአብሔር ልጅ እንደሆነ አምናለሁ” ሲል መሰከረ፣ ሰረገላውም እንዲቆም አዘዘ፡፡ ፊልጶስና ጃንደረባው ሁለቱም ወደ ውሃው ወረዱ ጃንደረባውም ተጠመቀ፡፡ ከውሃውም ከወጡ በኋላ የጌታ መንፈስ ፊልጶስን ነጠቀው ወንጌልን በአዛጦን እና በቂሳርያ ሊሰብክ ሔደ፡፡ ጃንደረባውም ፊልጶስን ሁለተኛ አላየውም ነገር ግን ደስ ብሎት ወደ ኢትዮጵያ ክርስቶስንና የክርስትና ሃይማኖትን ይዞ መጣ፡፡ በዚህ የተነሣ ከእስራኤል ቀጥሎ ክርስትናን በመቀበል ኢትዮጵያ የመጀሪያዋ ሀገር ሆነች፡፡

## ማጠቃለያ፡-

ልጆች በዚህ ትምህርት ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ እግዚአብሔርን ሊያመልክ ወደ ኢየሩሳሌም እንደተጓዘ፣ ወደ ኢትዮጵያ ሲመለስ መጽሐፍ ቅዱስ አያነበበ ሐዋርያው ፊልጶስ ወንጌልን ሰብኮለት ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ ነው ብሎ በፍጹም ልቡ ስላመነ እንደተጠመቀ እና ክርስትናን ወደ ኢትዮጵያ ይዞ እንደመጣ ተምራችኋል፡፡ ስለዚህ እናንተም እንደ ጃንደረባው መጽሐፍ ቅዱስን የማንበብ እና ያልገባችሁን ነገር የመጠየቅ ልምድ ሊኖራችሁ ይገባል፡፡

### *ጥያቄዎች፡-*

1. በመጽሐፍ ቅዱስ ጃንደረባ የሚለው ስም ምንን ያመለክታል?
2. ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ እያነበበ የነበረው መጽሐፍ ምን ይባላል?
3. ጃንደረባውን ያጠመቀው ሐዋርያ ማን ነው?
4. በጃንደረባው ዘመን የነበረችው የኢትዮጵያ ንግሥት ማን ትባላለች?
5. ሐዋርያው ፊልጶስ ጃንደረባውን ካጠመቀ በኋላ የት ሔደ?

www.zeorthodox.org

## ተግባር፡-

- መምህሩ ለልጆች ኢትዮጵያውያን ክርስትናን ከመቀበላቸው በፊት ለንግሥት ሳባ በቀዳማዊ ምኒልክ የአይሁድን እምነት ተቀብለው እንደነበር መጠነኛ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ያድርግ፡፡
- ልጆት ከጃንደረባው ሕይወት እና ጉዞ ምን እንደተማሩ እንዲወያዩ አድርግ፡፡

- እንደ ጃንደረባው ጉዞ በቤተ ክርስቲያን የሚዘጋጀ ልዩ ልዩ መንፈሳዊ ጉዞዎች ለመንፈሳዊ ሕይወት ያላቸውን ጠቀሜታ ንገራቸው፡፡
- መጽሐፍ ቅድስን ለመረዳት የመምህራንን እና የትርጓሜን አስፈላጊነት አጽንኦት በመስጠት ልጆች እንዲወያዩበት አድርግ፡፡
- ልጆች መጽሐፍ ቅዱስን ሲያነቡ ያልገባቸው ነገር እንዲሁም ጥያቄዎች ካሉአቸው ያለ ፍርሃት መምህራን ወንጌልን እንዲጠይቁ አበረታታቸው፡፡

www.zeorthodox.org

# አልዓዛር እና ባለጠጋው ሰው

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ልጆች ለሌሎች ማዘንን እንዲሁም በጎ ማድረግን እንዲለማመዱ መርዳት ነው፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "የሚምሩ ብፁዓን ናቸው፡ ይማራሉና፡፡" ማቴ. ፭፥፯

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ትርጓሜ ወንጌል፣ ማቴ. ፳፭፥፴፩-፵፮፣ ምሳሌ. ፫፥፳፯-፳፰፣ ፲፬፥፳፩፣ ሉቃ. ፲፮፥ ፲፱-፴፩

## መግቢያ

- መምህሩ ያለፈውን ሳምንት ትምህርት ይከልስላቸው፡፡
- ልጆች ምንም ለሌላቸው ምስኪኖች ታዝናላችሁ?
- ለሰዎች በጎ ነገሮችን የምታደርጉት ለምንድነው?
- ልጆች በዚህ ምድር በጎ ነገር ያደረጉ ሰዎች ሲሞቱ የት ይሔዳሉ ብላችሁ ታስባላችሁ?

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በተለያዩ ምሳሌዎች የእግዚአብሔርን መንግሥት ያስተምር ነበር፡፡ ከእነዚህ ምሳሌዎች መካከል የባለ ጠጋው እና የደሃው አልዓዛር ታሪክ በዋናነት የሚጠቀስ ነው፡፡ ዘወትር ያማረውን እየበላና እየጠጣ እንዲሁም እየለበሰ በብዙ ምቾች እና ደስታ ይኖር የነበረ አንድ ባለ ጠጋ ሰው ነበር፡፡ አልዓዛር የሚባል አንድ ድሃ በቁስል ሰውነቱ ተወርሶ በባለጠጋው ደጅ ተኝቶ ከባለ ጠጋው ማዕድ ከሚወድቀው ፍርፋሪ ሊጠግብ ይመኝ የነበረ ሲሆን ቁስሉን የሚጠግንበት ምግብ የሚሰጠው አንድም ሰው አልነበረም፡፡ በተለይ ባለ ጠጋው ደጁ ላይ የወደቀውን ደሃ አይቶ አላዘነለትም፡፡ አልዓዛርን መመገብ እና ማስታመም እየቻለ ይህን ባለማድረጉ አልዓዛር ሞተ፣ መላእክትም ወደ አብርሃም እቅፍ ወሰዱት፡፡

www.zeorthodox.org

ባለጠጋው ደግሞ ሞተና ተቀበረ በሲኦል ውስጥ በሥቃይ ሳለ አሻቅቦ ያ ደጁ ላይ ይተኛ የነበረውን ደሃውን አልዓዛር በአብርሃም እቅፍ አየው፡፡ ባለ ጠጋው ድምፁን ከፍ አድርጎ ጮኸ "የአብርሃም አባት ሆይ ማረኝ በዚህ በሲኦል ነበልባል እሰቃያለሁና አልዓዛር የጣቱን ጫፍ በውኃ ነክሮ ምላሴን እንዲያበርድልኝ አልዓዛርን ላክልኝ" ሲል ለመነው፡፡ አብርሃም ባለ ጠጋው የለመነው ነገር እንደማይቻል ነገረው፡፡ ባለጠጋው በድጋሚ አብርሃም አልዓዛርን ወደ አምስት ወንድሞቹ እንዲልከው እና ወደ ሥቃይ እንዳይገቡ እንዲመሰክርላቸው ለመነው፤ አብርሃም ግን ሙሴና ነቢያት አሉላቸው እነርሱን ይስሙ ሲል መለሰለት፡፡

## ማጠቃለያ፡-

ልጆች ከባለ ጠጋውና ከደሃው አልዓዛር ታሪክ በጎ ነገር ማድረግ ተገቢ እንደሆነ ለድሆች ማዘን እና መራራት እንደሚገባ ተምራችኋል፡፡ ባለጠጋው በሲኦል ሲሠቃይ የነበረው ሀብታም በመሆኑ ሳይሆን እግዚአብሔር ከሰጠው ላይ ለሌሎች ማካፈል ስላልቻለ እና ለእግዚአብሔር ቃል (ሕግ) ባለመታዘዙ ነው፡፡ አልዓዛርም በገነት በአብርሃም እቅፍ መኖር የቻለው ይህ ስለሆነ ሳይሆን እግዚአብሔርን ያመልክ፣ ይፈራ፣ ይታገስ እና ይጸና ስለነበር ነው፡፡ ስለዚህ ልጆች እናንተም እግዚአብሔር በሰጣችሁ ነገር ሁሉ ድሆችንና ምስኪኖችን እርዱ፣ በተቻላችሁ ሁሉ በጎ ነገር አድርጉላቸው፡፡ ይህን ለማድረጋችሁ ዋጋችሁን እግዚአብሔር እንደማያስቀር በብዙ እንደሚከፍላችሁ እመኑ፡፡

### *ጥያቄዎች፡-*

1. ባለጠጋው በደጁ የተኛውን አልዓዛርን ያልተንከባከበው ለምን ይመስላችኋል?
2. ባለጠጋው ለአልዓዛር ምን ማድረግ ይችል ነበር?
3. ሁሉም ባለጠጎች እንደዚህ ሰው ክፉ ናቸው ማለት እንችላለን?
4. ሁሉም ድሆች እንደ አልዓዛር መልካም ናቸው ልንል እንችላለን?
5. ሙሴን እና ነቢያትን ይስሙ ማለት ምን ማለት ነው?

## ተግባር፡-

- መምህሩ ልጆች ሰውን ክፉ የሚያደርገው ሀብት ሳይሆን የአመለካከት ችግር እንደሆነ እንዲገነዘቡ ያድርጋቸው፡፡
- ልጆች ድሆችን እና ምስኪኖችን ባላቸው አቅም ከአሁን ጀምሮ እንዴት መርዳት እንደሚችሉ ይወያዩበት፡፡

www.zeorthodox.org

# የማታው ተማሪ

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ሰው ከእግዚአብሔር የሚወለድበትን ምስጢር መማር፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "ሰው ከውኃና ከመንፈስ ካልተወለደ በቀር ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሊገባ አይችልም፡፡" ዮሐ. ፫÷፭

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ዮሐ.፫÷፩-፲፭፣ ኤፌ.፬÷፬፣ ማቴ.፳፰÷፲፱-፳፣ ሕዝ. ፴፮÷፳፭-፳፮

## መግቢያ፡-

- መምህሩ ያለፈውን ሳምንት ትምህርት ይከልስላቸው፡፡
- ልጆች ኒቆዲሞስን ታውቁታላችሁ?
- ከእግዚአብሔር የተወለዳችሁት መቼ ነው?
- የክርስትና ስማችሁን ታስታውሳላችሁ?
- የክርስትና እናት እና አባት ያስፈለገበት ምክንያት ምንድ ነው?

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው ሆኖ በዚህ ምድር በሚመላለስበት ጊዜ በቃሉ ትምህርት በእጁ ተአምራት ብዙ ሰዎችን እንደለወጠ በወንጌል ተጽፎ እናነባለን፡፡ ሰዎች ለተለያየ ነገር ወደ ክርስቶስ ቢመጡም እርሱ ግን የእግዚአብሔርን መንግሥት ያለመሰልቸት ይሰብካቸው ነበር፡፡ ከዕለታት አንድ ቀን ኒቆዲሞስ የሚባል ሰው በሌሊት ወደ ኢየሱስ መጣ፡፡ ኒቆዲሞስ ከፈሪሳውያን ወገን ሲሆን በዘመኑ የነበረውን የአይሁድን ትምህርት ጠንቅቆ የተማረ ምሁር ነበር፡፡ የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው ሆኖ ወደዚህ ዓለም ቢመጣም ብዙ ሰዎች አልተቀበሉትም ነበር፡፡ በተለይ ፈሪሳውያን በወንጌል ተጽፎ እንደምናነበው በተደጋጋሚ ለእግዚአብሔር ቃል ያላቸውን እንቢተኝነት ገልጸዋል፡፡

www.zeorthodox.org

ፈሪሳውያን ሕዝቡ የክርስቶስን ትምህርት እንዳይሰማ እና የእርሱ ደቀመዝሙር እንዳይሆን ዓዋጅ አውጀውም ነበር፡፡ በዚያን ዘመን የክርስቶስ ተማሪ (ደቀመዝሙር) መሆን ያስነቅፍ እና የተለያዩ መገለሎችን ያስከትል ነበር፡፡ በዚህ ምክንያት ኒቆዲሞስ በሌሊት መጥቶ ከመማር ይልቅ ሌሊትን የመረጠበት ምክንያት ከፈሪሳውያን ወገን ስለሆነና የታወቀ መምህር ስለነበር ከፈሪሳውያን ከፍተኛ ተቃውሞ እንዲሁም መገለል እንዳይደርስበት በመፍራት ነበር፡፡ ክርስቶስ ግን ሌሊትም ለኒቆዲሞስ ጊዜ ነበረው፡፡ ኒቆዲሞስ በሌሊት ወደ ኢየሱስ መጥቶ ኢየሱስ ክርስቶስ መምህር ሆኖ ከእግዚአብሔር ዘንድ እንደመጣ መሰከረ፡፡ ነገር ግን ይህን እውቀቱን

ክርስቶስ አላደነቀለትም፡፡ ስለዚህ “ሰው ከውሃና ከመንፈስ ካልተወለደ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት መግባት እንደማይችል” ነገረው፡፡ ስለእግዚአብሔር ማወቅ እና መናገር ብቻ በቂ እንዳልሆነ ነገር ግን በእግዚአብሔር ማመን ከእግዚአብሔር በጥምቀት መወለድ እና የእግዚአብሔርን ሥራ መሥራት ተገቢ እንደሆነ ለኒቆዲሞስ ጌታ ነገረው፡፡ ኒቆዲሞስ ሰው ከእግዚአብሔር የሚወለድበት ምስጢር ስላልገባው ተደንቆ “ሰው ከሸመገለ በኋላ እንዴት ሊወለድ ይችላል? ሁለተኛ ወደ እናቱ ማሕፀን ገብቶ ይወለድ ዘንድ ይችላልን?” ሲል ክርስቶስን ጠየቀ፡፡ ክርስቶስም ሰው ከእግዚአብሔር በሥጋ ሳይሆን በጥምቀት ከውሃና ከመንፈስ እንደሚወለድ ምስጢሩን ነገረው፡፡ ይህን የጌታችንን የኢየሱስ ከመንፈስ እግዚአብሔር የሚወለድበትን ምስጢር ምስጢረ ጥምቀት በማለት ትጠራዋለች፡፡ ምስጢር የተባለበት ምክንያት በሚታይ አገልግሎት የማይታይ ጸጋ፣ ሀብት እንዲሁም ልጅነት በዐርባ ቀን ሴቶችን ደግሞ በሰማንያ ቀን ታጠምቃለች፡፡ ሕፃናት ከውሃና ከመንፈስ ተወልደው የእግዚአብሔር ልጆች ይሆናሉ፡፡

ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔር መንግሥት ስለሆነች ሕፃናት በእግዚአብሔር መንግሥት የሚታወቁበትን መጠሪያ ስም (የክርስትና ስም) ትሰጣቸዋለች፡፡ ሕፃናት በቤተሰባቸው እና በክርስትና አባት ወይም እናት እምነት ተጠምቀው የእግዚአብሔር ልጆች እና የመንግሥተ ሰማይ ዜጋ ይሆናሉ፡፡ ቤተሰብ እንዲሁም የክርስትና አባት እና እናት ለሕፃናት እምነትን እና ምግባርን የማስተማር ኃላፊነት እንዲሁም ግዴታ አለባቸው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ቤተ ክርስቲያን አዲስ አማኒያንን ታጠምቃለች፡፡ ማንኛውም ሰው ከተጠመቀ በኋላ ሜሮን ይቀባል፡፡ በሜሮኑ መንፈስ ቅዱስ ያድርበታል፡፡ ጥምቀት በሥላሴ ስም ነው ማለት በአብ፣ በወልድ እና በመንፈስ ቅዱስ ስም የሚፈጸም አገልግሎት ነው፡፡ ጥምቀት አይደገምም፣ ከሥጋ እናታችን እንዴ ብቻ እንደምንወለድ ከእግዚአብሔርም አንድ ጊዜ ብቻ ነው የምንወለደው፡፡ ሰው ከውሃና ከመንፈስ በጥምቀት ከሥላሴ ካልተወለደ የእግዚአብሔርን መንግሥት ሊወርስ አይችልም፡፡

## ማጠቃለያ፡-

ልጆች ከዚህ ትምህርት ማንኛውም ሰው ከውሃና ከመንፈስ በጥምቀት ከእግዚአብሔር ካልተወለደ በቀር የእግዚአብሔርን መንግሥት ሊወርስ እንደማይችል ተገንዝባችኋል፡፡ ክርስቶስ የመማር ፍላጎት እንደኒቆዲሞስ ላለው ሁሉ መቼም ቢሆን እንደማይደክመው እና ለእያንዳንዳችን ጊዜ እንዳለውም አውቃችኋል፡፡ ኒቆዲሞስ ምሁር ሲሆን በትሕትና ከጌታ ለመማር ስለመጣ ሰማያዊ ምስጢርን እንደተማረ አስተውላችሁ የሁል ጊዜ ተማሪ ሁኑ፡፡

www.zeorthodox.org

### ጥያቄዎች፡-

1. የማታው ተማሪ ማን ነበር?
2. ኒቆዲሞስ በሌሊት ወደ ክርስቶስ የመጣበት ምክንያት ምንድነው?
3. ሰው ዳግመኛ ከእግዚአብሔር እንዴት ሊወለድ ይችላል?

4. የክርስትና አባት እና እናት ተግባር ምንድነው?
5. የክርስትና ስም ለምን አስፈለገ?
6. ጥምቀት ለምን አንድ ጊዜ ብቻ ይፈጸማል?
7. ጥምቀት ለማን ስም ነው?

## ተግባር፡-

- ልጆች ከኒቆዲሞስ ሕይወት ምን ተማራችሁ? ለመምህራችሁ እና ለጓደኞቻችሁ ተናገሩ፡፡
- የእግዚአብሔር ልጆች በመሆናችሁ የመንግሥቱ ተካፋዮች እንዴት እንደሆናችሁ ግለጹ፡፡
- የእግዚብሔርን መንግሥት መውረስ ማለት ምን እንደሆነ ተወያዩበት፡፡

www.zeorthodox.org

# ልደታ ለማርያም

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** የእመቤታችን የድንግል ማርያምን የልደቷን ታሪክ መማር፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** “ከሴቶች መካከል የተባረክሽ ነሽ፡፡” (ሉቃ. ፩÷፳፰)

**ተጨማሪ ምንባባት፡-**

⇒ ግንቦት አንድ ቀን የሚነበብ ስንክሳር መጽሐፍ፡፡

⇒ ነገረ ማርያም (ስለ እመቤታችን ታሪክ የተጻፉ ልዩ ልዩ መጻሕፍት)

## መግቢያ፡-

- መምህሩ ያለፈውን ሳምንት ትምህርት ይከልስላቸው፡፡
- ልጆች የድንግል ማርያም ልደት በቤተ ክርስቲያን መቼ እንደሚከበር ታስታውሳላችሁ?
- ቤተ ክርስቲያን የእመቤታችንን ልደት የምታከብርበት ምክንያት ምንድነው?

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

ልጆች የእመቤታችን የድንግል ማርያም የልደት ታሪክ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አልተጻፈም ነገር ግን በቤተ ክርስቲያን የታሪክ እና የትውፊት መጻሕፍት ውስጥ የልደቷ ታሪክ በስፋት ተዘርዝሮ ይተረካል፡፡ እነዚህ መጻሕፍት እንደሚነግሩን የእመቤታችን ወላጆች ኢያቄም እና ሐና በእግዚአብሔር ፊት ጻድቃን ሆነው እንደ እግዚአብሔር ሕግ ድሆችን እየረዱ እና እየተንከባከቡ ይኖሩ ነበር፡፡ ነገር ግን በትዳር ሕይወታቸው ልጅ አልነበራቸውም፤ በዚህ የተነሣ ለብዙ ጊዜ በጸሎትና በጾም እግዚአብሔርን ልጅ እንዲሰጣቸው ይጠይቁ ነበር፡፡ ተስፋ ሳይቆርጡ በእምነት ሁነው በትዕሥት እግዝአብሔርን ስለጠበቁ እግዚአብሔር የጸሎታቸውን ምላሽ የምሥራቹን እንዲነጋር መልአኩን ወደ ኢያቄም ላከ፡፡ መልአኩም በሕልም ለኢያቄም እግዚአብሔር ጸሎታቸውን እንደሰማ እና ልጅ እንደሚሰጣቸው ነገርው፡፡ ይህን የምሥራች ኢያቄም ለሚስቱ ሐና ነገራት፡፡ እግዚአብሔር እንዳለው ሐና በእርጅናዋ ፀነሰች፡፡ በሐና መፀነስ ከተገረሙት መካከል የሐና አክስት እንዷ ነበረች፡፡ የሐና አክስት አንድ ዐይን የነበራት ሲሆን በሐና መፀነስ ተደንቃ የሐናን ማሕፀን በእጇ ዳሰሰች፡፡ ሐና መፀነሷን በእጇ ዳስሳ ካረጋገጠች በኋላ በዚያው እጇ ዓይኗን ስትነካው ለብዙ ዘመናት ማየት የተሳነው ዓይን በራ፡፡ ይህን ተአምር የሰሙ ብዙ ሰዎች ወደ ሐና እየመጡ ማሕፀኗን እየዳሰሱ ከተለያየ በሽታ ይድኑ ይፈወሱም ነበር፣ ልዩ ልዩ ተአምራትም ይደረግላቸው ነበር፡፡ እመቤታችን ገና በእናቷ በቅዱስት ሐና ማሕፀን ሆና ድንቅ ተአምራት ታደርግ እንደነበር ከዚህ ታሪክ እንገነዘባለን፡ ነገር ግን እግዚአብሔር በሐና ማሕፀን ልዩ ልዩ ድንቃድንቅ ተአምራት ሲሠራ ያዩ አይሁድ ቀንተው ከፍተኛ ጥላቻ ስለአደረባቸው ሐና እና እያቄም ወደ ሊባኖስ ተራራ ተሰደዱ፡፡ ግንቦት አንድ ቀን እመቤታችን

www.zeorthodox.org

በሊባኖስ ተራራ ላይ ተወለደች ቅዱሳን ወላጆቿ በመወለዷ በጣም ተደስተው እና እግዚአብሔርን አመስግነው ስሟን ማርያም ብለው ጠሯት፡፡ ሐና እና ኢያቄም እመቤታችንን ከመውለዳቸው በፊት ስለት ተስለው ስለነበር እመቤታችን ሦስት ዓመት ሲሆናት ወደ ቤተመቅደስ አመጧት፤ እስከ ዐስራ አምስት አመቷ በቤተመቅደስ እያገለገለች ኖራለች፡፡ እግዚአብሔርም የልጁ እናት እንድትሆን መረጣት፡፡ ይህ የእመቤታችን የልደት ታሪክ በመጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮ ተመሳሳይ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ አብርሃምና ሳራ፣ ይስሐቅ፣ ርብቃ፣ ሐና እና ሕልቃና እንዲሁም ዘካርያስ እና ኤልሳቤጥ ለብዙ ዘመናት በትዳር ሕይወታቸው ልጅ ያልነበራቸው የእግዚአብሔር ሰዎች ነበሩ፣ ነገር ግን በእምነት እና በተስፋ እግዚአብሔርን በትዕግሥት በመጠበቃቸው የመውለጃቸው ዘመን ካለፈ በኋላ እግዜአብሐር ልጅ ሰጥቷቸዋል፡፡ (ዘፍ. ፳፩÷፩-፯፣ ፳፭÷፲፱-፳፯፣ ፩ሳሙ.፩÷፲፱-፳፣ ሉቃ.፩÷፭-፳፭)

## ማጠቃለያ፡-

ልጆች በዚህ ትምህርት ስለ እመቤታችን ድንግል ማርያም የልደት ታሪክ በቂ ግንዛቤ ጨብጣችኋል፡፡ ቤተ ክርስቲያን የእመቤታችንን ልደት መቼ፣ እንዴት እና ለምን እንደምታ ከብርም አውቃችኋል፡፡ ስለዚህ እናንተም ከሐና እና ከኢያቄም በእምነት፣ በተስፋ እና በትዕግሥት ሆናችሁ የጸሎታችሁን መልስ ከእግዚአብሔር ዘንድ ጠብቁ፡፡ ለሰዎች በጎ ነገር ማድረግንም ተለማመዱ፡፡

### *ጥያቄዎች፡-*

1. እመቤታችን ድንግል ማርያም የት እና መቼ ተወለደች?
2. የወላጆቿ ስም ማን ይባላል?
3. የእመቤታችንን የልደት ታሪክ የምናገኝባቸው የቤተ ክርስቲያን መጻሕፍት እነማን ናቸው?
4. ሐና እና ኢያቄም ወደ ሊባኖስ ተራራ የተሰደዱበት ምክንያት ምን ነበር?
5. የእመቤታችን የልደት ታሪክ በመጽሐፍ ቅዱስ ያልተጻፈበት ምክንያት ምንድነው?
6. ከዚህ ታሪክ ምን ተማራችሁ?

## ተግባር፡-

- መምህሩ ለልጆች ስለ አዋልድ መጻሕፍት መጠነኛ መረጃ ይስጣቸው፡፡
- ልጆች ከሐና እና ከኢያቄም ሕይወት ጋር ተመሳሳይነት ያላቸውን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ታሪኮች ለጓደኞቻችሁ ንገሩ፡፡

www.zeorthodox.org

# የድንግል ማርያም ክብር

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ለልጆች የድንግል ማርያምን ክብር ማስተማር፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "ትውልድ ሁሉ ብፅዕት ይሉኛል" ሉቃ. ፩÷፵፰

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ሉቃ.፩÷፳፮-፶፫፣ ማቴ.፩÷፲፰-፳፫፣ ዮሐ.፲፱÷፳፮-፳፯፣ ሕዝ.፵፬÷፩-፪

## መግቢያ፡-

- ማምህሩ ያለፈውን ሳምንት ትምህርት ይከልስላቸው፡፡
- ልጆች ድንግል ማርያምን ለምንድነው የምታከብሯት?
- ለድንግል ማርያም ያላችሁን ክብር በምንድነው የምትገልጹት?

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

ልጆች ባለፈው ሳምንት ትምህርታችን ስለ ድንግል ማርያም የልደት ታሪክ እንደተማርን ታስታውሳላችሁ፡፡ ዛሬ በዚህ ትምህርት ደግሞ ክብሯን እንማራለን፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ "ክብር" የሚለው ቃል ጌትነትን፣ ከፍተኛነትን፣ ብርሃንነትን እና ከእግዚአብሔር ሰው የሚቀበለውን ዋጋ ወይም ሹመትን ያመለክታል፡፡ እግዚአብሔር ብዙ ሰዎችን ለተለያዩ አገልግሎቶች በመምረጥ አክብሯል፡፡ ድንግል ማርያምን የልጁ እናት እንድትሆን በመምረጥ አክብሯታል፡፡ በዚህ የተነሣ ድንግል ማርያም ቅድስተ ቅዱሳን ትባላለች፡፡ ይህም ከተመረጡት በላይ የተመረጥሽ፣ ከተለዩት በላይ የተለየሽ፣ ከተቀደሱት በላይ የተቀደስሽ ነሽ ማለት ነው፡፡ ሌሎች ሲመረጡ ፈጣሪያቸውን እንዲያገለግሉ ነው፣ እርሷ ግን የፈጣሪዋ እናት ለመሆን የተመረጠች ናት፡፡ ከእርሷ በፊትም በኋላም የአምላክ እናት የተባለች ሴት የለችም፡፡

www.zeorthodox.org

ድንግል ማርያም ግን የአምላክ እናተ ናት፡፡ የመላእክት ማደሪያ (ማኅደረ መለኮት) ናት፡፡ ቤተ ክርስቲያን እመቤታችንን እግዚአብሔር የልጁ የኢየሱስ ክርስቶስ እናት እንድትሆን ስለመረጣት እና ስላከበራት ክብር ታከብራታለች፣ በቀደሳት ቅዳሴ ትቀድሳታለች፣ ባመሰገናት ምስጋና ታመሰግናታለች፣ በገብርኤል ሰላምታ ለእመቤታችን ሰላምታ ታቀርባለች፡፡ እመቤታችንን የመረጠ፣ የለየ፣ ያከበረና ከፍ ከፍ ያደረገ ራሱ እግዚአብሔር ነው፡፡ የካህኑ ዘካርያስ ሚስት ኤልሳቤጥ መንፈስ ቅዱሳን ተመልታ "አንቺ ከሴቶች መካከል የተባረክሽ ነሽ፣ የማሕፀንሽም ፍሬ የተባረከ ነው፡፡ የጌታዬ እናት ወደ እኔ ትመጣ ዘንድ እንዴት ይሆንልኛል? . . . ከጌታ የተነገረላት ቃል ይፈጸማልና ያመንህት ብፅዕት ናት" (ሉቃ. ፩÷፵፪-፵፭) ስትል የድንግል ማርያምን ክብር

መንፈስ ቅዱስ ገልጠላት ተናግራለች፡፡

ሌሎች ሴቶች ንጉሥን፣ ካህንን፣ ነቢያትን፣ ሐዋርያን፣ ቅዱሳን . . . ወዘተ ወልደዋል ድንግል ማርያም ግን የኤልሳቤጥን አምላክ ወልዳለች፡፡ ኤልሳቤጥ ጻድቅ ናት በእድሜም ከእመቤታችን የምትበልጥ አሮጊት ናት፤ ነገር ግን የእመቤታችን ጽድቅ ከእርሷ እንደሚበልጥ አውቃ እመቤታችንን አከበረቻት፡፡ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ እግዚአብሔር የመረጣቸውን ማክበር እንደሚገባ በሮሜ መልእክቱ "እግዚአብሔር የመረጣቸውን ማን ይከሳቸዋል? የሚያጸድቅ እግዚአብሔር ነው" (ሮሜ. 8÷33) በማለት አስተምሯል፡፡ ስለዚህ ቤተ ክርስቲያን የሐዋርያትን ትምህርት መሠረት በማድረግ በሚከተሉት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምስክርነቶች እመቤታችንን ታከብራለች፡፡

- ☚ ከሌሎች ሴቶች ለይታ እመቤታችንን ታከብራለች፡፡
- ☚ ቅዱስ ገብርኤል ክብሯን በምስጋናው በመግለጡ፡፡ (ሉቃ. ፩÷፳፰-፳፱)
- ☚ ኤልሳቤጥ በመንፈስ ቅዱስ ተቃኝታ የእመቤታችንን ክብር በመናገሯ፡፡
- ☚ ጌታ ለዮሐንስ አደራ ሲሰጥ ክብሯን ገልጧል፡፡
- ☚ ስሟ ያልተጠቀሰ አንዲት ሴት ክብሯን በመናገሯ፡፡ (ሉቃ.፲፩÷፳፯)
- ☚ እመቤታችን ራሷ "እነሆ ከዛሬ ጀምሮ ትውልድ ሁሉ ብፅዕት ይሉኛል" (ሉቃ. ፩÷፵፰) በማለቷ፡፡

በእነዚህ ከላይ በተዘረዘሩት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርቶች አማካኝነት ቤተ ክርስቲያን እመቤታችን ድንግል ማርያምን ከፈጣሪ በታች ከፍጡራን በላይ የሆነ ማዕርግ ሰጥታ ታከብራታለች፡፡

## ማጠቃለያ፡-

ልጆች በዚህ ትምህርት እግዚአብሔር ድንግል ማርያምን እንዴት እንዳከበራት በቂ ዕውቀት አግኝታችኋል፡፡ ስለዚህ እግዚአብሔር ባከበራት ክብር እመቤታችንን ማክበር እና ማመስገንን የዕለት ተዕለት ተግባራችሁ አድርጉ፡፡ የእግዚአብሔር መንፈስ ሳይሆን በርኩስ መንፈስ ተመርተው የድንግል ማርያምን ክብር የሚያቃልሉትን እና የሐሰት ትምህርት የሚያስተምሩትን አትከተሉ፡፡

www.zeorthodox.org

### ጥያቄዎች፡-

1. ቤተ ክርስቲያን ድንግል ማርያምን የምታከብርባቸውን ምክንያቶች ዘርዝር፡፡
2. ድንግል ማርያምን ከሌሎች ሴቶች ልዩ የሚያደርጋት ምንድነው?
3. በመንፈስ ቅዱስ ተቀኝታ የእመቤታችንን ክብር የተናገረች ሴት ማን ናት?
4. መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል እመቤታችንን ያመሰገነበት ምስጋና በየትኛው ወንጌል ተጽፎ ይገኛል?

## ተግባር፡-

- መምህሩ ልጆች ለእመቤታችን ለድንግል ማርያም ያላቸውን ፍቅር እና ክብር እንዴት መግለጽ እንደሚችሉ መንገዶቹን ይጠቁማቸው፡፡
- ልጆች እመቤታችንን ማክበር እና ማመስገን ከማን እንደተማራችሁ ለመምህራችሁ እና ለጓደኞቻችሁ ግለጹ፡፡

www.zeorthodox.org

# ቅዱስ ያሬድ

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ለልጆች የቅዱስ ያሬድን ታሪክ ማስተማር፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "ጻድቅ ሰባት ጊዜ ይወድቃልና ይነሣማል፡፡" ምሳሌ. ፳፬÷፲፮

**ተጨማሪ ምንባባት፡-**

- መምህር ኀሩይ ኤርምያስ መዝገበ ታሪክ ክፍል ሁለት ፲፱፻፺፫ ዓ.ም አዲስ አበባ፡፡
- ስንክሳር ግንቦት ዐሥራ አንድ ቀን የሚነበበው፡፡
- ስለ ቅዱስ ያሬድ ሕይወት እና ሥራዎች መረጃ የሚሰጡ መጻሕፍትን አንብቡ፡፡

## መግቢያ፡-

☛ መምህሩ ያለፈውን ሳምንት ትምህርት ይከልስላቸው፡፡

☛ ልጆች ስለ ቅዱስ ያሬድ የምታውቁትን ለመምህራችሁ ንገሩ፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

ቅዱስ ያሬድ ከአባቱ አዳም እና ከእናቱ ታውክልያ በ505 ዓ.ም በአክሱም ተወለደ፡፡ አባቱ ካህን ስለነበር ዕድሜው ለትምህርት ሲደርስ ፊደል እንዲማር ይስሐቅ ለሚባል መምህር ሰጡት፡፡ ከመምህር ይስሐቅ ፊደል አጥንቶ እንደጨረሰ መዝሙረ ዳዊት ሊማር የእናቱ ወንድም ወደሆኑት ወደ መምህር ጌዴዎን ሄዶ መማር ጀመረ፡፡ ነገር ግን ሰባት ዓመት ተምሮ ምንም የሚያውቀው ነገር አልነበረም፡፡ ከዕለታት አንድ ቀን መምህሩ ቅዱስ ያሬድን ጥያቄ ሲጠይቁት መመለስ ስላልቻለ በዚህ ተቆጥተው ገረፉት፡፡ ቅዱስ ያሬድ ሸሽቶ ወደ እናቱ ቤት ሲጓዝ መንገዱ ስለደከመው እና ፀሐይ ስለአቃጠለው ለዕረፍት አንድ ዛፍ ጥላ ሥር ተቀመጠ፡፡ በዚህ ጊዜ አንዲት ትል ዛፍ ላይ ለመውጣት ታደርግ የነበረውን ብርቱ ጥረት ተመለከተ፡፡ ይህች ትል ስድስት ጊዜ እየወጣች እና እየወደቀች ብርቱ ትግል ካደረገች በኋላ በሰባተኛው ግን ዛፉ ላይ መውጣት ቻለች፡፡ ይህ ክስተት የቅዱስ ያሬድን አመለካከት የቀየረ ትልቅ የሕይወት ትምህርት ሆነ፡፡ ቅዱስ ያሬድ እርሱም እንደ ትሉ እስከ መጨረሻው ቢጸና ትምህርቱ እንደሚገለጽለት በማመን ወደ መምህሩ እንደገና ተመለሰ፡፡ ከዚህ በኋላ ጌታ ኅሊናውን ንጹሕ ልቦናውን ብሩህ አድርጎለት ትምህርት ይገባው ጀመር፡፡ ከዕለታት አንድ ቀን ጌታ ሦስት አዕዋፋት (ወፎች) ከገነት ልኮለት በሰው ቋንቋ ሲያነጋግሩት ቅዱስ ያሬድ ተመስጦ መጣበት፣ ጌታ በመላእክት ሲመሰገንም ሰማ፡፡ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ የዜማ እና የመጻሕፍት ምስጢር ተገልጾለት በዜማ እግዚአብሔርን ማመስገን ጀመረ፡፡ ቅዱስ ያሬድ በዜማ እግዚአብሔርን ሲያመሰግን ብዙ ሰዎች በተመስጦ ይሰሙት ነበር፡፡ በተለይ በዘመኑ የነበሩት ዐፄ ገብረ መስቀል ለቅዱስ ያሬድ ዜማ ከፍተኛ ፍቅር ስለነበራቸው በቤተመንግሥታቸው ቅዱስ ያሬድን ያኖሩት ነበር፡፡ አንድ ቀን ቅዱስ ያሬድ በንጉሥ ዐፄ ገብረመስቀል ፊት ቆሞ ሲያመሰግን ንጉሡ ተመስጠው ሳያውቁ በያዙት ጦር እግሩን ወጉት በዚህ ንጉሡ

www.zeorthodox.org

በጣም ተጸጽተው ምን ላድርግልህ ሲሉ ቅዱስ ያሬድን ጠየቁት፡፡ ቅዱስ ያሬድ ንጉሡ ወደ ገዳም እንዲሔድ እና በዚያ እንዲኖር እንዲፈቅዱለት ጠየቀ፡፡ ንጉሡ እንዳሰናበቱት ቅዱስ ያሬድ ደቀመዛሙርቱን አስከትሎ ማስተማር ጀመረ፤ አምስት ድርሰቶችንም አበረከተ፡፡ አምስቱ የቅዱስ ያሬድ ድርሰቶች ድጓ፣ ጾመ ድጓ፣ ምዕራፍ፣ ዝማሬና መዋሥዕት ናቸው፡፡ ቅዱስ ያሬድ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የዜማ ሊቅ (አባት) እየተባለ የሚጠራ ሲሆን ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ያሬድን እና ዜማውን አክብራ እና ጠብቃ እዚህ ዘመን ደርሳለች፡፡

## ማጠቃለያ፡-

ልጆች ቅዱስ ያሬድ ትምህርት የማይገባው ሰው እንደነበር በኋላ ግን ከአንዲት ትል ባገኘው ትምህርት ወደ ትምህርት ቤት ተመልሶ ጎበዝ ተማሪ ለመሆን እንደቻለ ከዚህ ትምህርት ተረድታችኋል፡፡ እናንተም ተስፋ ሳትቆርጡ ደጋግማችሁ በማጥናት እና በመመራመር ጎበዝ ተማሪዎች መሆን ትችላላችሁ፡፡

### *ጥያቄዎች፡-*

1. ቅዱስ ያሬድ መቼ እና የት ተወለደ?
2. ቤተሰቦቹ ማን ይባላሉ?
3. ቅዱስ ያሬድ መዝሙረ ዳዊትን ከማን ተማረ?
4. ቅዱስ ያሬድ እንደገና ወደ ትምህርት ቤት እንዲመለስ ምክንያት የሆነው ነገር ምን ነበር?
5. የቅዱስ ያሬድ ድርሰቶች ስንት ናቸው?

## ተግባር፡-

- መምህሩ የቅዱስ ያሬድ ድርሰቶችን ይዘት እና ዝርዝር ለልጆች ይግለጽላቸው፡፡
- ልጆች እንደ ቅዱስ ያሬድ ከተፈጥሮ ብዙ ነገሮችን እንዴት መማር እንደሚችሉ አወያያቸው፡፡

www.zoorthodox.org

# አክዓብ እና ናቡቴ

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ልጆች ባላቸው ነገር ረክተው የሌሎችን ነገር ከመመኘትና በሌሎች ከመቅናት ራሳቸውን እንዲጠብቁ ማስተማር፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "ያላችሁም ይብቃችሁ፡፡" ዕብ.፲፫÷፭

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ፩ነገ. ፲፮÷፳፰-፳፪÷፵፣ ፳÷፩-፳፱፣ ፪ዜና. ፲፰፣ ዘጸ. ፳÷፲፮-፲፯፣፳፭÷፳፫

## መግቢያ፡-

- መምህሩ ያለፈውን ሳምንት ትምህርት ይከልስላቸው፡፡
- ልጆች ባላችሁ ነገር ደስተኞች ናችሁ?
- በእናትና ወንድሞቻችሁ ነገር ቀንታችሁ ወይም የእነርሱን ነገር ተመኝታችሁ ታውቃላችሁ?
- ልጆች የምትፈልጉትን ነገር ጠይቃችሁ ሳታገኙ ስትቀሩ ምላሻችሁ ምንድነው?

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

ንጉሥ አክዓብ ከ፰፻፸፬-፰፻፶፫(874-853) ቅድመ ልደተ ክርስቶስ በእስራኤል ላይ የነገሠ ሰባተኛ የእስራኤል ንጉሥ ነው፡፡ አክዓብ ማለት የስሙ ትርጉም የአባት ወንድም ማለት ሲሆን በመንግሥት አስተዳደር በኩል ጠንካራ ንጉሥ ነበር፡፡ ንጉሥ አክዓብ የእስራኤልን አምላክ የማታምን ጣዖትን የምታመልክ ኤልዛቤል የተባለች ሚስት ስለነበረችው እግዚአብሔርን የማይፈራ ንጉሥ ነው፡፡ በዚህ የተነሣ በእግዚአብሔር ፊት ክፋት ለመሥራት ራሱን የሸጠ ንጉሥ ከመሆኑም በላይ ሚስቱ ኤልዛቤል የምትመራው፣ ባዕድ አመልኮን የሚያስፋፉና ክፉ ነገርን የሚያደርግ ሆነ፡፡ (፩ነገ. ፲፮÷፴፩፣ ፩ነገ. ፳÷፳፭) በንጉሥ አክዓብ ቤተመንግሥት አጠገብ የወይን ቦታ የነበረው ናቡቴ የሚባል ሰው ነበር፡፡

አክዓብ የናቡቴን የወይን ቦታ ዘወትር በዓይኑ እየተመለከተ የራሱ ለማድረግ ይመኝ ስለነበር ከዕለታት አንድ ቀን ናቡቴ የወይን ቦታውን እንዲሸጥለት ወይም በሌላ ቦታ እንዲለውጠው ጠየቀው፡፡ ናቡቴ የአባቶችን ርስት መሸጥ በሕግ የተከለከለ ስለነበር "የአባቶቼን ርስት አልሰጥህም" ሲል ለንጉሥ አክዓብ መለሰ፡፡ ንጉሥ አክዓብ የልቡ ፍላጎትና ምኞት እንዳልተሳካ ባወቀ ጊዜ በጣም ተናደደ፤ ወደ ቤቱ ገብቶ እንጀራ አልበላም ብሎ ተሸፋፍኖ ተኛ፡፡ ሚስቱ ኤልዛቤል ለምን እንዳዘነ ስትጠይቀው ናቡቴ የአባቶቹን ርስት ለመስጠት ፈቃደኛ እንዳልሆነ ነገራት፡፡ ሚስቱ ኤልዛቤልም የናቡቴን ርስት እንደምትሰጠው ቃል ገብታለት አጽናናችው፡፡

www.zeorthodox.org

ኤልዛቤል በንጉሥ አክዓብ ስም ደብዳቤ ጽፋ በማኅተም አትማ ወደ ከተማው ሽማግሌዎች እና ከበርቴዎች ደብዳቤውን ላከች፡፡ ደብዳቤው ናቡቴን በሐሰት ክስ እና ምስክሮች እሰኪሞት ድረስ ከሰፈር አውጥተው እንዲገሉት የሚያዝ ነበር፡፡ በከተማው የሚኖሩ ሽማግሌዎችና ከበርቴዎች ኤልዛቤል እንዳዘዘቻቸው አደረጉ፡፡ ናቡቴ በድንጋይ ተደብድቦ (ተወግሮ) ሞተ፡፡ ወደ ኤልዛቤልም ናቡቴ እንደሞተ መልእክት ላኩ፡፡ ኤልዛቤል ናቡቴ እንደሞተ ስትሰማ በጣም ተደስታ ለባሏ ለንጉሥ አክዓብ ናቡቴ ሞቷል ሒድና የወይኑን ቦታ ውረስ አለችው፡፡ አክዓብ የናቡቴን የወይን ቦታ ለመውረስ ተነሣ ወደ ወይኑ አታክልትም ወረደ፡፡ በዚህ ጊዜ እግዚአብሔር ነብዩ ኤልያስን መልእክት አስይዞ ወደ አክዓብ ላከው "ገድለህ ወረስከውን?" ይልሃል እግዚአብሔር ሲል ኤልያስ አክዓብን ጠየቀው፡፡ ደሃውን ናቡቴን በግፍ ያለፍትህ ስለገደለ እግዚአብሔር እንደሚቀጣው ሚስቱን ኤልዛቤልንም እግዚአብሔር እንደሚፈርድባትና እንደሚበቀላትም ነገረው፡፡ ንጉሥ አክዓብ በጣም አዝኖ ወደ ቤተመንግሥት ተመለሰ፡፡ ነቢዩ ኤልያስ የተናገረውን ለሚስቱ ኤልዛቤል ነገራት፡፡ እግዚአብሔር በቃሉ ታማኝ ስለሆነ አክዓብ በጦርነት ሞተ ውሾችም ደሙን ላሱት በሚስቱ ኤልዛቤልም ይህ ሆነባት፣ የናቡቴን ደም እንዳፈሰሱ የእነርሱም ደም ፈሰሰ፤ እግዚአብሔር ስለ ናቡቴ ተበቀላቸው፡፡

## ማጠቃለያ፡-

ልጆች በዚህ ትምህርት ንጉሥ አክዓብ የእርሱ ያልሆነውን የናቡቴን የወይን ቦታ በመመኘቱ የልቡ መሻት ስላልተፈጸመ ናቡቴን ገድሎ የወይኑን ርስት እንደወረሰ በዚህም እግዚአብሔር እንደተበቀለው ተምራችኋል፡፡ ስለዚህ እናንተ ባላችሁ ነገር በመደሰት የሌላችሁን ነገር እግዚአብሔር በጊዜው እንዲሰጣችሁ በጸሎት በመጠየቅ የሌሎችን ነገር ከመመኘት እንዲሁም በሌሎች ከመቅናት ራሳችሁን ጠብቁ፡፡

### *ጥያቄዎች፡-*

1. ንጉሥ አክዓብ ስንተኛ የእስራኤል ንጉሥ ነው?
2. ሚስቱ ማን ትባላለች?
3. ናቡቴን ያስገደለው ማን ነበር እንዴት ተገደለ?
4. ወደ ንጉሥ አክዓብ የተላከ የእግዚአብሔር ነቢይ ማን ይባላል?
5. ንጉሥ አክዓብን እና ሚስቱ ኤልዛቤልን እግዚአብሔር እንዴት ተበቀላቸው?
6. ናቡቴን እስኪሞት ድረስ በድንጋይ የወገሩት እነማን ነቡሩ?

www.zeorthodox.org

## ተግባር፡-

- መምህሩ ምኞች የኃጢአት ጽንስ እንደሆነ ለልጆች በምሳሌ ያስረዳቸው፡፡
- ብዙ ጊዜ ሰዎች ኢ-ፍትሐዊ የሆኑ ተግባሮችን የሚፈጽሙባቸውን ምክንያቶች ልጆች እንዲወያዩባቸው አድርግ፡፡

- ልጆች ፍላጎቶቻቸውን ሌሎችን በማይጎዳ መንገድ እንዴት ማሟላት እንደሚችሉ ተግባራዊ ምሳሌዎችን በማምጣት አሳያቸው፡፡
- ልጆች እንዴት ባላቸው ነገር መርካት እና መደሰት እንደሚችሉ አወያያቸው፡፡

www.zeorthodox.org

# ቅዱስ ቂርቆስ እና ቅድስት እየሉጣ

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ልጆች ከቂርቆስ እና እየሉጣ ሕይወት እስከ ሞት ድረስ ለእግዚአብሔር መታመንን እንዲማሩ መርዳት፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "እነዚህ ሁሉ አምነው ሞቱ፡፡" ዕብ.፲፩÷፲፫

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ዕብ. ፲፩÷፩-፵፣ መጽሐፈ ስንክሳር፣ ገድለ ቂርቆስ ወእየሉጣ፣ ራዕ. ፪÷፲፣ ዳን.፫÷፩-፴

## መግቢያ፡-

- መምህሩ ያለፈውን ሳምንት ትምህርት ይከልሰላቸው፡፡
- ልጆች የቅዱሳንን ታሪክ ማጥናት ለምን አስፈለገ?
- ልጆች ቅዱሳንን በኑሮአችሁ ለመምሰል ትሞክራላችሁ?
- የምታውቋቸውን የቅዱሳን ስሞች ለመምህራችሁ ንገሩ?

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

ከቤተ ክርስቲያን ታሪክ እንደምንረዳው ቤተ ክርስቲያን ብዙ የመከራ፣ የሥቃይ እና የስደት ዘመናትን አሳልፋ ነው አሁን ያለንበት ዘመን ላይ የደረሰችው፡፡ በተለይ በመጀመሪያዎቹ የቤተ ክርስቲያን ዘመናት ብዙ ክርስቲያኖች በክርስቶስ በማመናቸው ብቻ ብዙ መከራን የተቀበሉበት እና ዋጋ ከፍለው ቤተ ክርስቲያንን ያገለገሉበት ዘመን ነበር፡፡ የቅዱስ ቂርቆስና የቅድስት እየሉጣ ታሪክ ይህን ክርስቲያኖች ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ ነው ብለው በማመናቸው የከፈሉትን ዋጋ የምናስታውስበት እና በመከራ ሁሉ ታግሰው ክርስትናን እንዴት ለእኛ እንዳቆዩልን የምናይበት ነው፡፡ ክርስቲያኖች በማያምኑ ነገሥታት ብዙ መከራ በሚቀበሉበት ዘመን ቅዱስ ቂርቆስ ከእናቱ ከእየሉጣ ተወለደ፡፡

www.zeorthodox.org

አባቱ በሕፃንነቱ ስለሞተ እናቱ ታሳድገው ነበር፡፡ ከመከራው ብዛት የተነሣ ቅድስት እየሉጣ የሦስት ዓመት ልጇን ቂርቆስን ይዛ የትውልድ ቦታዋን ጥላ ከልጇ ጋር ተሰደደች፡፡ ነገር ግን ተሰዳ የሔደችበትም ሀገር ክርስቲያኖች የሚጠሉበት ስለነበር ክርስቲያን በመሆኗ አገረ ገዢው ጋር ተከሳ ቀረበች፣ አድካሚ ሥራ እና ጣዖትን እንድታመልክ እምነቷን እንድትለውጥ ተፈረደባት፡፡ ይህ ፍርድ የቅድስት እየሉጣን እምነት የሚፈታተን ስለነበር ከባዱን ሥራ እየሠራች ነገር ግን እምነቷን እንደማትቀይርና ለጣዖት እንደማትሰግድ እንቢታዋን ገለጸች፡፡ ይህን እንቢታዋን የሰማው አገረ ገዢ ክርስትናዋን ጥላ እምነቷን ቀይራ ለጣዖት የማትሰግድ ከሆነ ከነ ልጇ በእቶን እሳት እንደሚያቃጥላት ነገራት፡፡

የዚህ ጊዜ ቅድስት እየሉጣ የልጇ ነገር በጣም አሳስቧት ፈራች ሕፃኑ ቅዱስ ቂርቆስ ግን በእምነት መንፈሳዊ ጀግና ስለነበር

እናቱ ጀርባ ላይ ሆኖ አገረ ገዢውን "ያንተ አማልክት ከድንጋይና ከእንጨት የተሰሩ የሰው እጅ ሥራ ውጤቶች ናቸው፡፡ ከጌታዬ ከኢየሱስ በቀር ሌላ አምላክ የለም" አለው፡፡ እናቱንም የምናመልከው አምላክ ከእቶኑ እሳት ያወጣናል አይዞሽ አትፍሪ አላት፡፡ አገረ ገዢው ቅዱስ ቂርቆስ እና ቅድስት እየሉጣ በእምነታቸው እንደጸኑ ባየ ጊዜ ወደ እሳት ውስጥ ጣላቸው፡፡ ነገር ግን እግዚአብሔር መልአኩ ቅዱስ ገብርኤልን ልኮ አዳናቸው፡፡ ይህን ተአምር ያዩ ብዙ ሰዎች በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ አመኑ፡፡ በመጨረሻም ሕፃኑ ቅዱስ ቂርቆስ ቅድስት እየሉጣ የሰማዕትነት ዘውድ ተቀዳጅተው ሐምሌ 15 ቀን ዐረፉ፡፡ ጸሎትና በረከታቸው ከእኛ ጋር ትሁን አሜን፡፡

## ማጠቃለያ፡-

ልጆች በዚህ ታሪክ እስከ ሞት ድረስ ለክርስቶስ መታመንን በሕፃኑ ቅዱስ ቂርቆስና በእናቱ በቅድስት እየሉጣ ተምራችኋል፡፡ ስለዚህ እናንተም የእነርሱን ፈለግ በመከተል ለክርስቶስ እስከሞት ድረስ መታመንን እና በእምነት በመጽናት በመከራ መታገስን ተለማመዱ፡፡

### *ጥያቄዎች፡-*

1. የቅዱሳንን የሕይወት ታሪክ ማጥናት ለምን ይጠቅማል?
2. ለቂርቆስና ለእየሉጣ ስደት ምክንያቱ ምን ነበር?
3. የእናት እና ልጅ የእምነት ጽናት ከየትኛው የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ጋር ይመሳሰላል?
4. የቅዱስ ቂርቆስ እናት በአገረ ገዢው የታዘዘችው ትእዛዝ ምን ነበር?
5. ከእሳት ያዳናቸው መልአክ ማን ይባላል?

## ተግባር፡-

- መምህሩ ልጆች ከመጽሐፍ ቅዱስ ጥናታቸው ጋር የቅዱሳንን ታሪክ ማንበብ የሚሰጠውን ጠቀሜታ ይግለጽላቸው፡፡
- ልጆች እምነታቸውን ለጊዜያዊ ደስታ እና ምኞት መለወጥ እንደሌለባቸው እና በየትኛውም ሁናቴ ውስጥ እምነታቸውን መመስከር እንዳለባቸው አጽንኦት ሰጥተህ አወያያቸው፡፡

www.zeorthodox.org

# ነቢያት እና የተመረዘው ምግብ

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** እግዚአብሔር ልጆቹን እንደሚጠብቅ ከክፉ ነገርም እንደሚያድናቸው ማስተማር፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "የሚገድልም ቢጠጡ አይጎዳቸውም" ማር.፲፮÷፲፰፡፡

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ፪ነገ. ፬÷፴፰-፵፩፣ ማር. ፲፮÷፲፯-፲፰፡፡

## መግቢያ፡-

- መምህሩ ያለፈውን ሳምንት ትምህርት ይከልስላቸው፡፡
- መምህሩ ምግብ ሊመረዝ የሚችልባቸውን ምክንያቶች ለልጆች ይግለጽላቸው፡፡
- ልጆች የሚመገቡትን እንዴት እንደሚመርጡ እና የአመጋገብ ሥርዓታቸው ምን እንደሚመስል ጠይቃቸው

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

ልጆች ባለፈው ሳምንት የእግዚአብሔር ሰው ኤልሳዕ በጸሎት እና በምልጃ የሱነማዊቷን ልጅ እንዳስነሣ ተምራችሁ እንደነበር ታስታውሳላችሁ፡፡ ኤልሳዕ በሱነማዊቷ ልጅ መነሣት የእግዚአብሔር ኃይል በመገለጡ በጣም ተደስቶ ወደ ጌልጌላ መጣ፡፡ በጌልጌላ ዝናብ በወቅቱ ስላልዘነበ በምድሩ ላይ ረሃብ ነበረ፡፡ የነቢያትም ልጆች ወደ ኤልሳዕ መጥተው በፊቱ ተቀምጠው የእግዚአብሔር ቃል ይማሩ ነበር፡፡ ኤልሳዕ አገልጋዩን ግያዝን ለነቢያት ልጆች ምግብ እንዲያዘጋጅና ወጥ እንዲሰራ አዘዘው፡፡ ግያዝ ለወጥ የሚሆን ቅጠላ ቅጠል ያመጣ ዘንድ ወደ ሜዳ ወጣ፤ ነገር ግን ለብዙ ጊዜ ዝናብ ስላልነበረ መሬቱ በመድረቁ ምንም ዓይነት አታክልት በምድሩ ላይ አልነበረም፡፡ በዚህ የተነሣ የምድረ በዳውን ቅጠል እና ሐረግ እንዲሁም የበረሐ ቅጠል ሰብስቦ ልብሱን ሞልቶ ወደ ቤት ተመለሰ፡፡ ግያዝ ድስቱን ጥዶ ከምድረበዳ ሰብስቦ ያመጣውን ቅጠል እና የበረሐ ቅል ወጥ አድርጎ ሠራው፡፡ ነገር ግን ግያዝ ያዘጋጀው ምግብ የተመረዘ ነበር፡፡ የነቢያት ልጆች ምግቡን ሊመገቡ ቀረቡ ወጡንም በቀመሱ ጊዜ "የእግዚአብሔር ሰው ሆይ በምንቸቱ ውስጥ ሞት አለ" ብለው ጮሁ፡፡ ምግቡንም ይበሉ ዘንድ አልቻሉም ነበር፡፡ በዚህ ጊዜ የእግዚአብሔር ሰው ኤልሳዕ አገልጋዩ ፈጥኖ ዱቄት እንዲያመጣለት አዘዘው፡፡ ዱቄቱንም በድስቱ ውስጥ ጨምሮ ምግቡን እንደገና እንዲመገቡ አደረገ፣ ሁሉም ጥዑም ምግብ ተመገቡ፡፡ እግዚአብሔር መርዛማውን ምግብ በነቢዩ ኤልሳዕ ጸሎት ጣፋጭ ምግብ አድርጎ ስለቀየረላቸው እግዚአብሔርን በአንድነት አመሰገኑ፡፡

www.zeorthodox.org

## ማጠቃለያ፡-

ልጆች በዚህ ትምህርት ሁሉም ነገር እንደማይበላ እና ለምግብ አገልግሎት እንደማይውል አወቃችሁ አይደል? ግያዝ የሚበላ አታክልት ባለመምረጡ የነቢያት ልጆች በመርዛማው ምግብ ሊሞቱ ነበረ፡፡ ነገር ግን እግዚአብሔር ልጆቹ በመርዛማው ወጥ እንዳይሞቱ ከሞት አዳናቸው፡፡ ስለዚህ ልጆች የምትመገቡትን ምግብ መምረጥ አለባችሁ፡፡ የማታውቁትን ምግብ ለራሳችሁም ሆነ ለሌሎች አትመግቡ፡፡ በተለይ የታሸጉ ምግቦችን ስትጠቀሙ ጊዜው ያለፈበት መሆኑን ወይም አለመሆኑን ማረጋገጥ አለባችሁ፡፡ የቤተሰባችሁን ፈቃድ ሳታገኙም የታሸጉ ምግቦችን አትመገቡ፡፡

### ***ጥያቄዎች፡-***

1. የነቢዩ ኤልሳዕ እንግዶች እነማን ነበሩ?
2. ኤልሳዕ ግያዝን ምን እንዲያደርግ አዘዘው?
3. ግያዝ የሠራው ወጥ መርዘኛ የሆነው በምን ምክንያት ነው?
4. መርዛማው ምግብ እንዴት ተለወጠ?
5. ልጆች ከዚህ ትምህርት ምን ተማራችሁ?

## ተግባር፡-

- መምህሩ ለልጆች እግዚአብሔር ተአምር የሚያደርገው ለምን እንደሆነ ይግለጽላቸው፡፡ ተአምራት ሁል ጊዜ የእግዚአብሔር ክብር የሚታይባቸው መሆን አለባቸው፡፡ ማንኛውም ተአምር የእግዚአብሔርን ስም የሚያከብር እና ሰዎችን የማይጠቅም ከሆነ እውነተኛ ተአምር አይደለም፡፡
- ልጆች ከምግብ በፊት እና በኋላ እግዚአብሔርን በጸሎት እንዲያመሰግኑ አድርጋቸው፡፡

www.zeorthodox.org

# የኤማሁስ መንገደኞች

**የትምህርቱ ዓላማ፦** ልጆች ከኤማሁስ መንገደኞች የእግዚአብሔርን ቃል መነጋገርን የዕለት ተዕለት ተግባራቸው እንዲያደርጉ ማስተማር ነው፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፦** "መጻሕፍትን ያስተውሉ ዘንድ አእምሮአቸውን ከፈተላቸው" ሉቃ. ፳፬÷፵፭፡፡

**ተጨማሪ ምንባባት፦** ሉቃ. ፳፬÷፲፫-፶፫፣ ኢሳ.፶፫÷፩-፲፣ መዝ.፳፩÷፩-፲፰

## መግቢያ፦

- መምህሩ ያለፈውን ሳምንት ትምህርት ይከልሱላቸው፡፡
- ልጆች የትንሣኤን በዓል እንዴት አከበራችሁ?
- ከቤተሰባችሁ እና ከጓደኞቻችሁ ጋር የእግዚአብሔርን ቃል የመማማር ልምድ አላችሁ? ልምዳችሁን ለመምህራችሁ እና ለክፍሉ ተማሪዎች ንገሩ፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት፦

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው ሆኖ በዚህ ምድር በቃሉ ትምህርት በእጁ ተአምራትን እያደረገ የእግዚአብሔርን መንግሥት ወንጌል ከሰበከ በኋላ ጊዜው ሲደርስ በመስቀል ተሰቅሎ ሞተ፡፡ አስቀድሞ እንደተናገረው በሶስተኛው ቀን ሞትን ድል አድርጎ ተነሣ፡፡ በመጀመሪያ ሽቱ ይዘው ማልደው ወደ መቃብሩ የመጡ ሴቶች የመቃብሩ ድንጋይ ተንከባሎ ባዶ መቃብር ተመለከቱ፡፡ መላእክት ክርስቶስ እንደተነሣ ትንሣኤውን ለሌሎች እንዲያበስሩ በነገሯቸው መሠረት ተመልሰው ትንሣኤውን ለዐሥራ አንዱ ሐዋርያት እና ለሌሎችም ተናገሩ፡፡ ነገር ግን ብዙዎቹ የሴቶቹ ምስክርነት ቅዠት ስለመሰላቸው አላመኗቸውም ነበር፡፡ ጴጥሮስ ግን ተነሥቶ ወደ መቃብሩ ሮጠ፣ ወደ መቃብር ውስጥ ዝቅ ብሎ ሲመለከት ክርስቶስ የተገነዘበትን ልብስ ብቻ ተመለከተ፣ በዚህ እየተደነቀ ተመለሰ፡፡ ምንም እንኳን ኢየሱስ ክክርስቶስ ስለ ሰው ልጆች ኃጢአት በመስቀል ተሰቅሎ እንደሚሞት በሦስተኛውም ቀን እንደሚነሣ በቅዱሳት መጻሕፍት የተጻፈ ቢሆንም በጊዜው ይህን ማመን እና መቀበል የከበዳቸው ብዙዎች ነበሩ፡፡ ከእነዚህ ሰዎች መካከል የኤማሁስ መንገደኞች ናቸው፡፡

www.zoorthodox.org

የኤማሁስ መንገደኞች ክርስቶስ ሞትን ድል አድርጎ በተነሣበት ቀን ከኢየሩሳሌም ወደ ኤማሁስ መንደር ይጓዙ ነበር፡፡ የጉዞአቸው ወሬ ኢየሱስ ክርስቶስ ነበር፡፡ ስለ ክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ ሲነጋገሩና ሲመራመሩ ራሱ ኢየሱስ ቀርቦ ከእነርሱ ጋር ይሔድ ነበር፡፡ እነርሱ ግን ዓይናቸው ተይዞ ስለነበር ማን እንደሆነ አላወቁትም፡፡ ጌታም ምንም እንደማያውቅ ሰው ሆኖ ስለምን እንደሚነጋገሩ በትሕትና ጠየቃቸው የኤማሁስ መንገደኞች የሆነውን ሁሉ ነገሩት፡፡ እርሱም ካደመጣቸው በኋላ አለማስተዋላቸውን

እና አለማመናቸውን ነቅፎ ከሙሴና ከነቢያት ሁሉ ጀምሮ ስለ እርሱ በመጻሕፍት ሁሉ የተጻፈውን ተረጎመላቸው፡፡ ወደ ኤማሁስ መንደር ሲቀርቡ ሩቅ የሚሔድ ስለመሰላቸው ከእነርሱ ጋር እንዲያድር ለመኑት፡፡ ጌታም ከእነርሱ ጋር ሊያድር ገባ ከእነርሱም ጋር በማዕድ ተቀምጦ ሳለ እንጀራውን አንሥቶ ባረከው፣ ቆርሶም ሰጣቸው ዓይናቸውም ተከፈተ ማን እንደሆነ አወቁት ጌታም ከእነርሱ ተሰወረ፡፡ የኤማሁስ መንገደኞች በመንገድ ሲያስተምራቸው እና መጻሕፍትን ሲተረጉምላቸው የመጣው ጌታ ኢየሱስ መሆኑን አውቀው በዚያው ሰዓት ተነሥተው ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሱ፡፡ የክርስቶስን ትንሣኤ ለዐሥራ አንዱ ሐዋርያት እና ከእነርሱ ጋር ለነበሩት መሰከሩ፡፡

## ማጠቃለያ፡-

ልጆች በዚህ ትምህርት ጌታ ኢየሱስ ሞትን ድል አድርጎ እንደተነሣ ነገር ግን ብዙዎች የክርስቶስን ትንሣኤ በእምነት መቀበል እንደተሳናቸው በተለይ ለኤማሁስ መንገደኞች ራሱ ጌታ ኢየሱስ ተገልጦ መጻሕፍትን እንዲያስተውሉ እና በእርሱ እንዲያምኑ እንደረዳቸው ተገንዝባችኋል፡፡ የኤማሁስ መንገደኞች የመጻሕፍትን ምስጢር ካስተዋሉ እና በትንሣኤው ካመኑ በኋላ የክርስቶስ ምስክር እንደሆኑ እናንተም የክርስቶስ ትንሣኤ ምስክሮች ሁኑ፡፡

### *ጥያቄዎች፡-*

1. የክርስቶስን ትንሣኤ በመጀመሪያ ለማየት የቻሉ እነማን ነበሩ?
2. ክርስቶስ የተገነዘበትን ልብስ በመቃብር ውስጥ የተመለከተ ሐዋርያ ማን ይባላል?
3. የኤማሁስ መንገደኞች ወሬያቸው ማን ነበር?
4. አብሮአቸው ይሔድ የነበረው ማን ነበር?
5. የኤማሁስ መንገደኞች መጻሕፍትን የተረጎመላቸው ክርስቶስ መሆኑን መቼ ተረዱ? ስለ ምን እንደገና ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሱ?

## ተግባር፡-

- መምህሩ ለልጆች የማስተዋልን ጥቅም ያብራራላቸው፡፡
- ልጆች የእግዚአብሔርን ቃል ከጓደኞቻቸው ጋር የመማማር ልምድ የሚያዳብሩባቸውን የተለያዩ ስልቶችን ንገራቸው፡፡
- መጽሐፍ ቅዱስ ትርጓሜ እንደሚያስፈልገው ትክክለኛ ምስጢሩን እና ፍቺውን አለማወቅ ወደ ስህተት እንደሚያመራ ግለጽላቸው፡፡

www.zeorthodox.org

# ጻድቁ አቡነ ተክለሃይማኖት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ልጆች ከአባታቸው ከጻድቁ ተክለሃይማኖት ሕይወት የሃይማኖትን ፍሬ እንዲመለከቱ እና በእምነት እርሱን እንዲመስሉ ማስገንዘብ ነው፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "ጻድቅንም በጻድቅ ስም የሚቀበል የጻድቁን ዋጋ ይወስዳል፡፡" ማቴ.፲÷፵፩

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ማቴ. ፲÷፵-፵፪፣ መጽሐፈ ስንክሳር፣ ገድለ ተክለሃይማኖት፡፡

## መግቢያ፡-

- መምህሩ ያለፈውን ሳምንት ትምህርት ይከልስላቸው፡፡
- ልጆች ስለ ጻዳቁ አቡነ ተክለሃይማኖት የምታውቁትን ለመምህራችሁ ንገሩ፡፡
- አንድ ሰው ጻዳቅ የሚሆነው እንዴት ነው?
- ቤተ ክርስቲያን ጻድቃንን የምታከብረው ለምንድነው?

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

በመጽሐፍ ቅዱስ "ጻድቅ" የሚለው ቃል ሕግን መፈጸም፣ እንደ ሕግ መኖርና መመራት፣ ትክክለኛነትን እና እውነተኛነትን ያመለክታል፡፡ "ጻድቅ" የሚለውም ቃል በሕግ የጸና፣ እንደ ሕግ የሚኖር እውነተኛ ሰውን የሚወክል ቃል ነው፡፡ ሰዎች አካሄዳቸውን በእግዚአብሔር ፊት ሲያደርጉና እንደ እግዚአብሔር ሕግ ሲኖሩ ጻድቃን ይባላሉ፡፡ ጻድቁ አቡነ ተክለሃይማኖትም በእግዚአብሔር ፊት እንደ እግዚአብሔር ሕግ የኖሩ ኢትዮጵያዊ ጻድቅ ናቸው፡፡ ጻድቁ ተክለሃይማኖት እግዚአብሔርን ከሚወዱ እና ከሚያከብሩ ከአባታቸው ጸጋዘአብ እና ከእናታቸው እግዚእ ሐረያ ታኅሣሥ 24 ቀን ተወለዱ፡፡ ጸጋዘአብ ማለት የአብ ጸጋ ማለት ሲሆን እግዚእ ሐረያ ማለት ደግሞ በጌታ የተመረጠች ማለት ነው፡፡ ጸጋ ዘአብ እና እግዚእ ሐረያ እግዚአብሔርን በፍጹም ልባቸው የሚያምኑ፣ በተለያየ ሕመም የሚሰቃዩ እና ችግረኞችን የሚረዱ ደጋግ ሰዎች ነበሩ፡፡

www.zeorthodox.org

በተለይ ለእግዚአብሔር መልአክ ለቅዱስ ሚካኤል የተለየ ፍቅር ስለነበራቸው በየወሩ በቅዱስ ሚካኤል አማላጅነት በመታመን የመልአኩን በዓል ድሆችን በመንከባከብ ያከብሩ ነበር፡፡ ከዕለታት አንድ ቀን ቅዱስ ሚካኤል በሕልም ተገልጾ እግዚአብሔር የተባረከ ልጅ እንደሚሰጣቸው ነገራቸው፡፡ እግዚአብሔር የሰጣቸውን ወንድ ልጅ ፍሥሐጽዮን ብለው ጠሩት፡፡ ፍሥሐጽዮን ማለት የጽዮን ደስታ ማለት ነው፡፡ ሕፃኑ ፍሥሐጽዮን መንፈስ ቅዱስን ተሞልቶ በሶስተኛው ቀን አሐዱ አብ ቅዱስ አሐዱ ወልድ ቅዱስ አሐድ ውእቱ መንፈስ ቅዱስ ብሎ አመሰገነ፡፡ እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ስለነበር ፍሥሐጽዮን በልጅነቱ ብዙ ተአምራትን አድርጓል፡፡ በአንድ ወቅት ረሃብ ነበር ቤተሰቦቹ በዚህ ምክንያት የቅዱስ ሚካኤልን ዝክር እንዳያቋርጡ ጻድቁ አቡነ ተክለሃይማኖት ዱቄትና

ዘይት በማብዛት ቤተሰቦቹ ዝክሩን ያለምንም ችጋር እንዲዘክሩ አድርጓል፡፡

ዝክር ማለት በእግዚአብሔር፣ በቅዱሳን እና በመላእክት ስም የሚደረግ መታሰቢያ ነው፡፡ ፍሥሐጽዮን እግዚአብሔርን እያገለገለ አደገ፡፡ በዐሥራ አምስት ዓመቱ ከአቡነ ቄርሎስ ሁለተኛ ዲቁና ተቀበለ፡፡ ወደ ቤት ሲመለስ ቤተሰቦቹ አንዲት ሴት እንዲያገባት እንዳጩለት ነገሩት፡፡ ነገር ግን ፍሥሐጽዮን ይህን ጥያቄ አልተቀበለውም ነበር፡፡ አንድ ቀን ፍሥሐጽዮን ከጓደኞቹ ጋር ለአደን እንደወጣ መልአኩ ቅዱስ ሚካኤል ተገልጦ ከዚህ በኋላ ያለውን ቀሪ ዘመኑን የሰዎችን ነፍስ በማዳን እግዚአብሔርን እንዲያገለግል መመረጡን ነገረው፡፡ መልአኩ የፍስሐጽዮንን ስም ተክለሃይማኖት (የሃይማኖት ዛፍ (ተክል)) ብሎ ለወጠው፡፡ ከዚህ በኋላ ተክለሃይማኖት ወደቤቱ ተመልሶ ገንዘቡን ለቤተ ክርስቲያን እና ለድሆች ሰጥቶ ወደ ገዳም ሄደ፡፡

በገዳም እያገለገለ እና እየተማረ የቅድስና ማዕርግን ተቀበለ፡፡ በትጋት ወንጌልን በመስበኩ ብዙ ሰዎችን ወደ ክርስትና ተመለሱ፡፡ በደብረ ዳሞ ገዳም ለብዙ ዓመታት በአገልግሎት ከቆየ በኋላ አንድ ቀን በገመድ ሲወርድ ገመድ ተበጥሶ ሲጸልይ ክንፍ ተሰጠው፡፡ ጻድቁ አቡነ ተክለሃይማኖት ሃያ ዘጠኝ ዓመታትን ያሳለፈው ደብረ አሰቦ በተባለ ቦታ ቆሞ በመጸለይ ነበር፡፡ ለረጅም ሰዓታት በመቆም ይጸልይ ስለነበረ እግሩ ሊቆረጥ ችሏል፡፡ አንድ እገሩ ቢቆረጥም ጸሎቱን እና ትጋቱን አላቋረጠም ነበር፡፡ በአንድ እግሩ ለሰባት አመታት ጸልዮአል፡፡ ጻድቁ ተክለሃይማኖት ዘመኑን ወንጌልን ለማያምኑ ሰዎች በመስበክ ብዙ ኢ-አማንያንን ክርስትናን እንዲቀበሉ አድርጓል፡፡ የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት እንዲሰፋ እና ገዳማዊ ሕይወት እንዲጠነክር ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደረገ ሲሆን በዘጠና ዘጠኝ ዓመቱ ነሐሴ ሃያ አራት ቀን በክብር አርፏል፡፡ ጸሎቱ ቃል ኪዳኑ እና በረከቱ ከሁላችን ጋር ይሁን፡፡

## ማጠቃለያ፡-

ልጆች ቤተ ክርስቲያን መሠረቷ ክርስቶስ ስለሆነ ስለ ወንጌል ብዙ ዋጋ የከፈሉትን ሁሉ ታከብራለች መልካሙን ገድላቸውን ታስታውሳለች፡፡ እግዚአብሔር ያከበራቸውን ታከብራለች፡፡ ጻድቃን የታመኑት በእግዚአብሔር ነው፣ ያገለገሉት ክርስቶስን ነው፡፡ ጻድቃንን መቀበል ማለት እምነታቸውን መቀበል የኑሮአቸውን እና የአገልግሎታቸውን ፍሬ እየተመለከትን በእምነት እነርሱን መምሰል እንዲሁም እነርሱ የኖሩትን ሕይወት በየዕለት ተዕለት ኑሮአችን መኖር ነው፡፡ ስለዚህ ልጆች እንደ ጻድቁ ተክለሃይማኖት በእግዚአብሔር ፊት በሕግ እና በሥርዓት እርሱ ደስ የሚሰኝበትን ኑሮ መኖርን ተለማመዱ፡፡ ጻድቃን ያመለኩትን አምላክ ካመለካችሁ እና የእነርሱን ሕይወት ከኖራችሁ በእነርሱ በረከት ትባረካላችሁ፡፡

www.zeorthodox.org

### ጥያቄዎች፡-

1. ልጆች ጻድቅ ማለት ምን ማለት ነው?
2. የአቡነ ተክለሃይማኖት ቤተሰቦች ማን ይባላሉ?
3. ተክለሃይማኖት የሚለውን ስም ያወጣላቸው ማን ነው?
4. ዝክር ማለት ምን ማለት ነው? ለምንስ አሰፈለገ?
5. አቡነ ተክለሃይማኖት በስንት ዓመታቸው እና መቼ ዐረፉ?

## ተግባር፡-

- መምህሩ ልጆች በዚህ ዘመን እንዴት የጻድቃንን ፈለግ መከተል እንደሚችሉ ያወያያቸው፡፡
- ልጆች ቤተሰቦቻችሁ የሚያከብሩትን በዓል እንዲሁም ዝክር ለጓደኞቻችሁ ንገሯቸው፡፡
- የቅዱሳን መታሰቢያ ቀናት ሌሎችን መርዳትን ስለሚያስታውሱን እና በጎ ነገሮችን እንድንሠራ ስለሚያደርጉን ቤተ ክርስቲያን ለጻድቃን፣ ለሰማዕታት፣ ለቅዱሳን . . . ወዘተ መታሰቢያ ቀናትን አሰናድታለች፡፡ ስለዚህ ልጆች ቅዱሳን የሚታሰቡባቸውን ቀናት እንዲያውቁ አድርጋቸው፡፡

www.zeorthodox.org

# ነቢዩ ኤልሳዕ መራራውን ውኃ አጣፈጠ

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ለልጆች እግዚአብሔር በቅዱሳኑ አድሮ ብዙ ተአምራት እንደሚያደርግ ማስተማር ነው፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "የጻድቅ ሰው ጸሎት በሥራዋ እጅግ ኃይል ታደርጋለች፡፡" ያዕ. ፭÷፲፮

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ፪ነገ. ፪÷፲፱-፳፪፣ ማቴ. ፯÷፯-፱፣ ዮሐ.፲፬÷፲፪-፲፬

## መግቢያ፡-

- መምህሩ ያለፈውን ሳምንት ትምህርት ይከልስላቸው፡፡
- ልጆች ነቢዩ ኤልያስን ታውቁታላችሁ? ስለ እርሱ የምታውቁት ምንድ ነው?
- የኤልያስ ደቀመዝሙር ማን ነበር?
- ተአምር ምንድ ነው? ቅዱሳን ተአምራት የሚያደርጉት በማን ኃይል ነው?

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

ልጆች ከዚህ ቀደም ስለ ነቢዩ ኤልያስ እንደተማራችሁ ታስታውሳላችሁ፡፡ ዛሬ ደግሞ የነቢዩ ኤልያስ ተማሪ እና አገልጋይ ሰለነበረው ሰለ ነቢዩ ኤልሳዕ እንማራለን፡፡ ኤልሳዕ የስሙ ትርጒም "እግዚአብሔር ደኅንነት ነው" ማለት ነው፡፡ ነቢዩ ኤልያስ ከእግዚአብሔር በተገለጠለት መሠረት ኤልሳዕን ለአገልግሎት ጠራው፡፡ ኤልሳዕ የእግዚአብሔር ጥሪ በኤልያስ በኩል እንደመጣለት ሥራውን ትቶ ነቢዩ ኤልያስን እየተከተለ ያገለግለው ነበር፡፡ (፩ነገ. ፲፯-፳፩፤ ፪ ነገ.፫÷፲፩)

www.zeorthodox.org

ነቢዩ ኤልያስ በእሳት ሰረገላ ወደ ሰማይ በተወሰደ ጊዜ ኤልሳዕ ስላየው የኤልያስ መንፈስ እጥፍ ድርብ ሆኖ አድሮበት ለረጅም ጊዜ እግዚአብሔርን አገለገለ፣ ብዙ ተአምራትንም አደረገ፡፡ ከዕለታት አንድ ቀን በኢያሪኮ ከተማ የሚኖሩ ሰዎች ነቢዩ ኤልሳዕ ወደ እነርሱ እንደመጣ ባዩ ጊዜ "የዚች ከተማ ኑሮ መልካም ነው ውኃው ግን ክፉ ነው ምድሪቱም ፍሬዋን ትጨነግፋለች" አሉት፡፡ የኢያሪኮ ከተማ ሰዎች ይህን ልመና ለኤልሳዕ ያቀረቡት እግዚአብሔር በቅዱሳኑ ነገርን ሁሉ መለወጥ እንደሚችል ይታመኑ ስለነበር ነው፡፡ ነቢዩ ኤልሳዕ የሰዎቹን ችግር ከተረዳ በኋላ የከተማውን ሰዎች አዲስ ማሰሮ እና ጨው እንዲያመጡለት አዘዘ፡፡ ሰዎቹም ኤልሳዕ እንዳዘዛቸው አደረጉ፡፡ አዲስ ማሰሮ በውስጡ ጨው አድርገው አመጡለት፤ ነቢዩ ኤልሳዕ ወደ ውሃው ምንጭ ወደ አለበት ስፍራ መጥቶ ጨው ጣለበት እና "እግዚብሔር እንዲህ ይላል ይህን ውኃ ፈውሼዋለሁ ከዚህም በኋላ ሞትና ጭንገፉ አይሆንበትም" ብሎ ለከተማው ሰዎች ተናገረ፡፡ ኤልሳዕም እንደ ተናገረው ውኃው እስከ ዛሬ ድረስ ተፈውሶአል፡፡ የኢያሪኮ ከተማ ሰዎች ከዛ ጊዜ

ጀምሮ ንጹሕ ውሃ መጠጣት ጀመሩ፡፡ የምድሪቱንም ፍሬ ተመገቡ፡፡ እግዚአብሔር በነቢዩ ኤልሳዕ ድንቅ ነገር ስለአደረገላቸው ዘወትር ያመሰግኑ ነበር፡፡

## ማጠቃለያ፡-

ልጆች ከዚህ ትምህርት እግዚአብሔር በነቢዩ ኤልሳዕ አማካኝነት እንዴት መራራውን ውሃ እንዳጣፈጠ እና የኢያሪኮ ከተማ ሰዎችን ታሪክ እንደቀየረ አስተውላችኋል፡፡ ሐዋርያው ያዕቆብ የጻድቅ ሰው ጸሎት ኃይልን ታደርጋለች ያለው ይህን ነው፡፡ ስለዚህ እናንተም እንደ ኢያሪኮ ሰዎች የእግዚአብሔርን ነቢያት አክብሩ፡፡ በጸሎታቸው እና በምልጃቸው እንዲሁም እግዚአብሔር በእነርሱ እንደሚሠራ ታመኑ፡፡

### *ጥያቄዎች፡-*

1. ኤልሳዕ ማለት የስም ትርጉም ምንድነው?
2. ኤልሳዕን ለአገልግሎት የመረጠው ማን ነበር? እንዴት?
3. ኤልሳዕ አገልግሎት የጀመረው መቼ ነው?
4. የኢያሪኮ ሰዎች ወደ ኤልሳዕ የመጡት ለምን ነበር?
5. ኤልሳዕ መራራውን ውኃ ለማጣፈጥ ምን አደረገ?
6. ኤልሳዕ የአማላጅነትን ሥራ የሠራው እንዴት ነው?

## ተግባር፡-

- መምህሩ የኢያሪኮ ከተማ እና የዮርዳኖስ ወንዝ የት እንደሚገኙ ለልጆች ካርታውን ያሳያቸው፡፡
- ልጆች የንጹሕ ውኃን ጥቅም እና እንዴት ከብክለት ሊጠብቁ እንደሚችሉ ግንዛቤ በማስጨበጥ እንዲወያዩ አድርጋቸው፡፡
- ልጆች ለምንድነው ኤልሳዕ አዲስ ማሰሮ እና ጨው እንዲያመጡለት የኢያሪኮ ሰዎችን ያዘዛቸው? ማሰሮው የምን ምሳሌ ነው? ጨውስ? መምህሩ ምሳሌውን ያብራራላቸው፡፡
- ጌታ ኢየሱስ “እናንተ የዓለም ጨው ናችሁ” ሲል ምን ማለቱ ነው?

www.zeorthodox.org

# ታላቋ ሴት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ለልጆች በእግዚአብሔር ፊት ትልቅ የሚሆኑበትን ምስጢር መንገር፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** “ሰው እንዲያይ እግዚአብሔር አያይም፡፡” ፩ሳሙ. ፲፮÷፯

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ፪ነገ. ፬÷፰-፴፯፣ ዮሐ. ፲፩÷፳፭

## መግቢያ፡-

- መምህሩ ያለፈውን ሳምንተ ትምህርት ይከልስላቸው፡፡
- ልጆች ሰውን ትልቅ የሚያደርገው ነገር ምንድነው?
- ሰዎችን የምትመዝኑበት ሚዛን ምንድነው?

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

ልጆች ባለፈው ሳምንት እግዚአብሔር በነቢዩ ኤልሳዕ ጸሎትና አማላጅነት በኢያሪኮ የነበረውን መራራ ውሃ እንዳጣፈጠ ተምራችኋል፡፡ ዛሬ ደግሞ በሱነም ከተማ ትኖር ለነበረች አንዲት ታላቅ ሴት ያደረገውን ተአምር እንማራለን፡፡ ሱነም ነቢዩ አልሳዕ ካገለገለባቸው ከተሞች አንዷ ናት፡፡ በእነሱም እግዚአብሔርን የምታምን እና የምትፈራ እጅግ መልካም የሆነች አንዲት ሴት ነበረች፡፡ ባሏም ሰፊ መሬት የነበረው ገበሬ ሲሆን ብዙ አገልጋዮችም ነበሩት፡፡ ኤልሳዕ ወደ ሱነም በሚመጣ ጊዜ ይህች ታላቅ ሴት ወደቤቷ እንዲገባ እና እንጀራ እንዲበላ እንዲሁም እንዲባርካት ትጋብዘው ነበር፡፡ ነቢዩ ኤልሳዕ ታላቋ ሴት እጅግ መልካም እና ትሑት ሴት ስለነበረች ግብዣዋን እየተቀበለ ወደ ቤቷ ይገባ ነበር፡፡ የእግዚአብሔር አገልጋይ ነቢዩ ኤልሳዕ የተለያዩ ከተሞችን እና በውስጣቸው የሚኖሩትን ሰዎች ደጋግሞ የመጎብኘት ልማድ ነበረው፡፡

www.zeorthodox.org

ሕሙማንን፣ ሐዘንተኞችን እና በልዩ ልዩ ችጋር ውስጥ ያሉ ሰዎችን ይጠይቃቸውና ይጸልይላቸውም ነበር፡፡ ነገር ግን የሚያድርበት ስፍራ አልነበረውም፡፡ የእግዚአብሔርን ቃል እየሰበከና ተአምራትን እያደረገ ይኖር የነበረው በቀርሜሎስ ተራራ ላይ ነበር፡፡ አንድ ቀን ታላቋ ሴት ባሏን ለእግዚአብሔር ሰው ኤልሳዕ ማረፊያ እንዲሠራለት ጠየቀችው፡፡ ባሏም ለኤልሳዕ ወደ ሱነም ሲመጣ የሚያርፍበት ቤት ሠራለት በውስጡም አልጋ፣ ጠረጴዛ፣ ወንበርና መቅረዝ (መብራት) አኖሩለት፡፡ አንድ ቀንም ኤልሳዕ ወደ ሱነም መጣ ወደተዘጋጀለት ቤት ገብቶ ዐረፈ፡፡ ነቢዩ ኤልሳዕ ወደ ሱነም በመጣ ጊዜ በዚህ ቤት ውስጥ ያርፍ ነበር፡፡ በሱነማዊቷ ሴት መልካምነት ነቢዩ አልሳዕ እጅግ በጣም ስለተደሰተ አገልጋዩን ግያዝን እንዲጠራት አዘዘው፡፡ ሱነማዊቷ ሴት መጥታ በፊቱ ቆመች፤ ነቢዩ ኤልሳዕ ሰለአደረገችለት በጎ ነገር ሁሉ ካመሰገናት እና ከባረካት በኋላ ምን እንዲያደርግላት እንደምትፈልግ ጠየቃት፡፡ እርሷ ግን

ባላት ነገር ደስተኛ ሰለነበረች ምንም የምትፈልገው ነገር እንደሌለ መለሰች፡፡ ነገር ግን ግያዝ ልጅ እንደሌላት ያውቅ ሰለነበረ ልጅ እንዲሰጣት ለነቢዩ አልሳዕ ነገረው፡፡ ኤልሳዕ ሱነማዊቷን እንደገና ጠርቶ “በሚመጣው ዓመት በዚህ ወራት ወንድ ልጅ ትታቀፊያለሽ” አላት፡፡ ኤልሳዕ እንዳላት ሴቲቱን እግዚአብሔር አሰባት፣ ፀነሰችም ወንድ ልጅም ወለደች፡፡ ሕፃኑም አደገ አንድ ቀንም እህል አጫጆች ወደ አሉበት ወደ አባቱ እርሻ መጣ፡፡ በዚያም ታሞ ራሴን! ራሴን! እያለ ወደ አባቱ መጣ፡፡ አባቱም አንዱን አገልጋይ ተሸክሞ ወደ እናቱ እንዲወስደው አዘዘው፡፡ እናቱ በጉልበቷ ላይ አስተኝታው ስትንከባከበው ጉልበቷ ላይ ሞተ፡፡ ወዲያው የሞተውን ልጇን የእግዚአብሔር ሰው አልጋ ላይ አስተኝታ በሩን ዘግታ ወጣች፡፡ ባልዋንም ጠርታ፡- ወደ እግዚአብሔር ሰው በፍጥነት ደርሼ እመለሰ ዘንድ አንድ አህያ እና አንድ ሎሌ ላከልኝ አለችው፡፡ ፈጥናም ወደ እግዚአብሔር ሰው ወደ ኤልሳዕ ወደ ቀርሜሎስ ተራራ መጣች፡፡

ኤልሳዕ ከሩቅ ስላያት ደህና እንደሆነች እንዲጠይቃት አገልጋዩን ግያዝን ላከው፡፡ ግያዝ “አንቺ ደህና ነሽን?” “ባልሽ ደህና ነውን?” “ልጅሽስ ደህና ነውን?” ብሎ ጠየቃት፡፡ እርሷም አዎ ሁሉ ዳህና ነው አለች፡፡ ወደ ተራራው ወደ እግዚአብሔር ሰው በመጣች ጊዜ እግሮቹን ይዛ ማልቀስ ጀመረች፣ ልጇ እንደሞተ ተናገረች፡፡ የእግዚአብሔር ሰው ኤልሳዕ ግያዝ በትሩን ይዞ እንዲሔድና በሕፃኑ ፊት ላይ እንዲያኖር አዘዘው፡፡ ነገር ግን የሕፃኑ እናት ነቢዩ ኤልሳዕን አልተውህም አንተን ትቼ አልሔድም ብላ ግድ ስላለችው ተነሥቶ ተከተላት፡፡ ግያዝ ኤልሳዕ እንዳዘዘው አድርጎ ነገር ግን ሕፃኑ ስላልነቃ ወደ ኤልሳዕ ተመልሶ የሆነውን ነገረው፡፡ ኤልሳዕ ወደ ሱነማዊቷ ቤት ሲገባ ሕፃኑ ሞቶ በአልጋው ላይ ተጋድሞ ነበር፡፡ ኤልሳዕ በሩን ዘግቶ እግዚአብሔር የሕፃኑን ነፍስ እንዲመልስ ከሞተም እንዲያስነሳው በጸሎት አጥብቆ ለመነ፡፡ በነቢዩ ኤልሳዕ ጸሎት እና ምልጃ እግዚአብሔር የሱነማዊቷን ልጅ ከሞት አስነሣ፡፡ ኤልሳዕ ግያዝን ጠርቶ የሕፃኑ እናት መጥታ ልጇን እንድትወስድ ነገረው፡፡ ሱነማዊቷ ሴት መጥታ ልጇን ታቀፈች፣ እግዚአብሔር ልጇን ከሞት ሰለአነሣላት አመሰገነች፡፡ ነቢዩ አልሳዕ እግር ሥር ወድቃ የነቢያትን አምላክ እግዚአብሔርን አከበረች፡፡

## ማጠቃለያ፡-

www.zoorthodox.org

ልጆች ሱነማዊቷን ሴት መጽሐፍ ቅዱስ ታላቅ ሴት ያላት በእግዚአብሔር ፊት ታላቅ ስለነበረች ነው፡፡ ባላት ነገር መርካትና መደሰት መቻሏ፣ በትዳሯ ታማኝ ሴት መሆኗ እና የእግዚአብሔርን ሰው ማክበሯ በተለይ በእግዚአብሔር ላይ የነበራት ፍጹም እምነት በእግዚአብሔር ፊት ታላቅ አድርጓታል፡፡ ሰውን በእግዚአብሔር ፊት ትልቅ የሚያደርገው ትምህርት፣ ገንዘብ ፣ ሥልጣን መልክ ወይም ውበት ሳይሆን እምነትና ምግባር ነው፡፡ ስለዚህ ልጆች እናንተም እንደ ታላቋ ሴት በፍጹም ልባችሁ በእግዚአብሔር በመታመን በጎ ነገርን ለማድረግ ትጉ፤ የእግዚአብሔር ሰዎችን ለይታችሁ በማወቅ አክብሯቸው እግዚአብሔር በሰጣችሁ ነገር ሁሉ ተደሰቱ፡፡

***ጥያቄዎች፡-***

1. ታላቋን ሴት ማን ነው ታላቅ ያደረጋት?
2. ሱነማዊቷ ሴት ለኤልሳዕ ምን አደረገችለት?
3. የነቢዩ ኤልሳዕ አገልጋይ ማን ይባላል?
4. ታላቋ ሴት ልጇ ሲሞት ምን አደረገች?
5. የሱነማዊቷን ልጅ ያስነሳው ማን ነው?

## ተግባር፡-

- መምህሩ ልጆች ከሱነማዊቷ ሴት ምን እንደተማሩ ውይይት እንዲያደርጉ ያግዛቸው፡፡
- ልጆች ለታመመ ሰው መጸለይ እንዲለማመዱ አድርጋቸው፡፡

www.zeorthodox.org

# ጌታ ኢየሱስ እና ዘኬዎስ

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ጌታ ኢየሱስ ለኃጢአተኞች ያለውን ፍቅር ማሳየት፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** “ዛሬ ለዚህ ቤት መዳን ሆኖለታል፡፡” ሉቃ. ፲፱÷፲

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ሉቃ.፲፱÷፩-፲፤ ፫÷፲፪-፲፫፤ ፲፭÷፩-፴፪፤ ማቴ. ፱÷፱፡፡

## መግቢያ፡-

- መምህሩ ያለፈውን ሳምንት ትምህርት ይከልስላቸው፡፡
- ልጆች ቀራጭ ማለት ምን ማለት ነው?
- ቀራጮች ኃጢአተኛ የሆኑበት ምክንያት ምንድነው?
- ቀራጮች በሕዝቡ ይጠሉ የነበረው ለምን ይመስላችኋል?

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

ከዕለታት አንድ ቀን ጌታ ኢየሱስ ከደቀመዛሙርቱ ጋር ብዙ ሕዝብ እየተከተለው በኢያሪኮ ከተማ ያልፍ ነበር፡፡ በኢያሪኮ ከተማ የቀራጮች አለቃ የነበረ ዘኬዎስ የሚባል ሰው ኢየሱስን ሊያይ ይናፍቅ ነበር፡፡ ቀራጭ ማለት ከነጋዴዎችና ከሕዝቡ እየገመተ ቀረጥ (ግብር) የሚሰበስብ ማለት ሲሆን ጌታ ኢየሱስ ሰው ሆኖ በኢየሩሳሌም ምድር በሚመላለስበት ጊዜ እስራኤል በሮም መንግሥት ግዛት ሥር ስለነበሩ የሮም መንግሥት ግብርን ለመሰብሰብ በየአገሩና በየከተማው ቀራጮችን ይሾም ነበር፡፡ ቀራጮችም በየከተማው እና በየመንገዱ ዳር ቀረጥን ያስከፍሉ ነበር፡፡ ብዙ ጊዜ ከመጠን በላይ እና ያለአግባብ ግብር በማስከፈል ሕዝቡን ያማርሩ እና ትርፉን እራሳቸው ያስቀሩ ስለነበር ያለ አግባብ ይበለጽጉ ነበር፡፡ በዚህ የተነሣ ቀራጮች ያለአግባብ ከሕዝቡ ግብር እየሰበሰቡ ለባዕድ መንግሥት ስለሚሰጡ ብዙ ትርፍም ለራሳቸው ስለሚያካብቱ በእስራኤላውያን ዘንድ ቀራጮች የተጠሉ ነበሩ፡፡ ከማኅበራዊ ሕይወትም ብዙ ጊዜ ይገለሉ ነበር፡፡ (ማቴ. ፭÷፵፮፤ ፱÷፲-፲፩፤ ፲፩÷፲፱፤ ፲፰÷፲፯)

ዘኬዎስ የቀራጮች አለቃ ነው፡፡ በጣም ስስታም እና ከመጠን በላይ ገንዘብን ያፈቅር ሰለነበረ ጥቂት ወዳጆች ብቻ ነበሩት፡፡ ዘኬዎስ ስለ ናዝሬቱ ኢየሱስ ከሰማ ጊዜ ጀምሮ ግን ጌታ ኢየሱስን በዓይኑ ለማየት ከፍተኛ ፍላጎት አደረበት፡፡ አንድ ቀን የዘወትር ተግባሩን እያከናወነ የናዝሬቱ ጌታ ኢየሱስ በኢያሪኮ እያለፈ እንደሆነ ሰማ፡፡ ወዲያውኑ ሥራውን ትቶ ወደ ጌታ መሮጥ ጀመረ፡፡ ነገር ግን ጌታ ኢየሱስን የሚከተለው ብዙ ሕዝብ ስለነበር እና በተለይ ደገሞ ዘኬዎስ በጣም አጭር ሰው ሰለነበር ጌታ ኢየሱስን ለማየት አልቻለም፡፡ በዚህ ተስፋ ሳይቆርጥ መፍትሔ ሲፈልግ አንድ የሾላ ዛፍ ተመለከተና ሮጦ ወደዛፍ ላይ ወጣ፡፡ በዚያን ዘመን እንደ ዘኬዎስ ላለ የተከበረና የተፈራ ሰው እንደ ልጆች የሾላ ዛፍ ላይ መውጣት የውርደት ምልክት ነበር፡፡ ነገር ግን ዘኬዎስ ጌታ ኢየሱስን ለማየት ሰው ምን ይለኛል ሳይል የሾላው ዛፍ ላይ ወጣ፡፡ ጌታ ኢየሱስ በሕፃናት፣ በሴቶች፣ በወንዶች፣ በወጣቶች . . . ወዘተ በብዙ

www.zeorthodox.org

ሕዝብ ተከቦ ወደ ሾላው ዛፍ እየቀረበ መጣ፡፡ ዘኬዎስ ጌታ ኢየሱስን የማየት ፍላጎቱ የበለጠ ጨመረ፤ ጌታን ለማየት ዓይኑን እያንከራተተ አንገቱን ግራና ቀኝ እየመዘዘ ሲፍጨረጨር ድንገት "ዘኬዎስ ዘኬዎስ" የሚል ድምፅ በጆሮው ውስጥ ጥልቅ አለ፡፡ የጠራው ጌታ ኢየሱስ ነበር በዚህ ዘኬዎስ "እንዴት ስሜን አወቀ" "ሾላ ላይ መሆኔንስ ማን ነገረው" እያለ ሲገረም እንደገና "ዘኬዎስ ከሾላው ላይ ውረድ ዛሬ ካንተ ጋር እውል ዘንድ ይገባኛል" ብሎ ጌታ ተናገረው፡፡፡ ዘኬዎስ በጣም ተደስቶ ከሾላው ዛፍ ላይ በፍጥነት ወርዶ በጌታ እግር ሥር ወደቀ፤ ጌታም በደሰታ አቅፎ ተቀበለው ወደ ቤቱ ገባ፡፡

ጌታ ኢየሱስ ቀራጩ ዘኬዎስን እንደተቀበለው፣ ኃጢአቱንም ይቅር እንዳለው ሕዝቡ ባዩ ጊዜ ሁሉም "ከኃጢአተኛ ሰው ጋር ሊውል ገባ" ብለው አንጎራጎሩ፡፡ ዘኬዎስ ጌታ ኢየሱስን እና ሕዝቡን በቤቱ በደስታ ያስተናግድ ጀመር፡፡ እንግዶቹን ለማስደሰት የተቻለውን ሁሉ አደረገ፡፡ ከዚህ በኋላ ዘኬዎስ በጌታ ፊት ቆመ "ጌታ ሆይ ካለኝ ሁሉ እኩሌታውን ለድሆች እሰጣለሁ፣ ማንንም በሐሰት ከስሼ እንደሆንሁ አራት እጥፍ እመልሳለሁ" አለ፡፡ ዘኬዎስ ጌታ ኢየሱስ ወደ ቤቱ ስለገባ ለድሆች ማካፈልን፣ ንስሓ መግባትንና የበደላቸውን እንዲሁም በሐሰት የከሰሳቸውን ይቅርታ መጠየቅን መካስን ተማረ፡፡ ጌታ ኢየሱስ በዘኬዎስ መመለስ በጣም ተደስቶ "እርሱ ደግሞ የአብርሃም ልጅ ነውና ዛሬ ለዚህ ቤት መዳን ሆኖለታል፣ የሰው ልጅ የጠፋውን ሊፍልግና ሊያድን መጥቶአልና" አለው፡፡

## ማጠቃለያ፡-

ልጆች ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ እኛ ለእኛ ከምናስበው በላይ ያስብልናል፡፡ ሁል ጊዜ ክፉ ተግባራችንን እንጂ እኛን አይጠላንም፡፡ ዘወትር እንደ ዘኬዎስ የእኛን ወደ እርሱ መመለስ የሚናፍቅና በፍጹም ፍቅር የሚያፈቅረን ጌታ ነው፡፡ ስለዚህ ክፉ የነበሩ ሰዎች ወደ ቤተ ክርስቲያን ሲመለሱ፣ ከእግዚአብሔር ሲታረቁ እግዚአብሔርን አመስግኑ ደስም ይበላችሁ እንጂ አታጉረምርሙ፡፡

### *ጥያቄዎች፡-*

1. ልጆች ዘኬዎስ ማን ነበር?
2. ዘኬዎስ ማንን ነበር ለማየት ይናፍቅ የነበረው?
3. ጌታ ኢየሱስ የዘኬዎስን ስም እንዴት ሊያውቅ ቻለ?
4. ዘኬዎስ ኢየሱስን ለማየት ምን አደረገ?
5. ጌታ ኢየሱስ ወደ ዘኬዎስ ቤት ሲገባ የሕዝቡ ምላሽ ምን ነበር? ጌታ ኢየሱስ ዘኬዎስን እንዴት ይቅር አለው?

www.zeorthodox.org

## ተግባር፡-

- መምህሩ ልጆች ቤተ ክርስቲያን መሔድን እንዲያዘወትሩ ሌሎች ጓደኞቻቸውንም እንዲጋብዙ ያድርጋቸው፡፡
- ልጆች ጌታ ኢየሱስን እንደ ዘኬዎስ እንዴት ደስ ታሰኙታላችሁ?
- ለክርስቶስ ብላችሁ የምትተውት እና ለሌሎች የምታካፍሉት ነገር ምን እንደሆነ ለመምህራችሁ ንገሩ፡፡

# የነሐሱ እባብ

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ልጆች በእግዚአብሔር እና በአገልጋዮቹ ላይ ማጉረምረም ኃጢአት መሆኑን አውቀው ራሳቸውን ከዚህ ክፉ ተግባር እንዲጠብቁ ማስተማር ነው፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "በእግዚብሔርና በአንተ ላይ ስለተናገርን በድለናል፡፡" ዘኍ. ፳፩÷፯

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ኦሪት ዘኍ. ፳፩÷፬-፱፣ ዮሐ.፫÷፲፬-፲፰፣ ማቴ. ፮÷፳፭-፴፫፡፡

## መግቢያ፡-

- መምህሩ ያለፈውን ሳምንት ትምህርት ይከልስላቸው፡፡
- ልጆች እግዚአብሔርን አባቴ ነው የምትሉት ለምንድ ነው?
- በእግዚአብሔር ላይ ማጉረምረም ምንጩ ምንድ ነው? በአገልጋዮቹስ ላይ?
- የእግዚአብሔር ስጦታዎች ምን ምን ናቸው? እግዚአብሔርን ስለ ሰጣችሁ ነገር ሁሉ ዘወትር ታመሰግናላችሁ?

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

ልጆች ከዚህ ቀደም እግዚአብሔር በግብጽ በፈርዖን የባርነት ቀንበር ሥር የነበሩትን እስራኤል በሙሴ አማካኝንት ሕዝቡን ነፃ እንዳወጣ ታውቃላችሁ፡፡ እግዚአብሔር በሙሴ አማካኝንት ለሕዝቡ ብዙ ነገር አድርጎላቸዋል፡፡ ከፈርዖን የባርነት ቀንበር እስራኤል ነፃ የወጡት፣ ባሕረ ኤርትራን የተሻገሩት፣ የቀኑ ፀሐይ የሌሊቱ ጨለማ እንዳይጎዳቸው ቀኑን ደመና እየጋረደ ሌሊቱን በብርሃን የመራቸው እና ይጠነቀቅላቸው የነበረ እግዚአብሔር ነበር፡፡ ይህ ብቻ አልነበረም ሕዝቡ በበረሐ በውሃ ጥም እንዲሁም በረሐብ እንዳይሙቱ ከሰማይ መና ከዓለት ላይ ውሃ እያፈለቀ እግዚአብሔር ሕዝቡን ይመግብ ነበር፡፡ እግዚአብሔር ለሕዝቡ ሥጋዊ ፍላጎት ብቻ ሳይሆን ለመንፈሳዊ ሕይወታቸውም ያስብላቸው ስለነበር በሙሴ አማካኝነት ደጋግሞ ይናገራቸው እና ሕጉንም ሰጥቷቸው ነበር፡፡ በእግዚአብሔር ፍቅርን ቸርነትን ይህ ሁሉ ተደርጎላቸው ሳለ ሕዝቡ ግን በእግዚአብሔርና በሙሴ ላይ "በምድረ በዳ እንሞት ዘንድ ከግብጽ ለምን አወጣችሁን? እንጀራ የለም ውኃ የለም ሰውነታችንም ይህን ቀላል እንጀራ ተጸየፈ" ብለው አጉረመረሙ፡፡ እግዚአብሔርም በሕዝቡ ላይ እባቦችን ሰደደ ሕዝቡንም ነደፉ፡፡

ከሕዝቡም ብዙ ሰዎች በእባቦቹ ተነድፈው ሞቱ፡፡ ከሕዝቡም መካከል የተወሰኑት ወደ ሙሴ መጥተው "በእግዚአብሔር እና በአንተ ላይ ስለተናገርን በድለናል እባቦችን ከእኛ ያርቅልን ዘንድ ወደ እግዚአብሔር ለምንልን" ብለው ሙሴን ተማጸኑት፡፡ ሙሴም ስለ ሕዝቡ ወደ እግዜአብሔር እባቡን እንዲያርቅላቸው ከሕመማቸውም መርዙን አርቆ እንዲፈውሳቸው ጸለየ፡፡ እግዚአብሔር

www.zeorthodox.org

የሙሴን ልመና እና ጸሎት ተቀብሎ ሙሴ የነሐስ እባብ ሠርቶ በዓላማ ላይ እንዲሰቅለው በእባቦቹ የተነደፉ ሰዎች አባቡን አይተው እንደሚድኑ ነገረው፡፡ ሙሴ እግዚአብሔርን እንዳዘዘው አደረገ፤ ሙሴ የነሐሱን እባብ ሠርቶ በዓላማ ላይ ሰቀለ በእባብ የተነደፉ ሰዎች ሁሉ የነሐሱን እባብ ባዩ ጊዜ ሁሉም ዳኑ፡፡

## ማጠቃለያ፡-

ልጆች ከዚህ ታሪክ በእግዚአብሔር እና በአገልጋዮቹ ላይ ማጉረምረም የሚያመጣውን የእግዚአብሔርን ቁጣ ተምራችኋል፡፡ ሕዝቡን እግዚአብሔር እንደገና የታረቀው በአገልጋዩ በሙሴ ጸሎት እና ልመና መሆኑንም አውቃችኋል፡፡ ስለዚህ በእግዚአብሔር እና በአገልጋዮች ላይ ክፉ ነገር ከመናገር እንደበታችሁን ጠብቁ፡፡ የነሐሱ እባብ የክርስቶስ መስቀል ምሳሌ ነበር በክርስቶስ ሞት ለብዙ ዘመናት ተጣልቶ የነበረው የሰው ልጅ የጥል ግድግዳ ፈርሶ ሰው እና እግዚአብሔር ታርቀዋል፡፡ ስለዚህ ልጆች በእባቡ መርዝ የተነደፉት ሰዎች የነሐሱን እባብ አይተው እንደዳኑ እናንተ ከሰይጣን ፈተና እና ከኃጢአት ለመዳን ዘወትር በሕሊናችሁ የክርስቶስን መስቀል አስታውሱ፡፡ (ገላ. ፫÷፩-፫፣ ፩ቆሮ. ፩÷፲፰)

### ጥያቄዎች፡-

1. እግዚአብሔር ለሕዝቡ ያደረገውን እንክብካቤ ግለጹ፡፡
2. ሕዝቡ በእግዚአብሔርና በሙሴ ላይ ምን ብለው አጉረመረሙ?
3. እግዚአብሔር ሕዝቡን በምን ቀጣቸው?
4. የነሐሱ እባብ እና የክርስቶስ መስቀል እንዴት ይመሳሰላሉ?
5. ሕዝቡን ከእባቡ መርዙ ያዳናቸው ማን ነበር?

## ተግባር፡-

- መምህሩ ልጆች በእያንዳንዱ እንቅስቃሴአቸው የክርስቶስን መስቀል ማስታወሳቸው የሚሰጠውን ጥቅም ይግለጽላቸው፡፡
- ልጆች የነሐሱ እባብ በሐዲስ ኪዳን የምን ምሳሌ እንደሆነ ከጓደኞቻችሁ ጋር ተወያዩ፡፡

www.zeorthodox.org

# ዐሥሩ ደናግል

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ልጆች ራሳቸውን ለእግዚአብሔር መንግሥት እንዴት ማዘጋጀት እንደሚገባቸው ማስተማር፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "እነሆ ሙሽራው ይመጣል ትቀበሉት ዘንድ ውጡ" ማቴ. ፳፭÷፮

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ማቴ. ፳፭÷፲፫፣ ፳፬÷፫-፶፩፡፡

## መግቢያ፡-

- መምህሩ ያለፈውን ሳምንት ትምህርት ይከልስላቸው፡፡
- ልጆች ራሳችሁን ለእግዚአብሔር መንግሥት እንዴት እያዘጋጃችሁ ነው? ለመምህራችሁ ንገሩ፡፡
- ልጆች እስካሁን ስንት ሰርግ ላይ ተገኝታችሁ ታውቃላችሁ?
- የሰርግ ሥነ-ሥርዓት ላይ በመገኘታችሁ ምን ተሰማችሁ?

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ብዙ ጊዜ ደቀመዛሙርቱን እና ሕዝቡን በምሳሌ ስለ እግዚአብሔር መንግሥት ያስተምራቸው ነበር፡፡ አንድ ቀን መንግሥተ ሰማያት መብራታቸውን ይዘው ሙሽራውን ሊቀበሉ የወጡ ዐሥር ቆነጃጅትን ትመስላለች ብሎ ማስተማር ጀመረ፡፡ ከእነዚህ ቆነጃጅት መካከል አምስቱ ልባሞች አምስቱ ደግሞ ሰነፎች ነበሩ፡፡ ሁሉም ወደ ሰርጉ ሙሽራውን እንዲቀበሉ ተጠርተዋል፡፡ አምስቱ ልባሞች ሙሽራውን ለመቀበል መብራታቸውን እና በማሰሮ ዘይት ይዘው ወጡ፡፡ አምስቱ ሰነፎች ግን መብራታቸውን ብቻ ይዘው ሙሽራውን ይጠብቁ ጀመር፡፡ ብዙ ጊዜ ጠብቀው ሙሽራው ስላልመጣ እጅግ ሰለደከማቸው እና እንቅልፍ እንቅልፍ ስላላቸው ሁሉም ተኙ፡፡ እኩለ ሌሊትም በሆነ ጊዜ "እነሆ ሙሽራው ይመጣል ትቀበሉትም ዘንድ ውጡ" የሚል ሁካታ ሆነ፡፡ ሁሉም ይህን ጥሪ ሰምተው ከእንቅልፋቸው ነቁ፤ መብራታቸውንም ለኩሰው ሙሽራውን በመጠባበቅ ላይ ሳሉ አምስቱ ሰነፎች ልባሞቹን መብራታችን ሊጠፋብን ስለሆነ ከዘይታችሁ ስጡን ብለው ጠየቋቸው፡፡ ነገር ግን ልባሞቹ የያዙት ዘይት ለራሳቸው እንጂ ለሰነፎቹ ስለማይበቃ ይልቁኑ በፍጥነት ዘይት ወዳለበት ሒደው እንዲገዙ ነገሯቸው፡፡ አምስቱ ሰነፎች ዘይት ሊገዙ በሄዱ ጊዜ ሙሽራው መጣ፡፡ አምስቱ ልባሞች ተዘጋጅተው መብራታቸውን እና ዘይታቸውን ይዘው ይጠብቁት ስለነበረ ከሙሽራው ጋር ወደ ሰርጉ ገቡ ደጁም ተዘጋ፡፡ አምስቱ ሰነፎች በሩ ከተዘጋ በኋላ መጥተው "ጌታ ሆይ ጌታ ሆይ ክፈትልን" አሉት፡፡ ሙሽራው ግን "እውነት እላችኋለሁ አላውቃችሁም" ሲል መለሰላቸው፡፡ ጌታ ኢየሱስ ይህን ምሳሌ ለሕዝቡ ከተናገረ በኋላ ሙሽራው የሚመጣበትን ቀኒቱንና ሰዓቱን አታውቁምና ነቅታችሁ ኑሩ አላቸው፡፡

www.zeorthodox.org

## ማጠቃለያ፡-

ክርስቶስ ዳግመኛ መቼ እንደሚመጣ ስለማናውቅ ሁል ጊዜ መብራታችንን እና ዘይታችንን ይዘን በንቃት መጠበቅ እንዳለብን ከዚህ ትምህርት በሚገባ ተምረናል፡፡ በዚህ ምሳሌ ሙሽራ የተባለው ራሱ ጌታ ኢየሱስ ነው፡፡ አምስቱ ልባሞች እምነትን ከምግባር ጋር የያዙ ንስሓ ገብተው ጌታን የሚጠብቁ ምሳሌ ናቸው፡፡ አምስቱ ሰነፎች ያልተዘጋጁ ሰዎች ምሳሌ ናቸው፡፡ ዘይቱ የምግባር መብራቱ የእምነት ምሳሌ ናቸው፡፡ በሩ ተዘጋ ማለት ሙሽራው ክርስቶስ ዳግመኛ ለፍርድ ከመጣ በኋላ ንስሓ ለመግባት የምናደርገው ጥረት ሁሉ ከንቱ ድካም መሆኑን አውቀን ዛሬውኑ ንስሓ መግባት እና መዘጋጀት እንዳለብን የሚያስተምር ምሳሌ ነው፡፡ ስለዚህ ልጆች እምነትን እና ምግባርን እንደ ልባሞቹ ቆነጃጅት ይዛችሁ ጌታ ኢየሱስን ነቅታችሁ ጠብቁት፡፡

### *ጥያቄዎች፡-*

1. ጌታ ኢየሱስ ብዙ ጊዜ በምሳሌ የሚያስተምረው ለምን ነበር?
2. ከዐሥሩ ቆነጃጅት መካከል አምስቱ ልባሞች የቀሩት ደግሞ ሰነፎች የተባሉበት ምክንያት ምን ነበር?
3. ዐሥሩ ቆነጃጅቶች ሙሽራው ሲዘገይ ምን አደረጉ?
4. በእኩለ ሌሊት የተሰማው ድምፅ ምን የሚል ነበር?
5. የዚህን ታሪክ ዝርዝር ምሳሌና ትርጉም ለጓደኞቻችሁ አስረዱ፡፡

## ተግባር፡-

- መምህሩ ይህን ትምህርት ልጆች በተግባር እንዲሠሩ አስፈላጊውን ቁሳቁስ ያሟላላቸው፡፡
- ከተማሪዎቹ መካከል አምስት ሴቶችን እና አምስት ወንዶችን በመምረጥ እንዲሁም አንድ ሙሽራ በማድረግ እንዲተውኑ ያድርጋቸው፡፡

www.zeorthodox.org

# ጌታችን ኢየሱስ የከነናዊቷን ሴት ልጅ ፈወሰ

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ጌታ ኢየሱስ ማንኛውንም ዓይነት በሽታ የማዳን እና የመፈወስ ኃይል እንዳለው ማስተማር፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "አንቺ ሴት እምነትሽ ታላቅ ነው" ማቴ.፲፭÷፳፰

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ማቴ.፲፭÷፳፩-፳፰፣ ፬÷፳፫-፳፭፣ ዕብ.፲፩÷፩-፫፣ ፩ዮሐ ፫÷፰

## መግቢያ፡-

- መምህሩ ያለፈውን ሳምንት ትምህርት ይከልስላቸው፡፡
- ልጆች በወንጌል ጌታ ኢየሱስ ከተለያየ በሽታ የፈወሳቸውን ሰዎች የምታስታውሱትን ለመምህራችሁ ንገሩ፡፡
- ቤተሳባችሁ ውስጥ አንድ ሰው በድንገት ቢታመም ምን ታደርጋላችሁ?

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

ጌታ ኢየሱስ በዚህ ምድር በነበረው አገልግሎት ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይል በትጋት የእግዚአብሔርን መንግሥት ወንጌል አስተምሯል፡፡ ብዙ ሰዎችን ከሰይጣን እስራት ፈቷል፡፡ ሕሙማንን በነፃ ፈውሷል፡፡ እርሱ ሰውን ለማዳን እና የመንግሥቱን ወንጌል ለማስተማር አይከብደውም ነበር፡፡ ጌታ ኢየሱስ በጌንሴሬጥ ምድር የነበሩት ሕመምተኞች በልብሱ ጫፍ ከፈወሳቸው በኋላ ወደ ጢሮስና ወደ ሲዶና ከተማ መጣ፡፡ በእነዚህ ከተሞች የምትኖር አንዲት ከነናዊት ሴት ልጇን ጋኔን ክፉኛ ያሰቃያት ስለነበር ጠዋትና ማታ የሴት ልጇን ሥቃይ እያየች ታለቅስ ነበር፡፡

ልጇን ከሰይጣን እስራት የሚፈታላት ሰው እየፈለገች የልጇን መዳን ስትጠባበቅ የናዝሬቱ ኢየሱስ በልዩ ልዩ በሽታ የተያዙ ሰዎችን በነፃ እንደሚፈውስ ሰማች፡፡ ጌታ ኢየሱስ የት እንደሚገኝ ስትጠይቅ እርሱ ወደምትኖርበት ከተማ እየመጣ እንደሆነ ነገሯት፡፡ የዚህን ጊዜ በፍጥነት ከቤቷ ወጥታ ወደ ጌታ መጣች፤ ነገር ግን ብዙ ሕዝብ ይከተለው ስለነበረ ቀርባ ችግሯን ማስረዳት እንደማትችል ሲገባት "ጌታ ሆይ፡- የዳዊት ልጅ ማረኝ ልጄን ጋኔን ክፉኛ ይዞአታል ብላ ጮኸች" ጌታ ኢየሱስ ግን ምንም ነገር አልመለሰላትም ዝም አላት፡፡ ከነናዊቷ ሴት ግን ያለማቋረጥ ደጋግማ መጮህ ጀመረች በዚህ ጊዜ ደቀመዛሙርቱ ወደ ጌታ ቀርበው "በኋላችን ትጮሃለችና አሰናብታት" እያሉ ለመኑት፡፡

www.zeorthodox.org

ጌታ ኢየሱስ ከነናዊቷ ሴት ትልቅ እምነት እንደነበራት ያውቅ ስለነበረ እና ለሕዝቡ የእምነትን ኃይል ማስተማር ስለፈለገ ለሴቲቱ ጩኸት ወዲያውኑ መልስ አልሰጠም፤ ይልቁንም የእምነቷን ጽናት ለሕዝቡ ለማሳየት "ከእስራኤል ቤት ለጠፉት በጎች በቀር አልተላኩም" ብሎ ተናገረ፡፡ ከነናዊቷ ሴት ግን ጌታ ሆይ እርዳኝ እያለች ሰገደችለት፡፡ ጌታ ኢየሱስ ግን እንደገና "የልጆችን እንጀራ

ይዞ ለቡችሎች መጣል አይገባም” አላት፡፡ ይህ ለሁለተኛ ጊዜ የሴቲቱ እምነት የፈተነበት ጥያቄ ነበር፡፡ ሴቲቱ ግን እምነቷ ትልቅ ስለነበረ ተስፋ ሳትቆርጥ “አዎን ጌታ ሆይ ቡችሎችም እኮ ከጌቶቻቸው ማዕድ የወደቀውን ፍርፋሪ ይበላሉ” አለች፡፡ ጌታ ኢየሱስ ከነናዊቷ ሴት ጠንካራ እና ጥልቅ እንዲሁም ጽኑ እምነት እንዳላት ባየ ጊዜ “አንቺ ሴት፡- እምነትሽ ታላቅ ነው እንደወደድሽ ይሁንልሽ” አላት፡፡ በዚያው ቅጽበት የሴቲቱ ልጅ የያዛት ክፉ ጋኔን ለቆአት ሔደ፣ ከሕመሟም ተፈወሰች፡፡

## ማጠቃለያ፡-

ከነናዊቷ ሴት በፍጹም ልቧ አምና ከጌታ ኢየሱስ ሌላ ማንም ልጇን ሊያድናት እንደማይችል አውቃ ወደ ክርስቶስ መጮሁዋ በእናቷ እምነት ልጇ ድናለች፡፡ በዚህ ትምህርት ጌታ ኢየሱስ የእስራኤል ብቻ ሳይሆን የዓለም አዳኝ መሆኑን አውቃችኋል፡፡ ስለዚህ እናንተም እንደ ከነናዊቷ ሴት በፍጹም ልባችሁ በእግዚአብሔር ታመኑ፡፡ ጌታ እንዲያደርግላችሁ የምትፈልጉትን ነገር በጊዜው እስኪሰጣችሁ በእምነት በመጽናት ተሰፋ ሳትቆርጡ ጠብቁ፡፡

### *ጥያቄዎች፡-*

1. የከነናዊቷ ሴት ችግር ምን ነበር?
2. ጌታ ኢየሱስ የሴቲቱን ጥያቄ በፍጥነት ያልመለሰው ልምንድነው?
3. የሴቲቱ ልጅ የዳነችው እንዴት ነበር?
4. ጌታ “እስራኤል ቤት ለጠፉት በጎች በቀር አልተላኩም” ሲል ምን ማለቱ ነው?
5. በክፉ ጋኔን ተይዛ የነበረችው ልጅ በእናቷ እምነት መዳኗ ምን ያመለከታል?

## ተግባር፡-

- መምህሩ ልጆች እያንዳንዱን ተግባራቸውን በእምነት ማከናወን የሚሰጣቸውን ጠቀሜታ ተግባራዊ ምሳሌዎችን በመጥቀስ ያስረዳቸው፡፡
- ልጆች በቤተሰባችሁ እምነት እና ጸሎት ወይም በእናንተ እምነት እግዚአብሔር ለሌሎች ያደረገውን ድንቅ ነገር ለጓደኞቻችሁ መስክሩ፡፡

www.zeorthodox.org

# ጌታችን ኢየሱስ የመበለቲቱን ልጅ አስነሣ

**የትምህርቱ ዓላማ፦-** ጌታ ኢየሱስ በሞት ላይ ሥልጣን እንዳለው ለልጆች ማሳወቅ፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፦-** "አንተ ጎበዝ እልሃለሁ ተነሣ" ሉቃ. ፯÷፲፬

**ተጨማሪ ምንባባት፦-** ሉቃ ፯÷፲፬-፲፯፣ ዮሐ. ፲፩÷፳፫-፳፯፣ ያዕቆ.፩÷፳፯

## መግቢያ፦-

- መምህሩ ያለፈውን ሳምንት ትምህርት ይከልስላቸው፡፡
- ልጆች እናት እና አባት የሌላቸውን ልጆች ትንከባከባላችሁ? እንዴት?
- ጧሪ እና ተንከባካቢ የሌላቸውን አረጋውያን የሚንከባከቡ ቤተሰቦች ያሏችሁ ልጆች ልምዳችሁን ለጓደኞቻችሁ ንገሩ፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት፦-

ልጆች ባለፈው ሳምንት ጌታ ኢየሱስ አጋንንትን በኃይል እና በሥልጣን እያወጣ ብዙ ሰዎችን ከሰይጣን እስራት ይፈታ እንደነበር ተምራተኋል፡፡ ዛሬ ደግሞ ጌታ ኢየሱስ በሞት ላይ ሥልጣን እንዳለው ትማራላችሁ፡፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በቅፍርናሆም ከተማ ምሽትን አሳለፈ፡፡ በዚያም የሮማ ወታደር አገልጋይ የነበረውን ሰው ከሕመሙ ከፈወሰው በኋላ ሲነጋ ወደ ናይን ከተማ መጣ፡፡ ደቀመዘሙርቱ እና ብዙ ሕዝብ ጌታ ኢየሱስን ይከተለው ነበር፡፡ ብዙ ሰዎች ጌታ ኢየሱስ እንዲባርካቸው እና ከተለያየ በሽታ እንዲፈውሳቸው ይፈልጉ ስለነበር ጌታ እጁን ዘርግቶ ባረካቸው ከነበረባቸውም በሽታ ሁሉ አዳናቸው፡፡ ወደ ናይን ከተማ በር በቀረቡ ጊዜ ጌታ ኢየሱስ ብዙ ሕዝብ ስለተመለከተ ከደቀመዛሙርቱ መካከል ምን እንደሆነ እንዲያዩ የተወሰኑትን ላካቸው፡፡ ሕዝቡ ወደ ጌታ እየቀረቡ መጡ፡፡ ብዙ ጩኸት እና ልቅሶ ይሰማ ነበር፡፡ እጅግ ከባድ ሐዘን ስለነበር ብዙ ሴቶች ጥቁር ልብስ ለብሰው ይጮሃሉ፣ ያለቅሳሉ፣ ደረታቸውን ይመታሉ፡፡ ወንዶችም በሐዘን ተውጠው እያለቀሱ የሞተውን ልጅ ተሸክመው ወደ ቀብር ስፍራ እየተጓዙ ነው፡፡

የሞተው ልጅ ለእናቱ አንድ የነበረ ሲሆን እናቱም በመበለት ነበረች፡፡ ልጆች በመጽሐፍ ቅዱስ መበለት ማለት ባልዋ የሞተባት ወይም በማናቸውም ምክንያት ያለ ባል የምትኖር ሴትን የሚያመለክት ነው፡፡ የተላኩት ደቀመዛሙርት ሁኔታውን ከጠየቁ በኋላ ወደ ጌታ ተመልሰው የሞተው ልጅ ለመበለቲቱ አንድ ብቻ እንደሆነ እና ከሞት እንዲያስነሣው ለመኑት፡፡

ጌታም ወደ መበለቲቱ ቀርቦ ባያት ጊዜ አዘነላት፣ እና አታልቅሺ አላት፡፡ የሞተውን ልጅ ወደ ተሸከሙት ሰዎች ቀርቦ ቃሬዛውን ነካ፡ የተሸከሙትም ሰዎች ቆሙ፡፡ ጌታ ኢየሱስም የሞተውን ልጅ "አንተ ጎበዝ ተነሣ" አለው፡፡ የሞተውም ልጅ ቀና ብሎ ተቀመጠ መናገርም ጀመረ፡፡ ጌታም ከሞት የተነሣውን ልጅ ወስዶ ለእናቱ ሰጣት፡፡ ይህን ሲመለከቱ የነበሩ ሁሉ የሆነውን ነገር

www.zeorthodox.org

አይተው በጣም ፈሩ "ታላቅ ነቢይ በእኛ መካከል ተነሥቶአል ደግሞ እግዚአብሔር ሕዝቡን ጎበኘ" እያሉ እግዚአብሔርን አመሰገኑ፡፡ የጌታ ኢየሱስም ዝና በይሁዳ ሁሉ በዙሪያውም ባለች አገር ሁሉ ወጣ፡፡

## ማጠቃለያ፡-

ልጆች በዚህ ትምህርት ጌታ ኢየሱስ ባሏ የሞተባትን ሴት እንዴት እንዳዘነላት አንድ ልጇንም ከሞት በማስነሣት እንዴት እንዳጽናናት አይታችኋል፡፡ እናንተም እንደ ጌታ ኢየሱስ እናት እና አባት የሞቱባቸውን ልጆች ፍቅር በመስጠት ተንከባከቧቸው፣ ጠያቂ የሌላቸውን ባልቴቶችን ከቤተሰባችሁ ጋር በመሆን በነገር ሁሉ እርዷቸው፡፡ ይህን በማድረጋችሁ ጌታ ኢየሱስ በብዙ በረከት እናንተን እና ቤተሰቦቻችሁን ይባርካል፡፡

### *ጥያቄዎች፡-*

1. ልጆች በባልቴት እና በመበለት መካከል ያለው ልዩነት ምንድነው?
2. የመበለቲቷ ልጅ የሞተው በየት ከተማ ነው?
3. ጌታ ኡየሱስ መበለቷን ምን አላት?
4. ጌታ ኢየሱስ የሞተውን ልጅ ምን ብሎ ተናገረው?
5. የሞተው ልጅ ከተነሣ በኋላ የሕዝቡ ምላሽ ምን ነበር?

## ተግባር፡-

- መምህሩ ልጆች ወላጅ አልባ ሕፃናትን እንዲጎበኙ ሁኔታዎችን ያመቻችላቸው፡፡
- ልጆች እናት እና አባት የሌላቸውን ልጆች በምን ማገዝ እና መርዳት እንደሚችሉ ውይይት ያድርጉ፡፡

www.zeorthodox.org

# ባሕራን

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ለልጆች ከባሕራን ታሪክ የመላእክትን ጥበቃ እንዲገነዘቡ ማድረግ፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "የእግዚአብሔር መልአክ በሚፈሩት ዙሪያ ይሰፍራል ያድናቸዋል፡፡" መዝ.፴፫(፴፬)÷፯

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ድርሳነ ሚካኤል፣ መዝ.፺(፺፩)÷፲፩፣ ዘጸ.፳፫÷፳፫-፳፫፣ ዘፍ.፲፱÷፩-፳፪

## መግቢያ፡-

- መምህሩ ያለፈውን ሳምንት ትምህርት ይከልስላቸው፡፡
- ልጆች የእግዚአብሔር መላእክት ዕለት ዕለት እንደሚጠብቋችሁ ታምናላችሁ?
- ስለ ቅዱስ ሚካኤል የምታውቁትን ለመምህራችሁ ንገሩ፡፡
- መላእክት ለሰው ልጆች ያስፈለጉበት ምክንያት ምንድነው?

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

ልጆች የእግዚአብሔር መላእክት ብዙ ሰዎችን ከክፉ ነገር እንደጠበቁ እና ከሞት እንዳዳኑ መጽሐፍ ቅዱስ የሚመሰክረው እውነት ነው፡፡ የእግዚአብሔር ሥራ በዘመናት የሚገደብ ስላልሆነ ዛሬም እግዚአብሔር መላእክቱን እየላከ ልጆቹን ከክፉ ነገር ያድናል፡፡ መላእክት ማለት የእግዚአብሔር መልእክተኞች ማለት ነው፡፡ ከእግዚአብሔር ኃጢአተኞችን ሊቀጡ የእግዚአብሔር ልጆችን ደግሞ ሊጠብቁ ይላካሉ፡፡ ቤተ ክርስቲያን መጽሐፍ ቅዱስን መሠረት በማድረግ መላእክት የእግዚአብሔር መልእክተኞች እንደሆኑ ታምናለች፡፡ እግዚአብሔር ስለአከበራቸው መላእክትን ታከብራለች፣ በጸሎታቸው እና በአማላጅነታቸው ትታመናለች፡፡ በዚህ ምክንያት ከመጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮ ጋር የማይጋጩ የመላእክትን ጥበቃ የሚናገሩ አዋልድ መጻሕፍት በቤተ ክርስትያን አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛሉ፡፡ ከነዚህ መካከል ድርሳነ ገብርኤል፣ ድርሳነ ዑራኤል፣ ድርሳነ ሩፋኤል፣ ድርሳነ ሚካኤል . . . ወዘተ ይገኙበታል፡፡ በዚህ ትምህርት በድርሳነ ሚካኤል ላይ ታሪኩ ስለተጻፈለት ባሕራን ስለሚባል ሰው እናጠናለን፡፡

www.zeorthodox.org

በአንድ ዘመን የገናናው መልአክ የቅዱሰ ሚካኤልን በዓል በየወሩ የሚያከብር በመልአኩ ስም ድሆችን የሚመግብ አንድ ሰው ነበር፡፡ በዚህ በጎ ሥራው ይቀናበት እና ይናደድበት የነበረ ሌላ ሰውም ነበር፡፡ የቅዱስ ሚካኤል ወዳጅ የነበረው ሰው ሚስት ፀነሰች፣ ነገር ግን በእርግዝናዋ ወራት ባሏ ታሞ ሞተ፡፡ የመውለጃዋ ጊዜ ሲደርስ ወንድ ልጅ ወለደች፣ አባቱ የቅዱስ ሚካኤል ወዳጅ ስለነበር መልአኩ ተገልጾ ከባረከው በኋላ እግዚአብሔር ሀብት እንደሚሰጠው ነገረው፡፡

ቀድሞውኑ በሕፃኑ አባት ሲቀና የነበረው ባለጠጋ ሰው ይህን ሲሰማ በጣም ስለቀና እና ስለተናደደ ሊገድለው ፈለገ፡፡ ይህን

ፍላጎቱን ለማሳካት ወደ ሕፃኑ እናት ሔዶ ልጁን እንድትሰጠው እና እንዲያሳድግላት አዛኝ እና ተቆርቋሪ መስሎ ጠየቃት፡፡ የሕፃኑ እናት ባሏ የሞተባት ሴት እና አቅም የሌላት ድሃ ስለነበረች የባሏ ጓደኛ ብዙ ገንዘብ ሲሰጣት እና ወዳጅ መስሎ ልጁን በማሳደግ እንደሚረዳት ሲገልጽላት በደስታ ልጁን ሰጠችው፡፡ ይህ ክፉ ባለጠጋ ሕፃኑን በሳጥን ውስጥ ከቶ በባሕር ላይ ጣለው፡፡ ሕፃኑን የያዘው ሳጥን በባሕሩ ላይ እየተንሳፈፈ ሩቅ ቦታ ሐደ፡፡ በመጨረሻም በአንድ የባሕር ዳርቻ ሳጥኑ ሕፃኑን ይዞ አረፈ፡፡ በዚህ ጊዜ አንድ የአካባቢው ገበሬ ሳጥኑን አግኝቶ ሲከፍተው በጣም ውብ የሆነ ልጅ በውስጡ በማግኙቱ ልጅም ስላልነበረው በጣም እየተደሰተ ወደቤቱ ወስዶ ሕፃኑን ማሳደግ ጀመረ፡፡ ገበሬው ሕፃኑን ከባሕር ዳርቻ ስላገኘው ስሙን ባሕራን ብሎ ሰየመው፡፡ ይህ በሆነ ከሃያ ዓመታት በኋላ ሕፃኑን የጣለው ባለጠጋ ሰው ወደ ገበሬው ሀገር በንግድ ምክንያት ይመጣና በገበሬው ቤት በእንግድነት ያርፋል፡፡ ባለጠጋው ለእንግድነት በገበሬው ቤት አርፎ እራት እየበሉ ሲጫወቱ ባሕራንን አይቶ ልጁ እንደሆነ ገበሬውን ይጠይቀዋል፡፡

ገበሬውም ከሃያ ዓመታት በፊት ከባሕር ዳርቻ እንዳገኘው የእግዚአብሔርን ተአምር ይነግረዋል፡፡ ነገር ግን ባለጠጋው ሰው ባሕር ላይ የጣለው ሕፃን እንዳልሞተ ባሕራን ማን መሆኑን በማወቁ እንደገና በቅንዓት ሊገድለው ፈልጎ አንድ ምክንያት ፈጠረ፡፡ ለገበሬው የረሳው ዕቃ እንዳለ እና ባሕራን ሔዶ እንዲያመጣለት ለዚህም ጥሩ ክፍያ እንደሚከፍለው ነገረው፡፡ ገበሬው በባለጠጋው ሐሳብ በመስማማቱ ባለጠጋው “ይህን ሰው ግደለው በድብቅ ቦታም ቅበረው” የሚል ደብዳቤ ለአገልጋዩ ጽፎ ባሕራንን ላከው፡፡ ይህን ያላወቀው ባሕራን የሞቱን ደብዳቤ ይዞ መጓዝ ጀመረ፡፡ ነገር ግን በመንገድ ላይ ቅዱስ ሚካኤል ወጣት ሰው መስሎ በፈረስ ላይ ሆኖ ተገለጠለትና ባለጠጋው የጻፈውን ደብዳቤ ከባሕራን ተቀብሎ መልእክቱን ቀይሮ መለሰለት፡፡ ቅዱስ ሚካኤል የቀየቀረው መልእክት “ልጄን ድራችሁ ሀብቴን አውርሱት” የሚል ነበር፡፡ በዚህ መሠረት ባሕራን የባለጠጋው ቤተ እንደደረሰ ደብዳቤውን ለአገልጋዩ ሰጠ፡፡ አገልጋዩም ድግስ ደግሶ የነጋዴውን ልጅ ለባሕራን ዳራት፡፡ ከአርባ ቀናት በኋላ ባለጠጋው ከንግዱ ወደ ቤቱ ሲመለስ የሰርግ ዘፈን ሰምቶ ምን እንደሆነ ይጠይቃል፡፡ የልጁ እና የባሕራን ሰርግ መሆኑን ሲሰማ በድንጋጤ ወድቆ ሞተ፡፡ ባሕራን የገዳዩን ልጅ አግብቶ ሀብቱን ወርሶ መኖር ጀመረ፡፡ ባለጠጋው ከሕፃንነቱ ጀምሮ ሊገድለው ይፈለገው ነበር እግዚአብሔር ግን ቅዱስ ሚካኤልን ልኮ ከሞት አስመለጠው፡፡ ዘወትር የመልአኩ ጥበቃ ባሕራንን ስላልተለየው ጠላቱ እና ገዳዩ ሊያገኘው አልቻለም ነበር፡፡

## ማጠቃለያ፡-

www.zeorthodox.org

ልጆች የእግዚብሔር መልአክ ቅዱስ ሚካኤል ባሕራንን ከሕፃንነቱ ጀምሮ እንዴት እንደጠበቀው የሞቱን ደብዳቤ ሽሮ ከሞት እንዳስመለጠው በዚህ ትምህርት አውቃችኋል፡፡ በእርግጥም የእግዚአብሔር መልአክ በሚፈሩት ሰዎች ዙሪያ ይከባል ያድናቸውማል የሚለው ቃል የታመነ መሆኑን ከባሕራን ሕይወት መረዳት ችላችኋል፡፡ ባሕራን አባቱ የቅዱስ ሚካኤል ወዳጅ ነበር፣ እርሱም የአባቱን መልካም ሥራ እየሠራ እና በቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን እያገለገለ ኖረ፡፡ ስለዚህ ልጆች እናንተም እንደ ባሕራን የእግዚአብሔር መላእክት እንደሚጠብቋችሁ በመታመን ለመላእክት ክብር ስጡ፡፡

***ጥያቄዎች፡-***

1. ባሕራን ማለት ምን ማለት ነው?
2. የባሕራን አባት መቼ ሞተ?
3. ባለጠጋው ሰው ባሕራንን ለመግደል ይፈልገው የነበረው ለምንድነው?
4. ባሕራንን እንደአባት ሆኖ ያሳደገው ማን ነበር?
5. የባሕራንን ደብዳቤ የቀየረው ማን ነው?

## ተግባር፡-

- መምህሩ ልጆች እያንዳንዳቸው ጠባቂ መልአክ እንዳላቸው እና የመላእክትን ተግባር ይግለጽላቸው፡፡
- ልጆች ቤተሰቦቻችሁ የየትኛው መልአክ ወዳጆች እንደሆኑ እና ለመልአኩ ያላቸውን ክብር እንዴት እንደሚገልጹ ለመምህራችሁ ንገሩ፡፡

www.zeorthodox.org

# አስቴር (ክፍል አንድ)

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ለልጆች ከአስቴር ሕይወት እግዚአብሔር ሌሎችን ለማዳን ሰዎችን እንደሚጠቀም ማስተማር፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "አስቴርም በሚያዩአት ሁሉ ዓይን ሞገስ አግኝታ ነበር" አስቴር. ፪÷፲፭

**ተጨማሪ ምንባብ፡-** መጽሐፈ አስቴር፤

## መግቢያ፡-

- መምህሩ ያለፈውን ሳምንት ትምህርት ይከልስላቸው፡፡
- መምህሩ ፋርስ የሚባለው ሀገር በዚህ ዘመን የትኛው ሀገር እንደሆነ ይግለጽላቸው፡፡
- ልጆች እግዚአብሔር ሰዎችን ምክንያት አድርጎ ያደረገላችሁ በጎ ነገር ምንድነው? ለመምህራችሁ እና ለጓደኞቻችሁ ተናገሩ፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

በፋርስ ንጉሥ አርጤክስስ ዘመን እስራኤላውያን በምርኮኝነት በፋርስ ይኖሩ ነበር፡፡ ከዕለታት አንድ ቀን የፋርስ ንጉሥ አርጤክስስ በቤተመንግሥቱ ታላቅ ግብዣ አደረገ፡፡ በግብዣውም ላይ ባለሥልጣኖች፣ ባለሚሎች እና አገልጋዮች ተገኝተው እየበሉ እና እየጠጡ እጅግ በጣም ይደሰቱ ነበር፡፡ ነገር ግን በግብዣው ላይ የንጉሡ ሚስት ንግሥት አስጢን ስላልተገኘች ብዙ ሰዎች አለመኖሯን ይጠይቁ ስለነበር ንጉሡ ንግሥት አስጢን የንግሥት ዘውድ ደፍታ እንዲሁም በከበሩ ጌጣጌጦች አሸብርቃ በፍጥነት ወደ ግብዣው እንድትመጣ ታማኝ አገልጋዮቹን ላከ፡፡ ንግሥት አስጢን ግን በግብዣው ላይ እንደማትገኝ አንቢታዋን በመግለጿ ንጉሥ አርጤክስስ በጣም ተናደደ፡፡ ንጉሡ ከአማካሪዎቹ ጋር በመሆን ብዙ ከመከረ በኋላ አስጢን ንግሥት መሆኗ እንዲቀር እና በምትኳ ንግሥት የምትሆን ሴት እንድትፈለግ ተሰማማ፡፡

www.zeorthodox.org

በንጉሡ ትእዛዝ መሠረት በፋርስ ይኖሩ የነበሩ መልከመልካም ሴቶች ከየሥፍራው ተሰብስበው ለምርጫ ቀረቡ፡፡ ከእነዚህ መልከመልካም እና ቆንጆ ሴቶች መካከል አስቴር አንዷ ነበረች፡፡ አስቴር በፋርስ በምርኮ ከሚኖሩ እስራኤላውያን መካከል አንዷ ስትሆን እናት እና አባት ስላልነበራት አጎቷ መርዶክዮስ ያሳድጋት ነበር፡፡ አጎቷ መርዶክዮስ የንጉሡን ዓዋጅ እንደሰማ አስቴር በጣም ቆንጆ ሴት ስለነበረች በንጉሡ እንድትመረጥ አዘጋጃት፡፡

ከዐሥራ ሁለት ወራት ዝግጅት በኋላ ቆነጃጅቱ በንጉሥ አርጤክስስ ፊት ቀረቡ፡፡ ከቆነጃጅቱ መካከል አስቴር በንጉሡ እና በሚያዩአት ሰዎች ሁሉ ፊት ሞገስን በማግኘቷ አንደኛ ሆና ተመረጠች፡፡ ከዛን ዕለት ጀምሮ አስቴር የፋርስ ንግሥት ሆና የንግሥና

ዘውድ ደፋች፡፡ ንጉሥ አርጤክስስ ቆንጆዋን እና ተወዳጅ የሆነችውን አስቴርን በማግኙቱ በጣም ተደስቶ ለአስቴር ክብር ታላቅ በዓል አድርጎ ሕዝቡን ጋበዘ፡፡ አስቴር በሰው ሀገር በምርኮ የምትኖር ሴት ስትሆን እግዚአብሔር ሞገስና ውበት ሆኗት የንጉሥ ሚስት ሆነች፡፡ በፋርስ መንግሥት ላይ እግዚአብሔር ንግሥት አድርጎ ሾማት፡፡

## ማጠቃለያ፡-

ልጆች በዚህ ትምህርት እግዚአብሔር አስቴርን በሰው ሀገር እንዴት እንዳከበራት እና ሞገስ እንደሆናት አይታችኋል፡፡ የአስቴር ቁንጅና ውጫዊ ብቻ አልነበረም፣ ውስጣዊ ውበትም ነበራት፡፡ እግዚአብሔር ሞገስ ስለሆናት እና መወደድን ስለሰጣት ከብዙዎች መካከል ተመርጣ ንግሥት ሆነች፡፡ እናንተም እግዚብሔር በነገር ሁሉ ሞገስ እንዲሆናችሁ እና በብዙ እንዲሾማችሁ ውስጣችሁ በእግዚአብሔር ቃል የተዋበ እና ያማረ ይሁን፡፡ ለውጫዊ ውበታችሁ እንደምትጨነቁ ሁሉ የውስጣችሁ ውበትም እንዲሁ ተጨነቁለት፡፡

### *ጥያቄዎች፡-*

1. እስራኤል በምርኮ በፋርስ በሚኖሩባት ዘመን የነበረ ንጉሥ ማን ይባላል?
2. የፋርስ ንጉሥ ሚስት ማን ትባል ነበር?
3. ንጉሥ አርጤክስስ አዲስ ንግሥት የፈለገበት ምክንያት ምን ነበር?
4. አስቴርን ያሳደጋት ሰው ማን ይባላል?
5. አስቴር የፋርስ ንግሥት የሆነችው እንዴት ነበር?
6. ከዚህ ታሪክ ምን ተማራችሁ?

## ተግባር፡-

- መምህሩ ልጆች ለቁንጅና የሚሰጡትን ከፍተኛ ግምት እንዲያስተውሉ በተለይ ከውጪያዊ ውበት በላይ ለውስጣዊ ውበታቸው እንዲያስቡበት ያስገንዝባቸው፡፡
- ልጆች አንድ ሰው (ሴት) ቆንጆ ነው (ናት) የምትሉበት መመዘኛ ምንድነው? ለመምህራችሁ እና ለጓደኞቻችሁ በመነገር ተወያዩበት፡፡

www.zoorthodox.org

# አስቴር (ክፍል ሁለት)

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** እግዚአብሔር በአስቴር አማካኝነት ሕዝቡን ከሞት እንዴት እንዳዳናቸው መማር፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** “አንተን ተስፋ የሚያደርጉ አያፍሩም” መዝ. ፳፬(፳፭)፥፫

**ተጨማሪ ምንባብ፡-** መጽሐፈ አስቴር፤

## መግቢያ፡-

- መምህሩ ያለፈውን ሳምንት ትምህርት ይከልስላቸው፡፡
- ልጆች ወደፊት ትልቅ ደረጃ ላይ ስትደርሱ ለቤተሰባችሁ፣ ለቤተ ክርስቲያን እና ለሀገራችሁ ምን ማድረግ እንደምትፈለጉ ለመምህራችሁ ንገሩ፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

ልጆች ባለፈው ሳምንት አስቴር አይሁድ በምርኮ በፋርስ ሀገር በሚኖሩበት ዘመን እግዚአብሔር ሞገስ ሆኗት ንግሥት ሆና መመረጧን ተምራችሁ ነበር፡፡ ዛሬ ደግሞ እግዚአብሔር አይሁድን ከሞት ለማዳን አስቴርን እንዴት ምክንያት እንዳደረጋት ትማራላችሁ፡፡ በንጉሥ አርጤክስስ ዘመን በፋርስ መንግሥት ላይ የተሾመ ሐማ የሚባል ባለሥልጣን ነበር፡፡ ሐማ ከፍተኛ ባለሥልጣንና የንጉሥ አርጤክስስ የቅርብ ሰው ስለነበረ ወደ ቤተመንግሥት ሲገባ እና ሲወጣ ብዙ ሕዝብ ይሰግድለት ነበር፡፡ ነገር ግን የንግሥት አስቴር አጎት መርደክዮስ ለሐማ እንደማይሰግድ እና አይሁዳዊ እንደሆነ የሐማ የቅርብ ሰዎች ከፉ ነገር ስለተናገሩበት ሐማ በጣም ተቆጣ፡፡

www.zeorthodox.org

ሐማ ንጉሥ አርጤክስስን በውሸት አሳስቶ በፋርስ መንግሥት ግዛት ውስጥ ያሉ አይሁዳውያን ሁሉ እንዲገደሉ በንጉሡ ማኅተም ዓዋጅ እንዲወጣ አደረገ፡፡ ብዙ አይሁዳውያን በሐማ ተንኮልና በዓዋጁ በጣም አዘኑ፡፡ ነገር ግን መርዶክዮስ እግዚብሔር አስቴርን ንግሥት ያደረጋት ለዚህ ቀን እንደሆነ በማመን እና በአስቴር ምክንያት የሞት ዓዋጅ እንደሚቀየር ተስፋ በማድረግ ወደ አስቴር መልእክት ላከ፡፡ ንግሥት አስቴር እና ሕዝቡ ሦስት ቀን እና ሦስት ለሊት በጾም እና በጸሎት እግዚአብሔርን ከጠየቁ በኋላ አስቴር ወደ ንጉሥ አርጤክስስ ገብታ ሁኔታውን አስረዳችው፡፡ ንጉሡም አስቴር ስለ ሕዝቧ ያቀረበችውን ልመና እና ምልጃ ተቀብሎ የሐማን ዓዋጅ ሻረ፡፡ ሐማ ንጉሥ አርጤክስስን በሐሰት በማሳሳቱ ሞት ተፈረደበት፡፡ አይሁድ በንግሥት አስቴር ምክንያት እግዚአብሔር የሞቱን ዓዋጅ በሕይወት እንደየቀረው፣ ሐማም እንደ ተፈረደበት ዜናውን ሲሰሙ እግዚአብሔርን አመሰገኑ፡፡

## ማጠቃለያ፡-

በምርኮ ይኖሩ ለነበሩ አይሁዳውያን ንግሥት አስቴርን ከሞት እንዲያመልጡ እግዚአብሔር ምክንያት እንዳደረጋት በዚህ ትምህርት አውቃችኋል፡፡ ሕዝቡ በፍጹም ልባቸው በመታመን እግዚአብሔርን በጾም እና ጸሎት ተስፋ በማድረጋቸው በአስቴር ልመና እንዲሁም ምልጃ የሞት ዓዋጅ ሊየቀር ችሏል፡፡ ስለዚህ ልጆች እግዚአብሔር ሰዎችን ምክንያት አድርጎ ስለአደረገላችሁ በጎ ነገር ሁሉ አመስግኑት፡፡ እናንተም ለሌሎች መዳን እና መለወጥ ምክንያት ሲያደርጋችሁ እንደ አስቴር እግዚአብሔርን በመተማመን ጠንክራችሁ አገልግሉ፡፡

### *ጥያቄዎች፡-*

1. የንጉሥ አርጤክስስ የቅርብ ሰው እና ከፍተኛ ባለሥልጣን ማን ይባላል?
2. ሐማ በአይሁድ ላይ ያወጀው ዓዋጅ ምን ነበር?
3. የሐማን ዓዋጅ እንደሰማ መርዶክዮስ ምን አደረገ?
4. የሞትን ዓዋጅ የቀየረው ማን ነው?
5. ከዚህ ታሪክ በተለይ ከአስቴር ሕይወት ምን ተማራችሁ?

## ተግባር፡-

- *መምህሩ ልጆች እግዚአብሔር በቤተሰቦቻቸው፣ በዘመዶቻቸው፣ በመምህራኖቻቸው፣ በሐኪሞቻቸው . . . ወዘተ እንዴት እንደረዳቸው እና የእነርሱን ውለታ መዘንጋት እንደማይገባ ተግባራዊ ምሳሌዎችን በመስጠት ያስረዳቸው፡፡*
- ልጆች ዕውቀት፣ ገንዘብ እና ሥልጣን ሲኖራችሁ ምን ለመሥራት አስባችኋል? ለመምህራችሁ እና ለጓደኞቻችሁ ንገሩ፡፡

www.zeorthodox.org

# ገብር ሔር

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** እንደታማኙ ባሪያ ልጆች እግዚአብሔር የሰጣቸውን ልዩ ልዩ ስጦታ መጠቀም እንዲችሉ መርዳት፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "አንተ በጎ ታማኝም ባሪያ በጥቂቱ ታምነሃል በብዙ እሾምሃለሁ" ማቴ. ፳፭÷፳፩፡፡

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ማቴ.፳፭÷፲፬-፴፣ ፪ጢሞ.፪÷፩፣ ቆሮ. ፲፪÷፬-፲፩፡፡

## መግቢያ፡-

- መምህሩ ያለፈውን ሳምንት ትምህርት ይከልስላቸው፡፡
- ልጆች ከእግዚአብሔር በነፃ ያገኛችኋቸው ስጦታዎች ምንድን ናቸው?
- ልጆች ተሰጥኦችሁን እና ዝንባሌአችሁን ለመምህራችሁ ንገሩ፡፡
- ተሰጥኦችሁን ወደ ፊት እንዴት ልተጠቀሙበት አስባችኋል?

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

ልጆች ባለፈው ሳምንት ስለ ዐሥሩ ቆነጃጅት፣ አምስቱ ልባሞች፣ አምስቱ ደግሞ ሰነፎች እንደነበሩ ልባሞቹ ወደ ሰርጉ እንደገቡ እና ሰነፎቹ ግን ወደ ሰርጉ መግባት እንዳልቻሉ ዝርዝር ትምህርቱን ተምራችሁ ነበር፡፡ ዛሬ ደግሞ በጌታ ስለተመሰገነው ሰለ ታማኙ አገልጋይ (ገብር ሔር) በዚህ ትምህርት እንማራለን፡፡ ከዕለታት አንድ ቀን አንድ ባለጠጋ ሰው ለሦስት ሰዎች እንደየአቅማቸው ለአንዱ አምስት መክሊት (ገንዘብ)፣ ለሁለተኛው ሁለት መክሊት፣ ለሦስተኛው ደግሞ አንድ መክሊት ሰጠቶአቸው እርሱ ወደሩቅ ሀገር ሔደ፡፡ አምስት የተቀበለው ባሪያ ነግዶ ዐሥር መክሊት ሆነለት፡፡ ሁለት የተቀበለውም ባሪያ ነግዶ አራት መክሊት አደረገው፡፡ ነገር ግን አንድ የተቀበለው መክሊቱን ሳይሠራበት ቆፍሮ መሬት ቀበረው፡፡ ከብዙ ዓመታት በኋላ ባለጠጋው ሰው ወደባሮቹ መጥቶ የሰጣቸውን ገንዘብ ምን እንዳደረጉት መጠየቅ ጀመረ፡፡

www.zeorthodox.org

አምስት የተቀበለው ሌላ አምስት እንዳተረፈ፣ ሁለትም የተቀበለው እንዲሁ ነገር ግን አንድ የተቀበለው መሬት ውስጥ እንደቀበረው ተራ በተራ ተናገሩ፡፡ ባለጠጋው ሰው አምስትና ሁለት የተቀበሉት "መልካምና ታማኝ ባሪያ በጥቂቱ ታምነሃል በብዙ እሾምሃለሁ ወደ ጌታ ደስታ ግባ" የሚል የምሥራች ቃል ተናገራቸው፡፡ አንድ መክሊት ለተቀበለው ግን "አንተ ክፉና ሃኬተኛ ባሪያ . . . መክሊቱን ውሰዱበት . . . በውጭ ወዳለው ጨለማ አውጡት በዚያ ልቅሶና ጥርስ ማፏጨት ይሆናል" ብሎ ፈረደበት፡፡ በጥቂቱ የታመኑት ሁለቱ ባሮች በብዙ ተሹመው ወደ ጌታቸው ደሰታ ሲገቡ ሰነፉ ባሪያ ግን ተዋርዶ እና ተፈርዶበት ወደ ጨለማ ውስጥ ተጣለ፡፡

## ማጠቃለያ፡-

ልጆች በዚህ ታሪክ እግዚአብሔር በሰጣቸው ነገር ተደስተው በታማኝነት ያገለገሉ ባሪያዎች በብዙ እንደተሾሙ እና ወደ ጌታቸው ደስታ እንደገቡ ሰነፉ ባሪያ ግን በስንፍናው ምክንያት ያለው ገንዘብ ተወስዶበት ወደ ውጪ እንደተጣለ ተምራችኋል፡፡ ስለዚህ እናንተም እንደታማኙ አገልጋይ እግዚአብሔር የሰጣችሁን ተሰጥኦ፣ መልካም ቤተሰብ፣ የትምህርት ዕድል፣ ጤና እና ችሎታ በመጠቀም በጎ ነገሮችን አድርጉ፡፡ ይህን ስታደርጉ በጥቂቱ መታመናችሁ ነውና እግዚአብሔር የበለጠ በዕውቀትና በማስተዋል ይባርካችኋል፡፡ እግዚአብሔር ስንፍናን እንደ ሚጠላም አውቃችሁ ራሳችሁን ከስንፍና ጠብቁ፡፡ በትምህርታችሁ፣ በሥራችሁ እና በአጠቃላይ በሕይወታችሁ ንቁ እና ጉበዝ ታታሪ ሠራተኛ ሁኑ፡፡

### *ጥያቄዎች፡-*

1. ባለጠጋው ሰው ገንዘቡን የሰጠው ለማን ነበር?
2. ባለጠጋው የማን ምሳሌ ነው? ባሮቹስ የማን ምሳሌ ናቸው?
3. ታማኝ አገልጋይ ማለት ምን ማለት ነው?
4. ሰዎች ሰነፍ የሚሆኑቱ በምን ምክንያት ነው?
5. ከዚህ ታሪክ ምን ተረዳችሁ?

## ተግባር፡-

- መምህሩ ልጆች የበለጠ ዝንባሌያቸውን እና ተሰጥኦቸውን እንዲያውቁ የሚያስች ላቸውን ዘዴ ይጠቁማቸው፡፡
- ልጆች ተሰጥኦቸውን በአግባቡ እንዴት መጠቀም እንደሚገባቸው ንገራቸው፡፡
- የሥዕል፣ የሥነ-ጽሑፍ፣ የግጥም እና የመዝሙር እንዲሁም የማስተማር ተሰጥኦ ያላቸውን ልጆች በመለየት አቅማችውን የሚያሳድጉበትን ሥልጠና እና የአገልግሎት መድረክ አመቻችላቸው፡፡

www.zeorthodox.org

# ኢያሱ

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ልጆች የእግዚአብሔርን ፈቃድ ብቻ ማገልገልን ከኢያሱ ታሪክ እንዲማሩ ማገዝ፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "ከሙሴ ጋር እንደ ሆንሁ እንዲሁ ከአንተ ጋር እሆናለሁ" ኢያሱ.1÷5፡፡

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** መጽሐፈ ኢያሱ፣ ዘጸ.፲፯÷፰-፲፫፣ ፳፬÷፲፫፣ ፴፪÷፲፯፣ ፴፫÷፲፩፣ ዘኁ. ፲፩÷፳፰፣ ፲፫ እና ፲፬፣ ፳፯÷፲፰-፳፫፣ ዘዳ. ፫÷፳፰፣ ፴፩÷፳፫፡፡

## መግቢያ፡-

- መምህሩ ያለፈውን ሳምንት ትምህርት ይከልስላቸው፡፡
- እግዚአብሔር ሰዎችን ለአገልግሎት የሚመርጠው እንዴት ነው?
- ልጆች ሙሴ እግዚአብሔርን እና ሕዝቡን እንዴት እንዳገለገለ አስታውሱ፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

ልጆች ከዚህ ቀደም በሙሴ መሪነት እግዚአብሔር ሕዝቡን ከግብጽ ባርነት ነፃ እንዳወጣ ተምራችሁ እንደነበር ታስታውሳላችሁ፡፡ በዚህ ትምህርት ከሙሴ በኋላ እስራኤል ከነዓንን እንዲወርሱ ሲመራቸው ስለነበረው ሰው ስለ ኢያሱ እንማራለን፡፡ ኢያሱ ማለት የስሙ ትርጉም "እግዚአብሔር አዳኝ ነው" ማለት ሲሆን የነዌ ልጅ ኢያሱ ብላቴና ሆኖ ከግብጽ ወጣ፡፡ ሙሴም ከአማሌቃውያን ጋር እንዲዋጋ ስለአዘዘው ከአማሌቅ ጋር ተዋግቶ አሸነፈ፡፡ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ የሙሴ የቅርብ ሰው ሆኖ ሙሴን ማገልገል ጀመረ፡፡ ከነዓንን እንዲሰልሉ ሙሴ ከቃዴስ ዐሥራ ሁለት ሰላዮችን ሲልክ ኢያሱ ከእነርሱ መካከል ነበረ፡፡ ዐሥር ሰላዮች ተመልሰው በሕዝቡ መካከል ሽብር ሲነዙ ኢያሱና ካሌብ ግን ከሙሴ ጋር ሆነው ሕዝቡን አረጋጉ፡፡ ሕዝቡን በእምነት እንውጣ ብለው በእግዚአብሔር እንዲታመኑ በማድረጋቸው ኢያሱና ካሌብ ከነዓን እንደሚገቡ እግዚአብሔር ተስፋ ሰጣቸው፡፡ የእግዚአብሔር ባሪያ ሙሴ ከሞተ በኋላ እግዚአብሔር የሙሴን አገልጋይ የነዌን ልጅ ኢያሱን ሕዝቡን እንዲመራ እና ለአባቶቻቸው የገባውን ቃል ኪዳን ከነዓንን እንዲያወርስ መረጠው፡፡ እግዚአብሔር ኢያሱን "በሕይወትህ ዕድሜ ሁሉ ማንም አይቋቋምህም ከሙሴ ጋር እንደሆንሁ እንዲሁ ከአንተ ጋር እሆናለሁ አልጥልህም አልተውህም . . . ጽና አይዞህ፣ አትፍራ፣ አትደንግጥ" ብሎ አበረታው፡፡

www.zoorthodox.org

የእስራኤል ሕዝብ በኢያሱ መሪነት ዮርዳኖስን ተሻግረው ኢያሪኮን ያዙ፡፡ ዋና ስፍራቸውም ጌልጌላ ሆነ፡፡ ከጌልጌላ እየዘመቱ የከነዓንን ነገሥታት አሸነፉ፡፡ እግዚአብሔር ቀኑን በማርዘም እና በገባኦን ሰማይ ላይ ፀሐይን በማቆም እንዲሁም በረዶ በማዝነብ

ረዳቸው፡፡ በመጨረሻም በእግዚአብሔር ኃይል በኢያሱ መሪነት እስራኤል ከነዓንን ወረሱ፡፡ ኢያሱ መሬቱን ለእስራኤል ነገዶች አከፋፈለ፡፡ ኢያሱ ሕዝቡ እግዚአብሔርን ትተው ጣዖታትን ቢያመልኩ እግዚአብሔር እንደሚቀጣቸው እና እንደሚፈርድባቸው አሳሰባቸው፡፡ ከዚህ በኋላ ኢያሱ የመሞቱ ጊዜ ሲቀርብ ሕዝቡን ሰብስቦ እግዚአብሔር ከአባቶቻቸው ከነ አብርሃም ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ ያደረገላቸውን ውለታ እንዳይረሱ አስጠነቀቃቸው፡፡ ከሕዝቡም ጋር ቃል ኪዳን ተጋብቶ ለመታሰቢያ ታላቅ ድንጋይ በሴኬም አቆመ፡፡ ኢያሱ በዘመኑ ሁሉ ለእግዚአብሔር በመታዘዝ ሕዝቡ እግዚአብሔርን ብቻ እንዲያመልኩና እንዲያገለግሉ አደረገ፡፡ ኢያሱ በመቶ ዐሥር ዓመቱ ሞተ፡፡ ሕዝቡም በርስቱ በኤፍሬም አገር ቀበሩት፡፡

## ማጠቃለያ፡-

ልጆች ኢያሱ በዘመኑ ሁሉ እግዚአብሔርን በእምነት የታዘዘ እና በፈቃደኝነት ያገለገለ ሰው እንደነበር ከዚህ ትምህርት አውቃችኋል፡፡ ስለዚህ እናንተም እንደ ኢያሱ በእምነት እግዚአብሔርን ታዘዙ፡፡ እግዚአብሔር በአገልግሎታችሁ እንዲከብር እና እንዲደሰት በመጨረሻም መንግሥቱን እንዲያወርሳችሁ ሁል ጊዜ ፈቃዱን አድርጉለት፡፡

### ***ጥያቄዎች፡-***

1. ኢያሱ የስሙ ትርጉም ምንድ ነው?
2. ሙሴ ከነዓንን እንዲሰልሉ ስንት ሰዎችን ልኮ ነበር?
3. ኢያሱና ካሌብ ብቻ ከነዓንን የወረሱበት ምስጢር ምን ነበር?
4. በኢያሱ መሪነት ሕዝቡ የተሻገሩት ወንዝ ምን ይባላል?
5. ኢያሱ በስንት ዓመቱ ሞተ የት ተቀበረ?

## ተግባር፡-

- መምህሩ ልጆች የእግዚአብሔርን ፈቃድ ከሰው ፈቃድ መለየት የሚችሉበትን ዘዴ ያሳያቸው፡፡
- ለልጆች መሪነት እንዴት እንደሆነ እና አንድ መሪ ሊኖሩት የሚያስፈልጉትን ባሕሪያት ይንገራቸው፡፡
- ልጆች ወደፊት ምን ዓይነት መሪ መሆን እንደምትፈልጉ ለመምህራችሁ ንገሩ፡፡

www.zeorthodox.org

# ቅዱስ እስጢፋኖስ

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ክርስቶስን የመምሰል ሕይወትን ከቅዱስ እስጢፋኖስ አገልግሎት ልጆች እንዲማሩ ማገዝ፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "ጌታ ሆይ ይህን ኃጢአት አትቁጠርባቸው" ሐዋ. ፯÷፷፡፡

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ሐዋ. ፮÷፩-፲፭፣ ፯÷፩-፷፣ ፩ቆሮ ፲፩÷፩፣ ፩ጢሞ ፫÷፰-፲፫፡፡

## መግቢያ፡-

- *መምህሩ ያለፈውን ሳምንት ትምህርት ይከልስላቸው፡፡*
- *ልጆች ሰማዕታት እነማን ናቸው?*
- *የዲያቆናት አገልግሎት በቤተ ክርስቲያን ምንድ ነው?*
- *ልጆች ለክርስቶስ ያላችሁ መታመን እስከ ምን ድረስ ነው?*

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

በሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን ዕለት ዕለት የእግዚአብሔር ቃል እየሰፋ ይሄድ ስለነበር ብዙ ሰዎች በክርስቶስ አምነው የሐዋርያትን ማኅበር ተቀላቀሉ፡፡ በዚያን ዘመን ሁሉም ያላቸውን እያመጡ አንድ ላይ ይኖሩና ይመገቡ ስለነበር ሕዝቡን መመገብ እንዲሁም ቃሉን ማገልገል ለሐዋርያት እጅግ እየከበደ መጣ፡፡ ቅዱሳን ሐዋርያት ይህን በማስተዋል ሕዝቡን ሰብስበው ከመካከላቸው በመልካም የተመሰከረላቸውን መንፈስ ቅዱስና ጥበብም የሞላባቸውን ሰባት ሰዎች እንዲመርጡ እና ሕዝቡን እንዲያገለግሉ አደረጓቸው፡፡ ሕዝቡም በሐዋርያት ቃል እጅግ ተደስተው ሰባት ሰዎችን መርጠው በሐዋርያት ፊት አቆሙአቸው፡፡ ሐዋርያትም ከጸለዩ በኋላ በሰባቱ ዲያቆናት ላይ እጃቸውን ጫኑባቸው፤ ከዚያን ዕለት ጀምሮ ዲያቆናት የሐዋርያትን ቤተ ክርስቲያን ማገልግል ጀመሩ፡፡ ዲያቆን ማለት አገልጋይ ማለት ሲሆን በሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን ለድሆች በትክክል እርዳታ ለማድረስ፣ በማዕድም ለማገልገል ተመርጠው ነበር፡፡ በኋላም እየቆየ ዲቁና በቤተ ክርስቲያን እንደ አንድ ማዕርግ ሆነ፡፡ ቅዱስ ጳውሎስም ስለ ዲያቆናት ጠባይና አገልግሎት በመልእክቱ ጽፏል፡፡

ቅዱስ እስጢፋኖስ በኢየሩሳሌም በሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን ከተሾሙት ሰባት ዲያቆናት መካከል አንዱ ነበር፡፡ ጸጋንና ኃይልን ተሞልቶ በሕዝቡ መካከል ድንቅንና ታላቅ ምልክትን ያደርግ ነበር፡፡ ከግሪክ አገር የመጡ አይሁድ ሲከራከሩት እስጢፋኖስ ይናገርበት የነበረው ጥበብና መንፈስ ይቃወሙ ዘንድ አልቻሉም፡፡ በዚህ የተነሣ አይሁድ በሐሰት እስጢፋኖስን ከሰውና የሐሰት ምስክሮችን አዘጋጅተው በአይሁድ ሸንጎ ፊት አቆሙት፡፡ ሊቀ ካህናቱም እስጢፋኖስን የተከሰሰበትን ምክንያት እንዲናገር እድል ሲሰጠው ቅዱስ እስጢፋኖስ ከአብርሃም ጀምሮ የነበረውን የአይሁድን ታሪክ፣ ነቢያት ስለክርስቶስ የተናገሩትን ትንቢት እና

www.zeorthodox.org

ፍጻሜውን ዘርዝሮ ከነገራቸው በኋላ ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ አዳኝ መሲሕ እንደሆነ ሞትን ድል አድርጎ በሥልጣኑ እንደተነሣ ያለ ፍርሐት በሕዝቡ ሁሉ ፊት በመመስከሩ የአይሁድ ሸንጎ እስጢፋኖስ በድንጋይ ተወግሮ እንዲሞት ፈረዱበት፡፡ ከከተማውም ውጪ አውጥተው ዕርቃኑን በድንጋይ ደብድበው ገደሉት፡፡ ሳውልም በእስጢፋኖስ መገደል ተስማምቶ የገዳዮቹን ልብስ ይጠብቅ ነበር፡፡ ቅዱስ እስጢፋኖስ ስለ ክርስቶስ በመጀመሪያ የተገደለ ሰማዕት ነው፡፡ ሰማዕት ማለት ምስክር ማለት ነው፡፡ ቅዱስ እስጢፋኖስ ስለ ክርስቶስ ሲመሰክር ስለተገደለ በቤተ ክርስቲያን የመጀመሪያው ሰማዕት ይባላል፡፡

ቅዱስ እስጢፋኖስ ሰማያት ተከፍተው የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስን በአባቱ ቀኝ ቆሞ ተመልክቶአል፡፡ ለገዳዮቹ "ጌታ ሆይ ይህን ኃጢአት አትቁጠርባቸው" ብሎ ለምኖአል፡፡ "ጌታ ኢየሱስ ሆይ ነፍሴን ተቀበል" ብሎ በመጸለዩ ኢየሱስ ክርስቶስ ከአብ ጋር እኩል እንደሆነ መስክሯል፡፡ ይህን መስክሮ ቅዱስ እስጢፋኖስ አንቀላፋ፤ ክርስቲያኖችም ወስደው ቀበሩት ታላቅ ልቅሶም አለቀሱለት፡፡

## ማጠቃለያ፡-

ልጆች ቅዱሳን ሐዋርያት ወንጌልን የሰበኩት እና ስለ ክርስቶስ የመሰከሩት እንደዛሬው በተመቻቸ ሁኔታ ውስጥ ሆነው ሳይሆን ብዙ ዋጋ ከፍለው ነው፡፡ በዚህ ትምህርት ቅዱስ እስጢፋኖስ በዱቁና እንዴት ቤተ ክርስቲያንን በታማኝነት ያገለግል እንደነበር በተለይ ስለ ክርስቶስ ጨክኖ እውነትን በመመስከሩ እንደሞተ አውቃችኋል፡፡ ስለዚህ እናንተም እንደ ቅዱስ እስጢፋኖስ የእውነት ምስክሮች በመሆን ቤተ ክርስቲያንን አገልግሉ፡፡

### *ጥያቄዎች፡-*

1. በሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን ለመጀመሪያ ጊዜ ስንት ዲያቆናት ተመረጡ?
2. የእስጢፋኖስ ክስ ምን ነበር?
3. እስጢፋኖስ በአይሁድ ሸንጎ ስለ ማን መሰከረ?
4. እስጢፋኖስ ክርስቶስን በሕይወቱ እንዴት መሰለ?
5. ቤተ ክርስቲያን የመጀመሪያው ሰማዕት እያለች የምትጠራው ማንን ነው?በእስጢፋኖስ ሞት የተባበረ ሰው ማን ይባላል?

www.zeorthodox.org

## ተግባር፡-

- መምህሩ ለልጆች በዚህ ዘመን የእውነት ምስክሮች እንዴት መሆን እንደሚችሉ እና እውነት የሚያስከፍለውን ዋጋ እንዲገነዘቡ ያወያያቸው፡፡
- ልጆች እንደ እስጢፋኖስ ቤተ ክርስቲያንን በምን ለማገልገል እንዳሰባችሁ ለመምህራችሁ እና ለጓደኞቻችሁ ንገሩ፡፡

# ዲቦራ

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ልጆች ከዲቦራ ጥበበኛ እና ጠንካራ መሪነትን እንዲማሩ መርዳት፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "እኔ ለእግዚአብሔር እቀኛለሁ" መሳ. ፭÷፫፡፡

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** መጽሐፈ መሳፍንት ምዕራፍ አንድ እና አምስት፡፡

## መግቢያ፡-

- መምህሩ ያለፈውን ሳምንት ትምህርት ይከልስላቸው፡፡
- ልጆች በንጉሥ እና በመስፍን መካከል ያለውን ልዩነት ታውቃላችሁ?
- ከመጽሐፍ ቅዱስ የምታውቋቸውን ነገሥታትና መሳፍንት ጥቂቶቹን ለመምህራችሁ ንገሩ፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

ናዖድ የሚባለው መስፍን ከሞተ በኋላ የእስራኤል ልጆች በእግዚአብሔር ፊት ክፉ ሥራ እንደገና በመሥራታቸው እግዚአብሔር ለከነዓን ንጉሥ ለኢያቢሰ አሳልፎ ሰጣቸው፡፡ የንጉሥ ኢያቢስ የሠራዊት አለቃ ሲሣራ ዘጠኝ መቶ የብረት ሰረገሎች ስለነበሩት ሃያ ዓመት ያህል እጅግ እስራኤልን አስጨነቃቸው፡፡ በዚህ ዘመን ዲቦራ የምትባል ሴት ነቢይትና ዳኛ ሆና በእስራኤል ልጆች ላይ ትፈርድ ነበር፡፡ በጦርነት ጊዜ በጦር አዝማችነት፣ በሰላምም ጊዜ በፈራጅነት እስራኤልንና እግዚአብሔርን ያገለግሉ ከነበሩት መሳፍንት ዲቦራ አንዷ ነበረች፡፡ ዲቦራ በዘንባባ ዛፍ ሥር ተቀምጣ በእስራኤል ልጆች ላይ ትፈርድ እንዲሁም ትንቢትን ትናገር ስለነበር እስራኤል መጥተው ጮኹ፡፡

www.zeorthodox.org

በዲቦራ አማካኝነት እስራኤል ከእግዚአብሔር ዘንድ ረድኤትን አገኙ፡፡ ነቢይቱ ዲቦራ ባርቅ የተባለውን ሰው አነሳስታ የኢያቢስን የሠራዊት አለቃ ሲሣራን በጦርነት እንዲገጥሙ አደፋፈራቸው፡፡ ነገር ግን ባርቅ ዲቦራ ከእርሱ ጋር ወደ ጦርነቱ የማትሄድ ከሆነ እርሱም እንደማይወጣ ስለነገራት ዲቦራ ከባርቅ ጋር ዐሥር ሺህ ሠራዊት ይዛ ወደ ታቦር ተራራ ወጣች፡፡ ጠላታቸውም በእግዚአብሔር ኃይል ተሸነፈ፡፡ እግዚአብሔር በነቢይቱ ዲቦራና በባርቅ አገልግሎት እስራኤልን ድል አድራጊ ካደረጋቸው በኋላ ዲቦራ ለእግዚአብሔር ክብር የምስጋና መዝሙር ዘመረች፡፡ ሕዝቡም ከሃያ ዓመት የጭቆና ዘመን በኋላ ነፃ በመውጣታቸው እግዚአብሔርን ከፍ ከፍ አድርገው አመሰገኑ፡፡

## ማጠቃለያ፡-

ልጆች ዲቦራ እግዚአብሔርን የምታፈቅር በፈቃዱም የምትመራ ጥበበኛ እና ጠንካራ ሴት ነበረች፡፡ በዚህ የተነሣ ከእግዚአብሔር ጋር በነበራት የጠበቀ ግንኙነት እና ጠንካራ እምነት ሕዝቡ በጠላቶቻቸው ላይ ድል አድራጊ እንዲሆኑ ከባርቅ ጋር በመሆን መራቻቸው፡፡ ስለዚህ ልጆች እናንተም ከእግዚአብሔር ጋር ቃሉን በማንበብ እና በጸሎት የጠበቀ ግንኙነት ካላችሁ እንደ ዲቦራ ሌሎችን ወደ እግዚአብሔር ማቅረብ እና የተሻለ ሕይወት እንዲኖሩ ማድረግ ትችላለችሁ፡፡

### *ጥያቄዎች፡-*

1. ናዖድ የተባለው መስፍን ከሞተ በኋላ የእስራኤል ልጆች ምን ሆኑ?
2. የከነዓናዊው ንጉሥ የሠራዊት አለቃ ማን ይባላል?
3. ዲቦራ ማን ናት?
4. ወደ ታቦር ተራራ ዲቦራ ከማን ጋር ሄደች?
5. የእስራኤል ልጆች በጦርነቱ እንዴት ድል ማድረግ ቻሉ?
6. ከዲቦራ ታሪክ ምን ተማራችሁ?

## ተግባር፡-

- መምህሩ ልጆች ስለ ነፃነት ትክክለኛ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ያድርጋቸው፡፡
- ሴቶች እንደ ዲቦራ በዚህ ዘመን እግዚአብሔርን እና ሕዝቡን እንዴት ማገልገል እንደሚችሉ አወያያቸው፡፡
- የነቢይቱ ዲቦራ እና የባርቅ መተባበር ምንን ያመለክታል ለመምህራችሁ እና ለጓደኞቻችሁ ሐሳባችሁን አካፍሉ፡፡

www.zeorthodox.org

# ጌታ ኢየሱስ የደቀመዛሙርቱን እግር አጠበ

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ልጆች ከጌታ ኢየሱስ አገልግሎት ትሕትናን እንዲማሩ ማገዝ፣

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "እናንተ ደግሞ እርስ በርሳችሁ እግራችሁን ትተጣጠቡ ዘንድ ይገባችኋል፡፡" ዮሐ. ፲፫÷፲፬

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ዮሐ.፲፫÷፩-፳፣ ማቴ. ፲፩÷፳፰-፴፣ ሮሜ.፲፪÷፲፮፣ ፊል. ፪÷፩-፲፩

## መግቢያ፡-

- መምህሩ ያለፈውን ሳምንት ትምህርት ይከልስላቸው፡፡
- ልጆች ካህናት የምእመናንን እግር በቤተ ክርስቲያን የሚያጥቡት መቼ ነው?
- በብሉይ ኪዳን እጅግ ትሑት የነበረውን ሰው አስታውሱ፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የመንግሥቱን ወንጌል እየሰበከ ደቀመዛሙርቱን ያስተምራቸው የነበረው በቃል ብቻ ሳይሆን በተግባርም ጭምር ነበር፡፡ ውደዱ ሲል ወዶ ነው፣ ጹሙና ጸልዩ ሲል እርሱ አስቀድሞ አድርጎት ነው፡፡ ጠላታችሁን ውደዱ፣ የበደላችሁን ይቅር በሉ ሲል እርሱ የሰቀሉትን ይቅር ብሎ ነው፡፡ ዛሬ በዚህ ትምህርት ጌታ ኢየሱስ ለደቀመዛሙርቱ ስለ ትሕትና እንዴት በተግባር እንዳስተማራቸው እናያለን፡፡ ጌታ ኢየሱስና ደቀመዛሙርቱ ሐሙስ ዕለት ማታ የፋሲካን እራት ከበሉ በኋላ በመታጠቢያ ውስጥ ውሃ አድርጎ ማበሻም ጨርቅ ይዞ ክርስቶስ የደቀመዛሙርቱን እግር ማጠብ ጀመረ፡፡ በዚህ ጊዜ ጴጥሮስ ምክንያቱን ስላልተረዳ አልታጠብም ሲል ተናገረ፡፡ ጌታ ግን ምክንያቱን በኋላ እንደሚረዳ እና እንደሚያስተውሉ ነግሮት አጠበው፡፡ የሁሉንም ደቀመዛሙርት እግር አጥቦ ከጨረሰ በኋላ እግራቸውን ያጠበው ትሕትናን ሊያስትምራቸው እንደሆነ ነገራቸው፡፡

www.zeorthodox.org

እርሱ መምህር እና ጌታቸው ሆኖ ሳለ የእነርሱን እግር ካጠበ እነርሱ ደግሞ ትሑታን ሆነው እርስ በርሳቸው መከባበር እና መታዘዝ እንዳለባቸው አዘዛቸው፡፡ ትሕትና ራስን ዝቅ ማድረግ ሲሆን ሌላ ሰው እንዲጠቀም መፈለግን እና ከራስ ይልቅ ሌላ ሰው እንደሚሻል መቁጠርን ያመለክታል፡፡ እግዚአብሔር ትሕትናን ይወዳል፡፡ (፪ ዜና. ፯÷፲፬፣ ምሳ. ፲፭÷፴፫) ክርስቲያኖች ሁላችን በትሕትና እንድንመላለስ ታዘናል፡፡ (፩ጴጥ.፫÷፰፣ ፊል.፪÷፫-፬) ለዚህ ነው ጌታ ደቀመዛሙርቱ እርስ በርሳቸው በትሕትና እንዲያገለግሉ በስቅለቱ ዋዜማ በጸሎተ ሐሙስ ዕለት ይህን የተግባር ትምህርት ያስተማራቸው፡፡

## ማጠቃለያ፡-

ጌታ ሰዎችን ሁል ጊዜ በቃል ከማስተማር ይልቅ በተግባር ማስተማር የበለጠ እንደሆነ የደቀመዛሙርቱን እግር በማጠብ አሳይቶናል፡፡ ስለዚህ ልጆች ቃሉን የምትሰሙ ብቻ ሳይሆን የምታደርጉ ሁኑ፡፡ እርስ በርሳችሁም ተከባበሩ በፍቅርም ቤተ ክርስቲያንን አገልግሉ፡፡

***ጥያቄዎች፡-***

1. ልጆች ጌታ በተግባር ያስተማራቸው ትምህርቶች ምንድናቸው?
2. እግሬን አልታጠብም ያለው ሰው ማን ነበር?
3. ጌታችን የደቀመዛሙርቱን እግር ያጠበበት ዕለት ምን ይባላል?
4. ትሕትና ምንድ ነው?
5. ከክርስቶስ አገልግሎት ምን ተማራችሁ?

## ተግባር፡-

- መምህሩ ልጆች በትሕትና እንዴት ቤተ ክርስቲያንን ማገልገል እንደሚችሉ ያወያያቸው፡፡
- በራስ መተማመን እና በትሕትና መካከል ያለውን ልዩነት መምህሩ ያስረዳቸው፡፡

www.zeorthodox.org

# ሳውል በደማስቆ

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ልጆች ትክክለኛ ባልሆነ ሃይማኖት ቅንዓት በሌሎች ላይ ክፉ ነገር እንዳያደርጉ ከሳውል ታሪክ እንዲረዱ ማድረግ፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** ስሜን ይሸከም ዘንድ ለእኔ የተመረጠ ዕቃ ነው፡፡

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ሐዋ. ፱፥፩-፲፱፣ ፳፫፥፯፣ ፳፪፥፳፮-፳፱፣ ፯፥፶፰-፷፣ ፊል ፫፥፭-፮

## መግቢያ፡-

- መምህሩ ያለፈውን ሳምንት ትምህርት ይከልስላቸው፡፡
- ልጆች ለእግዚአብሔር ቀንታችሁ ታውቃላችሁ? እንዴት?
- ልጆች ስለ ሃይማኖት አክራሪነት ያላችሁ ግንዛቤ ምንድነው? ለመምህራችሁ ንገሩ፡፡
- በሃይማኖት ስም ክፉ ነገርን የሚያደርጉ ሰዎች ምንጫቸው ምንድነው?

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

አይሁድ በተለያዩ ሀገሮች ተበትነው በሚኖሩበት ዘመን ሳውል በጠርሴስ ከተማ ተወለደ፡፡ ሳውል ማለት ከእግዚአብሔር የተለመነ ማለት ሲሆን አባቱ ከብንያም ወገን የሆነ ፈሪሳዊ ስለነበር ለትምህርት ወደ ኢየሩሳሌም ተልኮ ስመጥር ከሆነው አስተማሪ ከገማልያል የሙሴን ሕግና የአይሁድን ወግ ጠንቅቆ ተማረ፡፡ ከኢየሩሳሌም ውጪ ተበትነው በሌላ ሀገር የሚኖሩ አይሁድ ሁለት ዜግነት ስለነበራቸው ሳውል ከአባቱ ሮማዊ ዜግነት ወረሰ፡፡ በተበተኑት አይሁድ ዘንድ በሁለት ስም መጠራት የተለመደ ስለነበር ሳውል ሁለት ስም ነበረው፡፡ ይህም ሳውል የዕብራይስጥ ስሙ ሲሆን ጳውሎስ ደግሞ ሮማዊ ስሙ ነው፡፡ ሳውል በተወለደበት በጠርሴስ ከተማ በልጅነቱ ድንኳን መስፋትን ተማረ፡፡ ጎልማሳ በሆነ ጊዜ ስለ አይሁድ ሃይማኖት ቀንቶ በክርስቶስ ያመኑትን አጥብቆ ጠላቸው ሊያጠፋቸውም ፈለገ፡፡ በዚህ ምክንያት እስጢፋኖስ በድንጋይ ሲወገር የገዳዮቹን ልብስ እየጠበቀ ሞቱን ይመለከት ነበር፡፡

www.zeorthodox.org

ከዚህ በኋላ የጌታን ደቀመዛሙርት እንደሚገድላቸው እየዛተባቸው ወደ ሊቀ ካህናቱ ሄደ በክርስቶስ የሚያምኑትን ሰዎች ሁሉ እያሰረ ወደ ኢየሩሳሌም እንዲያመጣቸው ደብዳቤ ተቀበለ፡፡ ነገር ግን ሳውል አማኞችን ለማሳሰር ወደ ደማስቆ ሲጓዝ ሳለ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ከሰማይ "ሳውል ሳውል ስለምን ታሳድደኛለህ?" ሲል ጠራው፡፡ ሳውልም በሰማዩ ብርሃን ተመቶ መሬት ላይ ወድቆ ነበር፡፡ ሳውልም የሚናገረው ማን እንደሆነ ሲጠይቅ "አንተ የምታሳድደኝ እኔ ኢየሱስ ነኝ" የሚል መልስ ሰማ፡፡ ሳውል በሰማው ቃል በጣም ደንግጦ እና ተደንቆ "ጌታ ሆይ ምንአደርግ ዘንድ ትወዳለህ?" ሲል ጌታን ጠየቀ፡፡ ጌታ ኢየሱስም ተነሥቶ ወደ

ደማስቆ ከተማ እንዲገባ በዚያም ሊያደርገው የሚገባውን ነገር የሚነግሩት ሰዎች እንደሚያገኝ ነገረው፡፡ ሳውልም ከወደቀበት ሲነሣ ማየት ተሳነው፤ አብረውት የነበሩት ሰዎች እየመሩት ወደ ከተማው ገባ፡፡ ሦስት ቀን እና ሦስት ሌሊት ሳያይ፣ ሳይበላና ሳይጠጣ ኖረ፡፡ ሳውል ኃጢአቱን ተረድቶ ክርስቶስን በማመኑ ጌታ ሐናንያን ወደ ሳውል ላከው፡፡ ሐናንያ ሳውል ወዳለበት ቤት መጥቶ እጁን ጫነበት ሳውልንም እንዲህ ሲል ተናገረው "ወንድሜ ሳውል ሆይ፡- ጌታ እርሱም በመጣህበት መንገድ የታየህ ኢየሱስ ነው ደግሞ ታይ ዘንድና መንፈስ ቅዱስ ይሞላብህ ዘንድ ላከኝ" አለው፡፡ ወዲያውም በዚያው ቅጽበት እንደ ቅርፊት ያለ ከሳውል ዓይን ውስጥ ወደቀ ያን ጊዜም ሳውል አየ ተነሥቶም በሐናንያ እጅ ተመጠቀ፤ ምግብም በልቶ በረታ፡፡ ሐናንያ ጳውሎስ ለወንጌል አገልግሎት በተለይም ወንጌልን ለሕዝብ ለመስበክ ጌታ እንደጠራው ለሳውል ነገረው፡፡ ጳውሎስም የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል ለማገልገል ከዚያን ዕለት ጀምሮ ተለየ፡፡

## ማጠቃለያ፡-

ልጆች በዚህ ትምህርት ሳውል ለአይሁድ ሃይማኖት እና ለአባቶች ወግ በመቅናት በክርስቶስ ባመኑት ላይ ክፉ ነገርን ያደርግ እና ክርስቲያኖችን ያሳድድ እንደነበር ነገር ግን በደማስቆ መንገድ ላይ ጌታ ኢየሱስ እንደለወጠው እና ወደ ትክክለኛው መንገድ እንዳመጣው አይታችኋል፡፡ ስለዚህ እናንተም ለሃይማኖት ያላችሁን ቅንዓት ልትመራምሩ እና ልትፈትሹ ያስፈልጋችኋል፡፡ ሳውል ቅንዓቱ አይሁድን እና ሊቀ ካሕናቱን ለማስደሰት ነበር እንጂ እግዚአብሔርን በአገልግሎቱ ለማስደሰት አልነበረም፡፡ በዚህ የተነሣ ስሜቱን እና የራሱን ፍላጎት ሲያገለግል ክርስቲያኖችን ሲያሳድድ እና የቅዱሳትን ደም ሲያፈስ በደማስቆ መንገድ ላይ ጌታ ተገልጦ የእግዚአብሔር ፈቃድ ምን እንደሆነ ገለጠለት፡፡ የእግዚአብሔር ፈቃድ ፍቅር ነው እንጂ ጥላቻ አይደለም፡፡ እግዚአብሔር በሰዎች ላይ ክፉ ስለአደረግን እና የሌሎችን ደም ስለ አፈሰስን፣ ስማቸውን በሐሜት ስለአጠፋን . . . ወዘተ አይደሰትም፡፡ እግዚአብሔር በአገልግሎታችን የሚደሰተው ፈቃዱን ስናደርግ ነው፡፡ ፍቃዱ ደግሞ እርስ በርሳችን እንድንከባበር፣ እንድንዋደድ፣ ከሁሉ ጋር በሰላም እንድንኖር እና ጠላቶቻችንን እንኳን እንድናፈቅር በጎ ነገርም እንድናደርግላቸው መሆኑ በቅዱሳት መጻሕፍት ተገልጧል፡፡ ስለዚህ ልጆች የእግዚአብሔር ፈቃድ ምን እንደሆነ አውቃችሁ ሰውን ወይም የራሳችሁን ፈቃድ ሳይሆን የእግዚአብሔርን ፈቃድ አገልግሉ፡፡

www.zeorthodox.org

### *ጥያቄዎች፡-*

1. ሳውል የተወለደበት ከተማ ምን ይባል ነበር?
2. ሳውል ስንት ዜግነት ነበረው?
3. የሳውል መምህር ማን ይባል ነበር?
4. ሳውል ከትምህርት ሌላ ምን ሞያ ነበረው?
5. ሳውል ክርስቲያኖችን ያሳድድ የነበረው ለምንድነው?
6. ሳውል እንዴት ክርስትናን ተቀበለ?

## ተግባር፡-

- መምህሩ በዚህ ታሪክ አማካኝነት ልጆች እውነተኛ የሃይማኖት ቅንዓት እንዲኖራቸው ያድርግ፡፡
- ልጆች እግዚአብሔርን በአገልግሎታችሁ እንዴት ደስ ማሰኘት እንደምትችሉ ተወያዩ፡፡
- ልጆች ከሳውል ታሪክ ምን እንደተማራችሁ ለመምህራችሁ እና ለጓደኞቻችሁ ግለጹ፡፡

www.zeorthodox.org

# ቅዱስ ጳውሎስ በልስጥራ ተአምር አደረገ

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ሐዋርያው ጳውሎስ በትምህርቱ እና በተአምራቱ ጣዖት አምላኪዎችን እንዴት ለክርስቶስ እንደማረከ መማር፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "ወደ ሕያው እግዚአብሔር ዘወር ትሉ ዘንድ ወንጌልን እንሰብካለን፡፡" ሐዋ. ፲፬÷፲፭

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ሐዋ. ፲፬÷፰-፲፰፣ ፫÷፲፩-፲፫፣ ዮሐ. ፭÷፴፮-፵፯፣ ፯÷፲፮-፲፱

## መግቢያ፡-

- መምህሩ ያለፈውን ሳምንት ትምህርት ይከልስላቸው፡፡
- ልጆች ሐዋርያት ተአምራት ያደርጉ የነበረው ለምንድ ነው?
- በወንጌል አገልግሎት መከበር እና ከፍ ብሎ መታየት ያለበት ማን ነው?
- ልጆች በክርስቶስ የሚያምኑትን እንዴት ለመማረክ ታስባላችሁ?

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

ልጆች ባለፈው ሳምንት ትምህርት ሳውል ምንም እንኳን የሙሴን ሕግና የአባቶችን ወግ ከታላቁ መምህር ከገማልያል ቢማርም ትክክለኛ መረዳት እና እውነተኛ የሃይማኖት ቅንዓት ስላልነበረው በክርስቶስ ያመኑትን እንዴት የሳድድ እንደነበረ በኋላ ግን በደማስቆ መንገድ ጌታ እንዴት እንዳስተካከለውና ወደ እውነተኛው መንገድ እንደመራው ተምራችሁ ነበር፡፡ ዛሬ በዚህ ትምህርት ሳውል ክርስቶስን ከተቀበለ በኋላ ስለ አገለገለው የወንጌል አገልግሎት፣ በተለይ በልስጥራ ስለ አደረገው ተአምር እንማራለን፡፡

www.zeorthodox.org

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በክርስቶስ አምኖ ከተጠመቀ በኋላ የመጀመሪያ የወንጌል አገልግሎቱን የጀመረው በደማስቆ ከተማ በአይሁድ ምኩራቦች ስለ ክርስቶስ በመመስከር ነበር፡፡ ከዚህ በኋላ ሐዋርያው ጳውሎስ በተለያዩ የአሕዛብ ሀገራት በመዳዝ ወንጌልን እየዘራ ሰበከ፣ ብዙዎችንም በክርስቶስ እንዲያምኑ አደረገ፡፡ በተለይ ሦስት ታላላቅ ጉዞዎችን ወደ አሕዛብ ሀገር በማድረግ ወንጌልን በስፋት በማገልገሉ ብዙ ሕዝብ በክርስቶስ ስለ አመነ ቤተ ክርስቲያን በአሕዛብ ሀገር እየሰፋች ሔደች፡፡ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ክርስትናን በአሕዛብ ሀገር ለማስፋፋት እጅግ ከባድ ዋጋ የከፈለ ሲሆን የተለያዩ ተአምራትን በክርስቶስ ስም በማድረግ እና መልእክታትን በመጻፍ ክርስቲያኖች በእምነት እና በምግባር እንዲጸኑ አድርጓል፡፡ ሐዋርያው ጳውሎስ ወንጌልን ከሰበከባቸው ከተሞች መካከል ልስጥራ አንዷ ነበረች፡፡ በልስጥራ ከተማ ሐዋርያው ጳውሎስ እና በርናባስ ከተወለደበት ዕለት ጀምሮ ሽባ የሆነ እና መራመድ የማይችል ሰውን በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ስለ አዳኑት እና ሰውዬው በልስጥራ ሰዎች ፊት ቆሞ መራመድ ስለቻለ የልስጥራ ሰዎች በተደረገው ተአምር እጅግ ተደንቀው ሐዋርያው ጳውሎስን እና በርናባስን በሰው አምሳል የተገለጡ አማልክት ናቸው ብለው አመኑ፡፡ ወዲያውም ጳውሎስን ሄርሜን በርናባስን ደግሞ ድያ ብለው ያመልኳቸው በነበሩት ጣዖታት ስም ጠሯቸው፡፡

የልስጥራ ሰዎች እና የጣዖታት ካህናት የነበሩት በአንድነት ሆነው ለመሥዋዕት የሚሆኑ በሬዎችን አዘጋጅተው ጳውሎስን እና በርናባስን ሊያመልኳቸው ተነሡ፡፡ ነገር ግን ሐዋርያው ጳውሎስ እና በርናባስ ይህን ሲሰሙ "እኛ እንደ እናንተ ሰዎች ነን ከዚህም ከንቱ ነገር ሰማይንና ምድርን ባሕርንም በእነርሱ ያለውንም ወደ ፈጠረ ወደ ሕያው እግዚአብሔር ዘወር ትሉ ዘንድ ወንጌልን እንሰብካለን" ብለው ሰበኳቸው፡፡ ጳውሎስና በርናባስ የእግዚአብሔር አገልጋዮች እንጂ አማልክት እንዳልሆኑ አስረግጠው በመናገራቸው እና መራመድ የማይችለው ሰው በእግዚአብሔር ኃይል እንደ ዳነ ሲመሰክሩላቸው የልስጥራ ሰዎች ጣዖታትን ማምለክ ትተው በእግዚአብሔር አመኑ፡፡

## ማጠቃለያ፡-

ልጆች ሐዋርያው ጳውሎስ የቀደመውን ክፉ ሥራውን ትቶ ወንጌልን እንዴት በአሕዛብ ሀገር በብዙ ዋጋ እንዳገለገለ በአንድ ወቅት በልስጥራ ከተማ ከበርናባስ ጋር ሆነው በሽባው ሰው መዳን ምክንያት የልስጥራ ሰዎች ጣዖትን ማምለክ ትተው በእግዚአብሔር እንዳመኑ በዚህ ትምህርት አውቃችኋል፡፡ ስለዚህ ወንጌልን የምናገለግለው ሰዎች ወደ እግዚአብሔር እንዲመለሱ እንጂ እኛን እንዲከተሉ እንዳልሆነ አውቃችሁ በአገልግሎታችሁ ሁሉ እግዚአብሔር እንዲከብር እና የእርሱ ኃይል እንዲታይ ትጉ፡፡

### *ጥያቄዎች፡-*

1. በልስጥራ ከተማ ከሐዋርያው ጳውሎስ ጋር ያገለገለው ሰው ማን ነበር?
2. በልስጥራ ከተማ የተደረገው ተአምር ምን ነበር?
3. የልስጥራ ሰዎች በተደረገው ተአምር ምን አደረጉ?
4. ለሕዝቡ አድናቆት የእነ ጳውሎስ ምላሽ ምን ነበር?
5. ከሐዋርያው ጳውሎስና በርናባስ አገልግሎት ምን ተማራችሁ?

## ተግባር፡-

- መምህሩ ልጆች በመንፈሳዊ ሕይወታቸው እና በአገልግሎታቸው ሌሎችን እንዴት ወደክርስቶስ ማቅረብ እንደሚችሉ ያወያያቸው፡፡
- ልጆች በመንፈሳዊ ሕይወቱ(ቷ) እና በአገልግሎቱ(ቷ) የማረኩአችሁን ሰዎች ለጓደኞቻችሁ አካፍሉ፡፡

www.zeorthodox.org

# ገድለ ሰማዕታት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ሰማዕታት በእምነት፣ በምግባር እና በጽናት ይህን ክፉ ዓለም ድል መንሳት እንደቻሉ ማስተማር፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "እነርሱም ከበጉ ደም የተነሣ ድል ነሱት ነፍሳቸውንም እስከ ሞት ድረስ አልወደዱም፡፡" ራእ. ፲፪÷፲፩

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ይሁዳ. ቁ.፫-፬፣ ፩ዮሐ. ፪÷፲፫-፲፯፣ ፩ጴጥ. ፫÷፮-፲፩፣ ፪ ጢሞ. ፬÷፮-፰፣ ኤፌ. ፮÷፲-፳፣ ሐዋ ፳፪÷፳

## መግቢያ፡-

- መምህሩ ያለፈውን ሳምንት ትምህርት ይከልስላቸው፡፡
- ልጆች ገድል ምንድነው? ሰማዕታትስ እነማን ናቸው? የምታውቁትን ለመምህራችሁ ተናገሩ፡፡
- ልጆች ሰይጣንን ድል የምትነሱት በምንድነው?

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

ልጆች ሀገራችን ኢትዮጵያ በየዓመቱ የአርበኞችን ቀን በታላቅ ድምቀት እንደምታከብር ታውቃላችሁ፡፡ በከተማችን በአዲስ አበባ የአርበኞች ሕንፃ፣ ሐውልት እና ትምህርት ቤት ይገኛሉ፡፡ አርበኛ ማለት ስለ ሀገሩ እና ሰለ ነፃነቱ እስከ ሞት ድረስ የታገለ ማለት ሲሆን የክርስትና አርበኛ ደግሞ ስለ እግዚአብሔር መንግሥት ብሎ ዓለምን እና ምኞቱን የተወ በእምነት ዲያብሎስን ድል የነሳ ማለት ነው፡፡ ሰማዕት ማለትም የእውነት ምስክር ማለት ሲሆን በሃይማኖቱ ምክንያት የተገደለ ሰው ሰማዕት ይባላል፡፡ ገድል የሚለው ቃል ደግሞ ለእግዚአብሔር መንግሥት ብሎ ፈቃድን፣ ክፉ ፍላጎትንና በአጠቃላይ ኃጢአትን መተውን ያመለክታል፡፡ ስለዚህ ገድለ ሰማዕታት የሚለው ሐረግ ስለ ወንጌል ብለው ሕይወታቸውን አሳልፈው የሰጡ ሰማዕታትን፣ ቅዱሳንን፣ መነኮሳትን፣ ባሕታውያንን፣ ደናግላንን . . . ወዘተ በአጠቃላይ አምነታቸውን ጠብቀው፣ በወንጌል መሠረት ላይ ቆመው፣ መስቀሉን ተሸክመው፣ የቅድስናን ሥራ እየሠሩ የዓለምን እና የዲያብሎስን ምኞት ያለ ደም መፍሰስ በእምነት፣ በጸሎትና በጾም ስለ ሃይማኖታቸው የሚጋደሉ ምእመናንን የሚያጠቃልል ሐረግ ነው፡፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በቀራንዮ በመስቀል ላይ የከበረ ደሙን በማፍሰሱ ሰማዕታት የእርሱን ፈለግ በመከተል ስለ እውነት፣ ስለ ወንጌልና ስለመንግሥተ ሰማያት ሕይወታቸውን እንዲሰዉ ኃይል ሆኗቸዋል፡፡ በዚህ የተነሣ በማያምኑ ሰዎች ፊት ስለ ወንጌል ሲመሰክሩ የሞቱትን የወንጌል አርበኞች ሰማዕታት ቤተ ክርስቲያን ታከብራቸዋለች፡፡

www.zeorthodox.org

ሰማዕታት በበጉ በኢየሱስ ክርስቶስ ደም አማካኝነት እና የወንጌሉን ቃል በሕይወታቸው በተግባር በመኖር በመንፈሳዊ ሕይወት ዲያብሎስን እና ምኞቱን እንዴት ድል ማድረግ እንደሚቻል አሳይተውናል፡፡ ሰማዕታት የእውነት ምስክሮች፣ የክፉ ሰዎችን

ዛቻ እና ማስፈራራት ሳይሰቀቁ በድፍረት ስለክርስቶስ የመሰከሩ በአጠቃላይ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ክርስትናን በእምነት፣ በፍቅር እና በትሕትና የኖሩ ናቸው፡፡ አባቶቻችን ቅዱሳን እና ሰማዕታት በዚህ ምድር ብዙ መከራ ተቀብለዋል፡፡ ታስረዋል፣ ተደብድበዋል፣ ተሰደዋል፣ ተርበዋል፣ ተገድለዋል . . . ወዘተ፡፡ ይህ ሁሉ የሆነባቸው እግዚአብሔርን በማመናቸው እና የእውነት ምስክሮች ስለነበሩ ነው፡፡ ነገር ግን የእግዚብሔር ሰላም እና ፍቅሩ በልባቸው ያለ ማቋረጥ ይፈስ ስለነበረ ደስ እያላቸው መከራን ሳይፈሩ ይቀበሉ ነበር፡፡ ቅዱስ እስጢፋኖስ፣ ቅዱስ ጳውሎስ፣ ቅዱስ ጴጥሮስ፣ ቅዱስ ያዕቆብ፣ ቅዱስ ዮሐንስ መጥምቅ፣ ቅዱስ ጊዮርጊስ . . . ወዘተ. ቤተ ክርስቲያን ሁል ጊዜ የምታስታውሳቸው ሰማዕታት ናቸው፡፡

## ማጠቃለያ፡-

ልጆች በዚህ ትምህርት ሰማዕታት የዓለምን እና የዲያብሎስን ምኞት በእምነት ድል በመንሳት እንዴት የእምነት ምስክሮች እንደሆኑ ተምራችኋል፡፡ ስለዚህ እናንተም በዚህ ዘመን ራሳችሁን ከሐሰት፣ ከኃጢአት፣ ከበደል እና ከክፉ ተግባራት በመጠበቅ እና እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ በእምነት እና በምግባር በሃይማኖት በመጽናት የሰማዕታትን ፈለግ መከተል ትችላላችሁ፡፡

### ጥያቄዎች፡-

1. ልጆች በዚህ ዘመን ሰማዕት መሆን ይቻላል እንዴት?
2. ቤተ ክርስቲያን ሰማዕታትን የምታከብረው ለምንድ ነው?
3. ገድለ ሰማዕታት ስለ እነማን ይናገራል?
4. ሰማዕታት የዲያብሎስን ምኞት ድል መንሳት የቻሉት እንዴት ነው?
5. ከዚህ ትምህርት ምን ተማራችሁ?

## ተግባር፡-

- መምህሩ ልጆች የበለጠ ስለ ሰማዕታተ ጥልቅ ግንዘቤ እንዲኖራቸው የሰማዕታትን ገድል የሚናገህረ መጻሕፍትን እንደያነቡ አበራታታቸው
- ልጆች የሰማዕታትን በዓል እንዴት እንደምታከበሩ ለመምህሩና ለጓደኞቻችሁ ንገሩ፡፡

www.zeorthodox.org

# ቅዱስ ጳውሎስ በድንጋይ ተወገረ

**የትህምህርቱ ዓላማ፡-** ሐዋርያት ለወንጌል አገልግሎት የከፈሉትን ዋጋ ከሐዋርያው ጳውሎስ እና ከበርናባስ ሕይወት መማር፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** “ስለ አንተ ቀኑን ሁሉ እንገደላለን” ሮሜ. ፰÷፴፮

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ሐዋ. ፲፬÷፲፱-፳፣ መዝ. ፳፪(፳፫)÷፩፣ ሮሜ. ፰÷፴፯-፴፱

## መግቢያ፡-

- መምህሩ ያለፈውን ሳምንት ትምህርት ይከልስላቸው፡፡
- ልጆች ወንጌልን መስበክ ዋጋ እንደሚያስከፍል ታውቃላችሁ? እንዴት?
- ከክርስቶስ ፍቅር ሊለያችሁ የሚችል ነገር አለ? ካለ ምን?
- ክርስቲያን በመሆናችሁ ከሰዎች የደረሰባችሁን ተቃውሞ ለመምህራችሁ እና ለጓኞቻችሁ ንገሩ፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

ባለፈው ሳምንት ሐዋርያው ጳውሎስና በርናባስ በልስጥራ ከእናቱ ማሕፀን ጀምሮ መራመድ የማይችል ሆኖ የተወለደውን ሰው በእግዚአብሔር ኃይል እንዳዳኑ በዚህም የተነሣ የልስጥራ ሰዎች ጣዖት ማምለክን ትተው ወደ እግዚአብሔር ዘወር እንዳሉ ተምራችሁ ነበር፡፡ ነገር ግን አይሁድ በልስጥራ አቅራቢያ ከሚገኙ ከተሞች መጥተው የልስጥራ ሰዎችን አባበሉ፡፡ ከቀናት በፊት ጳውሎስን ሊያመልኩ ይፈልጉ የነበሩ ሁሉ በአይሁድ ምክር እና ማባበል ተለውጠው የጳውሎስ ጠላቶች ሆኑ፡፡ ጳውሎስን በድንጋይ ወገሩት፣ የሞተም መስሎአቸው ከከተማ ውጪ ጥለውት ተመለሱ፡፡ ወደ ከተማ ተመልሰውም የጳውሎስን ሞት መናገር ጀመሩ፡፡ ነገር ግን በርናባስ እና ሌሎች ደቀመዛሙርት ወደ ጳውሎስ ሲመጡ ጳውሎስ ከዚያ ሁሉ የድንጋይ ድብደባ በኋላ ተነሥቶ ወደ ከተማ ገባ፡፡ በማግስቱም ከበርናባስ ጋር ወደ ደርቤን ከተማ ተጉዞ ወንጌልን እየሰበከ ብዙ ደቀመዛሙርትን አፈራ፡፡ በክርስቶስ ያመኑትን ደቀመዛሙርት በሃይማኖት እንዲጸኑ እና ወደ እግዚአብሔር መንግሥት በብዙ መከራ እንደሚገቡ እያስተማሩ ወደ ልስጥራ እና በአካባቢው ወዳሉ ከተሞች ተመለሱ፡፡

www.zeorthodox.org

## ማጠቃለያ፡-

ልጆች ሐዋርያው ጳውሎስ እውነትን በመመስከሩ የደረሰበትን መከራ እና እንግልት ከዚህ ትምህርት አስተውላችኋል፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ ወንጌልን በተለያዩ ሰዎች ፊት ቆሞ በመመስከሩ ብዙ መከራ ቢቀበልም አገልግሎቱን ግን አላቋረጠም፣ እንዳውም ከክርስቶስ ፍቅር ማንም ሊለየው እንደማይችል ስለሚያምን በትጋት ያገለግል ነበር፡፡ እናንተም እንደ ጳውሎስ ከሰዎች የሚደርሱባችሁን ክፉ ነገሮች ሳትፈሩ የክርስቶስን ወንጌል ስበኩ፣ በክርስቶስ ፍቅር ሊለያችሁ የሚችል አንዳች ኃይል እንደ ሌለ በማመን በአገልግሎታችሁ ትጉ፡፡ ዛሬም ቢሆን እንደ ልስጥራ ሰዎች በክፉዎች ምክር ተታለው በእግዚአብሔር አገልጋዮች ላይ የሐሰት ወሬ የሚያሰራጩ የስድብን ቃል የሚናገሩ እና ለድብድብ እንዲሁም ድንጋይ ለመወርወር የሚሰለፉ ብዙዎች ስለሆኑ እንደዚህ ካለው ክፉ ነገር ራሳችሁን ጠብቃችሁ የእውነት ምስክር እና አገልጋይ ሁኑ፡፡

### *ጥያቄዎች፡-*

1. የልስጥራ ሰዎች ሐዋርያው ጳውሎስን ለምን ጠሉት?
2. የልስጥራ ሰዎች ጳውሎስን ምን አደረጉበት?
3. ሐዋርያው ጳውሎስ ወደ ደርቤን ከማን ጋር ሐደ?
4. በደርቤን የነበሩትን ደቀመዛሙርት ምን አስተማራቸው?
5. ከጳውሎስ አገልግሎት ምን ተማራችሁ?

## ተግባር፡-

- መምህሩ ልጆች በመንፈሳዊ አገልግሎት የሚገጥማቸውን ፈተና እንዴት ድል አድርገው አገልግሎታቸውን መቀጠል እንደሚችሉ ያወያያቸው፡፡
- ልጆች ከዚህ ቀደም በመንፈሳዊ አገልግሎታችሁ የገጠማችሁን ፈተና እና እግዚአብሔር እንዴት እንዳሳለፉችሁ ለጓደኞቻችሁ መስከሩ፡፡

www.zeorthodox.org

# የነቢዩ ዳንኤል ጾም

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ልጆች በጾም ራሳቸውን መግዛት እንዲለማመዱ እና የጾምን በረከት እንደ ነቢዩ ዳንኤል እንዲካፈሉ ማስተማር፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** “ሙሽራው ከእነርሱ የሚወሰድበት ጊዜ ይመጣል፣ በዚያ ጊዜም ይጾማሉ፡፡” ማቴ. ፱÷፲፭

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ት/ዳን ምዕራፍ አንድ እና ሁለት፣ ማቴ. ፱÷፲፬-፲፯፣ ፮÷፲፮-፲፰፣ ት/ኢሳ. ፶፰÷፲፩-፲፪፣ ኤር. ፲፬÷፲፩-፲፪

## መግቢያ፡-

- መምህሩ ያለፈውን ሳምንት ትምህርት ይከልስላቸው፡፡
- ልጆች ጾም ምንድ ነው?
- ጾም ለምን ይጠቅማል?
- በመጽሐፍ ቅዱስ በጾም የተጠቀሙ ሰዎችን ታስታውሳላችሁ?

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

ነቢዩ ዳንኤል የስሙ ትርጉም “እግዚአብሔር ፈራጅ ነው” ማለት ሲሆን ብዙ ጸጋ እና ችሎታ የነበረው እስራኤላዊ ወጣት ነበር፡፡ የባቢሎኑ ንጉሥ ናቡከደነፆር እስራኤልን ሲማርክ ዳንኤልን እና ሌሎችን ወደ ባቢሎን ወሰዳቸው፡፡ ዳንኤል በባቢሎን ሀገር የከለዳውያንን ትምህርትና ቋንቋ ተማረ፡፡ ናቡከደነፆር ከኢየሩሳሌም ማርኮ ካመጣቸው ወጣቶች መካከል ጥበብና ማስተዋል ያላባቸውን መልከ መልካም የሆኑትን መርጦ በቤተመንግሥቱ ጥሩ ምግብ እና መጠጥ እየተመገቡ ለሦስት ዓመታት እንዲቆዩ ከተመረጡት መካከል ከይሁዳ የመጡ ዳንኤል፣ አናንያ፣ ሚሳኤልና አዛርያ ነበሩ፡፡ አስፋኔዝ የተባለው የንጉሡ አገልጋይ ለዳንኤል ብልጣስር፣ ለአናንያ ሲድራቅ፣ ለሚሳኤልም ሚሳቅ፣ ለአዛርያም አብድናጎ የሚባሉ ስሞችን አወጣላቸው፡፡ ዳንኤል እና ሦስቱ ወጣቶች የእስራኤልን አምላክ እግዚአብሔርን ያመልኩ ስለበር በቤተመንግሥቱ ምግብ እንዳይረክሱ አስበው ምግቡን አንበላም አሉ፡፡

www.zeorthodox.org

ለዐሥር ቀናት የቤተመንግሥቱን ምግብ ሳይመገቡ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ እያከበሩ ጾሙ፡፡ ይመገቡ የነበረው ጥራጥሬ እና አታክልት ብቻ ነበር፡፡ በዚህ ሁኔታቸው አስፋኔዝ ሲጨነቅ ሰንብቶ ስነለነበር የዳንኤልን እና የሦስቱ ወጣቶች ፊታቸው አምሮ ሰውነታቸውም ወፍሮ ሲመለከት እጅግ በጣም ተደነቀ፡፡ በንጉሡ አማካኝነት በተደረገው ምርጫም ዳንኤልና ሶሶቱ ወጣቶች ውድድሩን አሸንፈው ለመመረጥ ቻሉ፡፡ ከሌሎቹ ይልቅ በጥበብና በማስተዋል እጅግ የበለጡ ስለነበሩ ንጉሥ ናቡከደነፆር በጣም ደስ

ተሰኝቶ በቤተመንግሥቱ ሾማቸው፡፡ ከዚህ በኋላ ነቢዩ ዳንኤል ናቡከደነፆርን፣ ብልጣሶርን፣ ዳርዮስን እና ቂሮስንም በማስተማር፣ ሕልምን በመፍታት እና መጻሕፍትን በመተርጎም አገለገለ፡፡ በዚህም ምክንያት ዳንኤል በማያምኑ ሰዎች መካከል እየዋለ ታማኙን ጌታ በኑሮው እና በአገልግሎቱ አስከበረ፡፡ ዳንኤል በመልካም አካሔዱ በባቢሎን የታወቀ ሰው ሆነ፡፡ ነገር ግን ከአምላኩ ሕግ በቀር ሰበብ ስለአልተገኘበት ክፉዎች በዳንኤል ጸጋ እና አገልግሎት ቀንተው ጣዖታቸውን ባለማምለኩ ወደ አንበሳ ጉድጓድ ተጣሉ፡፡ እግዚአብሔርም ዳንኤል በአንበሳ እንዳይበላ የአናብስቱን አፍ በኃይሉ ዘጋ፣ ዳንኤልንም አዳነው፡፡ ብዙ ሰዎች በዳንኤል አምላክ አመኑ፡፡ ዳንኤል ለእግዚአብሔር ሕዝብ እየጸለየ ብዙ ራእይ አየ፡፡ ነቢዩ ዳንኤል ያያቸው ሕልሞችና ራእዮች ብዙ ምስጢር ያለባቸው ሲሆን ዋና የትንቢቱ ዓላማ ግን በመጨረሻ እግዚአብሔርና ሕዝቡ እንደሚያሸንፉ መግለጥ ነው፡፡

## ማጠቃለያ፡-

ነቢዩ ዳንኤልና ሦስቱ ወጣቶች በምርኮ በባቢሎን ሀገር ሲኖሩ የእስራኤልን አምላክ አልዘነጉም ነበር፡፡ ይልቁን በጾም እና በጸሎት እያመኑ እግዚአብሔርን በማያምኑት መካከል ያመልኩ ነበር፡፡ በዚህም እግዚአብሔር በሰው ሀገር ሞገስ ሆናቸው፡፡ በብዙ በረከት በጥበብና በማስተዋል ስለባረካቸው ከብዙዎች መካከል ተመርጠው በቤተመንግሥት ተሾሙ፡፡ ልጆች እናንተም ከእነዚህ ወጣቶች በመማር የአባቶቻችሁን አምላክ ሳትዘነጉ በጾምና በጸሎት ራሳችሁን እየገዛችሁ እግዚአብሔርን በማያምኑ ሰዎች ፊት አስከበሩ፡፡ እግዚአብሔር ትምህርታችሁን እንዲገልጥላችሁ፣ በጤና፣ በጥበብና በማስተዋል ባርኮ ከፍ ያለ ደረጃ እንዲያደርሳችሁ እንደ እነ ዳንኤል በልጅነት እና በወጣትነት ዘመናችሁ እንደ እግዚአብሔር ሕግ እና ፈቃድ መኖርን ተለማመዱ፡፡

### *ጥያቄዎች፡-*

1. ኢየሩሳሌም ድረስ ወርዶ እስራኤልን የማረከ የባቢሎን ንጉሥ ማን ይባላል?
2. ዳንኤል እና ሦስቱ ወጣቶች የቤተመንግሥቱን ምግብ ያልተመገቡት ለምንድ ነው?
3. እነ ዳንኤል በጾም እና በጸሎት በመትጋታቸው ምን አገኙ?
4. ዳንኤል ወደ አንበሳ ጉድጓድ የተጣለው በምን ምክንያት ነበር?

## ተግባር፡-

www.zeorthodox.org

- ልጆች በቤተ ክርስቲያን የሚታወቁትን ሰባቱን አጽዋማት በዝርዝር ለመምህራችሁ እና ለጓደኞቻችሁ ንገሩ፡፡

# ጸሎተ ሐና

**የትምህርቱ ዓላማ፦** በጸሎት የምንለምነውን እና የምንጠይቀውን ከእግዚአብሔር እንደምንቀበል ከሐና ጸሎት መማር፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፦** “ልቤ በእግዚአብሔር ጸና” ፩ሳሙ. ፪÷፩

**ተጨማሪ ምንባባት፦** ፩ሳሙ. ፩፣፪፣ ማቴ. ፯÷፯-፲፪፣ ሉቃ. ፲፩÷፱-፲፫

## መግቢያ፦

- መምህሩ ያለፈውን ሳምንት ትምህርት ይከልስላቸው፡፡
- ልጆች እግዚአብሔር እንዲሰጣችሁ የምትፈልጉት ነገር ምንድነው?
- በቀን ስንት ጊዜ እንደምትጸልዩ ለመምህራችሁ ንገሩ፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት፦

መጽሐፍ ቅዱስ ሰዎች ከእግዚአብሔር ጋር የነበራቸውን የጠበቀ ግንኙነት የሚተርክ መጽሐፍ ነው፡፡ በዚህ ትምህርት ከእግዚአብሔር ጋር የጠበቀ የጸሎት ሕይወት ስለነበራት ሴት እንማራለን፡፡ በተራራማው በኤፍሬም ሀገር የሚኖር ሕልቃና የሚባል አንድ ሰው ነበር፡፡ ሕልቃና ሁለት ሚስቶች ነበሩት፡፡ የአንደኛዋ ሚስቱ ስም ሐና ሲሆን የሁለተኛዋ ደግሞ ፍናና ይባል ነበር፡፡ ሕልቃና ከፍናና ብዙ ልጆችን ወልዶ ነበር ነገር ግን ሐና መካን ስለነበረች ልጅ አልነበራትም፡፡ ሕልቃና ቤተሰቡን ሁሉ ይዞ በሴሎ ለሠራዊት ጌታ ለእግዚአብሔር ይሰግድ እና መሥዋዕትን ይሰዋ ዘንድ በየዓመቱ ከከተማው ይወጣ ነበር፡፡ ፍናና ከሕልቅና ልጆች ስለወለደች ልጅ የሌላትን ሐና በጣም ታስቆጣት እና ታበሳጫት ነበር፡፡ በዚህ የተነሣ ብዙ ጊዜ ሐና ታለቅስና ታማርር ስለነበር ምግብ አትቀምስም ነበር፡፡

www.zeorthodox.org

አንድ ቀን እንደተለመደው ለእግዚአብሔር ሊሰግድ መሥዋዕትም ሊያቀርብ ሕልቃና ቤተሰቡን ሁሉ ይዞ ወደ ሴሎ ወደ እግዚአብሔር ቤተመቅደስ ወጣ፡፡ በሴሎ ለእግዚአብሔር ከሰገዱ በኋላ እየበሉ እና እየጠጡ ሲደሰቱ ፍናና ግን እንደለመደችው ሐናን በነገር ማበሳጨት እና ማስመረር ጀመረች፡፡ ሐናም በዚህ በጣም ልቧ ስለአዘነ በጣም አለቀሰች፡፡ ባሏ ሕልቃና ሊያጽናናት እንኳ ቢሞክር ሐና በጣም አዝና ስለነበር ወደ ቤተመቅደሱ ብቻዋን ሔዳ እግዚአብሔር ወንድ ልጅ እንዲሰጣት፣ እርሱ የሚሰጣትን ልጅ መልሳ ለእግዚአብሔር እንደምትሰጥ ስለት ተሳለች፤ እያለቀሰች ጸሎቷን ወደ እግዚአብሔር አቀረበች፡፡ ሐና ስትጸልይ ካህኑ ዔሊ በቤተመቅደስ ደጃፍ ተቀምጦ ይመለከት ስለነበር ሐና የወይን ጠጅ ጠጥታ ሰክራ የምትለፈልፍ ስለመሰለው “የወይን ጠጅሽን ከአንቺ አርቂው” ሲል ሐናን ተናገራት፡፡ ሐና ግን የወይን ጠጅ ጠጥታ የምትለፈልፍ ሴት ሳትሆን እግዚአብሔር ልጅ እንዲሰጣት

በጸሎት እየጠየቀች እንደሆነ ለእግዚአብሔር ካህን አስረዳችው፡፡ የእግዚአብሔር ካህን ዔሊ "የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር የለመንሽውን ልመና ይስጥሽ" ብሎ ባረካት፡፡ ሐናም ደስተኛ ሆና ወደ ቤቷ ተመለሰች፡፡ እግዚአብሔርም ሐናን አሰባት፤ የመውለጃዋ ወራት ካለፈ በኋላ ሐና ወንድ ልጅ ወለደች፡፡ እግዚአብሔር ልመናዬን ሰምቷል ስትል ስሙን ሳሙኤል ብላ ጠራችው፡፡

ሐናም ሕፃኑ ሳሙኤልን ጡት እያጠባች ጡት እስኪተው ድረስ በቤትዋ ተቀመጠች፡፡ ሕፃኑ ሳሙኤል ጡት መጥባት በተወ ጊዜ ሳሙኤልን እና ለመሥዋዕት የሚሆኑ ነገሮችን ይዛ ወደ እግዚአብሔር ቤት መጣች፡፡ ሕፃኑ ሳሙኤልን በእግዚአብሔር ካህን በዔሊ ፊት ይዛ ቆማ "ወደ እግዚአብሔር ለመጸለይ በዚህ በአንተ ዘንድ ቆማ የነበረች ሴት እኔ ነኝ ስለዚህ ሕፃን ጸለይሁ እግዚአብሔርም የለመንሁትን ልመናዬን ሰጥቶኛል እኔም ደግሞ ለእግዚአብሔር ሰጥቼዋለሁ ዕድሜውን ሁሉ ለእግዚአብሔር የተሰጠ ይሆናል" ብላ ሳሙኤልን ለካህኑ ዔሊ ሰጠችው፡፡ እግዚአብሔር ልመናዋን ስለተቀበለ፣ የተዘጋውን ማሕፀኗን ስለከፈተላት እና የጠላቶቿን አፍ ወንድ ልጅ ሰጥቶ ስለዘጋ በጸሎት እና በምስጋና እንዲሁም በውዳሴ ሐና ፈጣሪዋን አመሰገነች፡፡ ሳሙኤል ከዚያን ቀን ጀምሮ ከካህኑ ዔሊ ጋር በቤተመቅደስ መኖር ጀመረ፡፡ ካህኑ ዔሊ ሳሙኤልን በእግዚአብሔር ቃል እየኮተኮተ በቤተመቅደስ ያሳድገው ይንከባከበውም ነበር፡፡

## ማጠቃለያ፡-

ልጆች ከሐና ታሪክ ጸሎት ከልብ በሚመነጭ ፍቅር ወደ እግዚአብሔር የሚቀርብ ልመና እንጂ ተራ ንግግር እንዳልሆነ ተምራችኋል፡፡ ሐና በፍጹም ልብዋ አምና ጥያቄዋን እግዚአብሔር መመለስ እንደሚቻለው እርግጠኛ ሆና በማቅረብዋ ከእግዚአብሔር የምትፈልገውን በጸሎት መቀበል ቻለች፡፡ ልጆች እናንተም በተሰበረ ልብ፣ በጽኑ እምነት ከእግዚአብሔር የምትፈልጉትን መቀበል እንደምትችሉ አምናችሁ ጸልዩ፡፡

### *ጥያቄዎች፡-*

1. በተራራማው በኤፍሬም ሀገር ይኖር የነበረው ሰው ማን ይባላል?
2. ሕልቃና ስንት ሚስት ነበረው? እነማን ይባላሉ?
3. ሕልቃና ለሠራዊት ጌታ ለእግዚአብሔር ለመስገድ እና መሥዋዕት ለማቅረብ የሚወጣበት ስፍራ ምን ይባላል?
4. ሐና ታለቅስና ትማረር የነበረው ለምንድነው?
5. የሐና ጸሎት ምን ነበር ምን ብላ ተሳለች?
6. በቤተመቅደስ ደጃፍ ተቀምጦ የነበረው ካህን ማን ነበር?
7. ከሕልቃና እና ከቤተሰቡ ታሪክ ምን ተማራችሁ?

www.zeorthodox.org

## ተግባር፡-

- መምህሩ ልጆች ከሐና ታሪክ ጋር የሚመሳሰል ታሪክ ያላቸውን ሴቶች እንዲያስታውሱ ያድርጋቸው፡፡
- ልጆች ከቤተሰቦቻችሁ ጋር እግዚአብሔር ታመልካላችሁ? የት እና እንዴት እንደምታመልኩ ለጓደኞቻችሁ ተናገሩ፡፡
- እስከ አሁን ድረስ በጸሎት ከእግዚአብሔር ዘንድ የተቀበላችሁት ነገር ምንድነው?ስለተደረገላችሁ ነገር ታመሰግናላችሁ?

www.zeorthodox.org

# የረዓብ እምነት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** እግዚአብሔር በእመነት ሆነን የምንሠራውን በጎ ሥራ ሁሉ ዋጋ እንደሚከፍለን ከረዓብ ሕይወት መማር፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "አምላካችሁ እግዚአብሔር በላይ በሰማይ በታችም በምድር እርሱ አምላክ ነው" መ.ኢያ.፪÷፲፩

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** መ.ኢ.ያ. ፪÷፩-፳፩፣ ፮÷፳፪-፳፫፣ ዕብ. ፲፩÷፩-፫፣ ሮሜ. ፲÷፲፫-፲፯፡፡

## መግቢያ፡-

- መምህሩ ያለፈውን ሳምንት ትምህርት ይከልስላቸው፡፡
- ልጆች እምነት ምንድነው?
- ለሰዎች በጎ ነገር የምታደርጉት ለምንድነው?
- ለሰዎች በጎ ሥራ በመሥራታችሁ እግዚአብሔር ለእናንተ ያደረገው መልካም ነገር ምንድነው?

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

እስራኤል ከግብጽ ከወጡ በኋላ ከሙሴ ቀጥሎ ሕዝቡን ወደ ከነዓን ሲመራ የነበረው ሰው ኢያሱ ነበር፡፡ ከአርባ ዓመት የበረሐ ጉዞ በኋላ ወደ ተስፋይቱ ምድር ለመግባት ሲቃረቡ በፊታቸው ያላቸውን የኢያሪኮን ከተማ እንዲሰልሉ ኢያሱ ሁለት ሰዎችን ላከ፡፡ ረዓብ በኢያሪኮ ከተማ መግቢያ ትኖር የነበረች ጋለሞታ ሴት ናት፡፡ የእስራኤልን ሰላዮች በቤቷ ውስጥ አስተናገደች፡፡ የኢያሪኮ ንጉሥ ወደ ቤቷ የገቡትን ሰላዮች እንድታወጣ ቢያዛትም እርሷ ግን ሁለቱን ሰላዮች በቤቷ ደብቃ ከሞት አዳነቻቸው፡፡ ረዓብ እስራኤል በእግዚአብሔር ኃይል ከነዓንን እንደሚወርሱ ያመነች ሴት በመሆኗ እምነቷን ለሁለቱ ሰላዮች መስክራ እስራኤል ኢያሪኮን በያዙ ጊዜ ለእርሷ እና ሌበተሰቦቿ ቸርነት እንዲያደርጉላት ለመነቻቸው፡፡ ሁለቱም ሰላዮች ረዓብ ምስጢራቸውን የምትጠብቅ ከሆነ እግዚአብሔር ኢያሪኮን አሳልፎ ሲሰጣቸው በጎ ነገር እንደሚያደርጉላት ቃል ገቡላት፡፡ ከዚህ በኋላ ረዓብ ሁለቱን ሰላዮች በቤቷ መስኮት በኩል በገመድ ወደ ከተማው አወረደቻቸው፡፡ አሳዳጆቻቸው እስኪመለሱም ድረስ ሦስት ቀን በከተማው ውስጥ ተሰውረው እንዲቆዩ ከዚያም ወደ ኢያሱ ተመልሰው እንዲሔዱ ነገረቻቸው፡፡ ሁለቱ ሰላዮች የረዓብን ምክር ተቀብለው እነርሱን ያወረደችበትን ቀይ ገመድ መስኮቷ ላይ እንድታስረው ነግረዋት መንገዳቸውን ቀጠሉ፡፡ ሰላዮቹ ወደ ኢያሱ ተመልሰው በኢያሪኮ የነበራቸውን ቆይታ በተለይ ረዓብ የምትባል ሴት ያደረገችላቸውን በጎ ነገር ለኢያሱ ነገሩት፡፡ እስራኤል በኢያሱ መሪነት እና በእግዚአብሔር ኃይል ኢያሪኮን ያዙ፡፡ ኢያሱም ረዓብን እና ቤተሰቦቿን እንዳይገደሉ ለሁለቱ ሰላዮች ትእዛዝ ሰጠ፣ ከእስራኤልም ጋር እንዲኖሩ

www.zeorthodox.org

ፈቀደላቸው፡፡ በመጨረሻም ረዓብ ከሁለቱ ሰላዮች አንዱን ሰሎሞንን አግብታ የንጉሥ ዳዊትን ቅድመ አያት ቦኤዝን ወለደች፤ ከእርሷም ዘር ክርስቶስ ተወለደ፡፡ (ማቴ. ፩÷፫፣ ዕብ. ፲፩÷፴፩)

## ማጠቃለያ፡-

ረዓብ እግዚአብሔር ሁሉን ቻይ መሆኑን አምና ለሁለቱ ሰላዮች በእምነት በጎ ነገር በማድረጓ እግዚአብሔር እርሷን እና ቤተሰቧን እንዴት ከሞት እንዳዳነ በኋላም የዳዊትን ቅድመ አያት ወልዳ ከክርስቶስ የዘር ሐረግ ጋር እንደተቆጠረች በዚህ ትምህርት አውቃችኋል፡፡ ስለዚህ ልጆች እናንተም እንደ ረዓብ በፍጹም ልባችሁና ነፍሳችሁ በእግዚአብሔር በመታመን ለሰዎች በጎ ነገር አድርጉ፡፡ እግዚአብሔር በእምነት ሆናችሁ ያደረጋችሁትን መልካም ነገር ሁሉ በብዙ እጥፍ በረከት ይመልስላችኋል፡፡

### *ጥያቄዎች፡-*

1. ኢያሱ ወደ ኢያሪኮ የላካቸው ሰላዮች እነማን ነበሩ?
2. በኢያሪኮ ሰላዮቹን ተቀብላ በቤቷ ያስተናገደች ሴት ማን ትባላለች?
3. ረዓብ በእግዚአብሔር እንዴት ልታምን ቻለች?
4. ሁለት ሰላዮች ከኢያሪኮ ንጉሥ እንዴት ሊያመልጡ ቻሉ?
5. እስራኤል ኢያሪኮን ሲይዙ ለረዓብ ምን አደረጉላት?
6. ከረዓብ ታሪክ ምን ተማራችሁ?

## ተግባር፡-

- መምህሩ ልጆች እምነት እና ምግባር የማይነጣጠሉ እንደሆነ እንዲያውቁ ያድርጋቸው፡፡
- ልጆች በአካባቢያችሁ ላሉ ሰዎች እንዴት በጎ ነገር ማድረግ እንደምትችሉ ከጓኞቻችሁ ጋር ተወያዩ፡፡
- እግዚአብሔር በሰዎች ያደረገላችሁን በጎ ነገር ለማስታወስ ሞክሩ፡፡ ስለተደረገላችሁም ነገር አመስጋኞች ሁኑ፡፡

www.zeorthodox.org

# የንጉሥ ሕዝቅያስ ጸሎት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** በዕንባ እና በለቅሶ የሚቀርብ ጸሎት ታላቅ ኃይል እንዳለው ለልጆች ማስተማር፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** “ጸሎትህን ሰምቻለው ዕንባህንም አይቻለሁ እነሆነ እፈውስሃለሁ፡፡” ፪ነገ. ፳÷፭

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ፪ነገ. ፳÷፩-፳፩፣ ፲፰ እና ፲፱፣ ያዕ.፭÷፲፫-፲፭

## መግቢያ፡-

- መምህሩ ያለፈውን ሳምንት ትምህርት ይከልስላቸው፡፡
- ልጆች የጸሎት ዓይነቶችን ለይታችሁ ታውቃላችሁ?
- ለታመመ ሰው ጸሎት አድርጋችሁ ታውቃላችሁ? እንዴት?

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

ሕዝቅያስ በነቢዩ ኢሳያስ ዘመን ከ፯፻፲፮-፮፻፹፯(716-687) ቅድመ ልደት ክርስቶስ የነገሠ ዐሥራ ሦስተኛው የይሁዳ ንጉሥ ነው፡፡ ሕዝቅያስ የስሙ ትርጉም እግዚአብሔር ኃይሌ ነው ማለት ሲሆን እጅግ ደግ እና መልካም ሰው ስለነበር ከይሁዳ ነገሥታት ሁሉ እርሱን የሚመስል የለም ተብሎ ተመስክሮለታል፡፡ ንጉሥ ሕዝቅያስ ከሠራቸው በጎ ሥራዎች መካከል ባዕድ አምልኮትን አጥፍቶአል፣ ሙሴ የሠራውን የናሱን እባብ ሰባብሯል፣ የጣዖት አምልኮን አጥፍቶአል፣ የእግዚብሔርን ቤተመቅደስም አድሷል፡፡ በዘመኑ የቤተ ክህነቱ እና የቤተመንግሥቱ አስተዳደር መልካም ስለነበረ እግዚአብሔር ደስ ተሰኝቶ ሕዝቅያስ ጠላቶቹን ድል እንዲያደርግ ረዳው፡፡ በአንድ ወቅት ንጉሥ ሕዝቅያስ ለሞት በሚያደርስ ክፉ ሕመም ታሞ አልጋ ይዞ ተኛ፡፡

ንጉሡ በሕመም አልጋ ላይ ሆኖ ወደ ነቢዩ ኢሳያስ መልእክተኞችን ልኮ የእግዚአብሔር ፈቃድ ምን እንደሆነ እንዲነግረው ጠየቀ፡፡ ነቢዩ ኢሳያስ ንጉሥ ሕዝቂያስን ሊጠይቀው ወደ ቤተመንግሥት መጣ “ትሞታለህ እንጂ በሕይወት አትኖርምና ቤትህን አስተካክል” ሲል ለንጉሡ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ነገረው፡፡ ንጉሡ ይህን እንደሰማ ፊቱን ወደ ግድግዳው አዙሮ እግዚአብሔር እንዲምረው ጸለየ፣ በጣምም አለቀሰ፡፡ እግዚአብሔርም የሕዝቅያስን ጸሎት ሰማ፡፡ ነቢዩ ኢሳያስን እንደገና ወደ ንጉሥ ሕዝቅያስ እንዲህ የሚል መልእክት ይዞ እንዲሔድ አደረገው፡- “ጸሎትህን ሰምቻለሁ ዕንባህንም አይቻለሁ እንሆ እፈውስሃለሁ በሦስተኛውም ቀን ወደ እግዚአብሔር ቤት ትወጣለህ በዕድሜህም ላይ ዐሥራ አምስት ዓመት እጨምራለሁ፡፡”

ንጉሥ ሕዝቅያስ ይህን መልእክት ሲሰማ መንፈሱ ታደሰ፣ ጉልበቱም በረታ እርሱ እና ቤተሰቦቹ ሁሉ እግዚአብሔር ስለ አጽናናቸው በጣም ደስ አላቸው፤ ከዚህ በኋላ ኢሳይያስ አገልጋዮቹ የበለስ ጥፍጥፍ እንዲያመጡለት አዘዛቸው፣ እነርሱም ኢሳይያስ እንዳዘዛቸው የበለስ ጥፍጥፍ አምጥተው በንጉሡ እባጭ ላይ አደረጉለት፡፡ ንጉሡ ሕዝቅያስም ከሕመሙና ከስቃዩ ተፈወሰ፡፡ ንጉሡ እና በዚያ የነበሩት ሁሉ እግዚአብሔርን አመሰገኑ፡፡

www.zeorthodox.org

## ማጠቃለያ፡-

ንጉሥ ሕዝቅያስ በፍጹም ልቡ በእግዚአብሔር ይታመን ስለነበር የሞቱን ዜና ሰምቶ ተሰፋ ሳይቆርጥ እግዚአብሔር እንዲምረው በጸሎት በማልቀሱ እግዚአብሔር ምሕረት አድርጎለታል፤ ዕድሜም ተጨምሮለታል፡፡ ስለዚህ ልጆች እናንተም ከአቅማችሁ በላይ የሆነ ችግር ሲገጥማችሁ እግዚአብሔር ከችግራችሁ በላይ እንደሆነ በፍጹም ልባችሁ በመታመን በጸሎት እና በዕንባ ልመናችሁን ወደ እግዚአብሔር አስታውቁ እንጂ በምንም ነገር አትጨነቁ፡፡ እግዚአብሔር እንደ ንጉሥ ሕዝቅያስ ችግራችሁን ይፈታል ከሥቃያችሁ ያሳርፋችኋል፡፡

### *ጥያቄዎች፡-*

1. ሕዝቅያስ ማለት የስሙ ትርጉም ምን ማለት ነው?
2. ንጉሥ ሕዝቅያስ በነገሠበት ዘመን ይኖር የነበረ ነቢይ ማን ይባላል?
3. ንጉሥ ሕዝቅያስ በዘመኑ ምን አደረገ?
4. ንጉሥ ሕዝቅያስ በሕመም አልጋ ላይ ሆኖ ምን ሰማ?
5. እግዚአብሔር የንጉሡን ጸሎት የመለሰው እንዴት ነበር?
6. ከዚህ ታሪክ ምን ተማራችሁ?

## ተግባር፡-

- መምህሩ ልጆች የታመመ ሰው ሲጠይቁ ጸሎት እንዲያደርጉ እና ሕሙማንን እንዲያጽናኑ ይንገራቸው፡፡
- ልጆች ታማችሁ ታውቃላችሁ? የምታውቁ ከሆነ ለጓደኞቻችሁ በሕመም አልጋ ላይ ሆናችሁ ይሰማችሁ የነበረውን ስሜት እና ምን ታደርጉ እንደነበር ልምዳችሁን አካፍሏቸው፡፡
- የታመሙ ሰዎች ከእናንተ ምን እንደሚፈልጉ እና እንዴት ልታገለግሏቸው እንደምትችሉ ተወያዩበት፡፡

www.zeorthodox.org

# ካህኑ ዔሊና ልጆቹ

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** **ልጆች ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔር** መቅደስ እንደሆነች ተገንዝበው የመቅደሱን ጌታ እንዲያከብሩ ማስተማር ነው፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** “**ቤቱ ለአሕዛብ ሁሉ የጸሎት** ቤት ትባላለች” ማር. ፲፩÷፲፯

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ማር. ፲፩÷፲፭-፲፱፣ ፩ሳሙ. ፩-፮፣ ዮሐ. ፪÷፲፫-፳፭፣ መዝ. ፲፬(፲፭)÷፩-፭

## መግቢያ፡-

- መምህሩ ያለፈውን ሳምንት ትምህርት ይከልስላቸው፡፡
- ልጆች የእግዚአብሔር ቤት የት ይገኛል?
- የእግዚአብሔር ቤት ምን ተብሎ ይጠራል?
- በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ ለመኖር የሚያስፈልጉ ነገሮች ምንድናቸው?
- በእግዚአብሔር ቤት የተከለከሉ ነገሮች ምንድናቸው?

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

በመጽሐፈ ሳሙኤል ቀዳማዊ የእግዚአብሔር ካህን ዔሊና አገልግሎቱ እንዲሁም ስለ ሁለት ልጆች ታሪክ ተጽፎ እናነባለን፡፡ ካህኑ ዔሊ አፍኒን እና ፊንሐስ የሚባሉ ሁለት ልጆች ነበሩት፡፡ ዔሊ በሊቀ ካህንነትና በፈራጅነት እስራኤልን ያገለገለ ሲሆን በዘመኑ የእግዚአብሔር የመቅደሱ ድንኳን በሴሎ ተተክሎ ስለነበር ከሁለት ልጆቹ ጋር እግዚአብሔር እና ሕዝቡን በሴሎ በእግዚአብሔር መቅደስ ያገለግል ነበር፡፡ ነገር ግን የካህኑ ዔሊ ልጆች አፍኒን እና ፊንሐስ በእግዚአብሔር መቅደስ ካህን ሆነው እያገለገሉ የመቅደሱን ጌታ አያከብሩም ነበር፡፡ እግዚአብሔርንም ባለመፍራታቸው ከሕጉ እና ከመንገዱ ወጥተው ኃጢአትን ይሠሩ እና ይበድሉ ነበር፡፡

www.zeorthodox.org

አባታቸው ካህኑ ዔሊ ልጆቹ በእግዚአብሔር እና በሕዝቡ ፊት ኃጢአትን ሲሠሩ በዓይኑ እየተመለከተ ልጆቹን በሚገባ ባለ መምከሩ እና ባለመስገዱ በደካማነቱ ተነቀፈ፡፡ (፩ሳሙ. ፪÷፲፩-፳፮) እግዚአብሔር ካህኑ ዔሊና ልጆቹ መቅደሱን ስለ አላከበሩ በእነርሱ ላይ ተቆጣ፡፡ በመቅድስ ያገለግል ለነበረው ለብላቴናው ሳሙኤል ካህኑ ዔሊን እና ልጆቹን እግዚአብሔር በከባድ ፍርድ እንደሚቀጣቸው ነገረው፡፡ እግዚአብሔርም ለሳሙኤል የተናገረው ነገር ተፈጸመ፡፡ አፍኒን እና ፊንሐስ እስራኤል ከፍልስጥኤማውያን ጋር ሲዋጉ በጦር ሜዳ ላይ በጠላት እጅ ተመትተው ሞቱ፡፡ በውጊያውም ላይ የእግዚአብሔር ታቦት ተማረከች፡፡ አንድ ሰውም ለካህኑ ዔሊ ሁለቱም ልጆቹ በጦር ሜዳ እንደሞቱ፣ የእግዚአብሔርም ታቦት እንደተማረከች ሲነግረው በድንጋጤ ከመቀመጫው ወድቆ ሞተ፡፡ ክህነትም ከዔሊ ቤት ተወስዶ ለሌላ በተሰጠ ጊዜ እግዚአብሔር የፈረደበት ፍርድ ተግባራዊ

ሆነ፡፡ (፩ነገ. ፪÷፳፮-፳፯÷፴፫)

## ማጠቃለያ፡-

ልጆች ከዚህ ትምህርት ካህኑ ዔሊና ልጆቹ በእግዚአብሔር ቤተመቅደስ እየኖሩ የመቅደሱን ጌታ እግዚአብሔርን ባለማክበራቸው የእግዚአብሔርን ፍርድ እንዴት እንደተቀበሉ አይታችኋል፡፡ ስለዚህ እናንተም በቤተ ክርስቲያን ስትኖሩ የቤተ ክርስቲያንን ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን አክብሩ፣ ለመቅደሱ ጌታ በፍቅር እና በትሕትና እየታዘዛችሁ አገልግሉ፡፡ በመቅደሱ ክፉ ነገሮችን ከሚያደርጉት ጋር አትተባበሩ፡፡

### ጥያቄዎች፡-

1. በሴሎ በእግዚአብሔር መቅደስ ከልጆቹ ጋር ያገለግል የነበረው ካህን ማን ይባላል?
2. የካህኑ ዔሊ ልጆች ማን ይባላሉ?
3. የዔሊ ልጆች ነውር እና ኃጢአት ምን ነበር?
4. እግዚአብሔር መቅደሱን ባላከበሩት ላይ እንደሚፈርድ ለማን ተናገረ?
5. በካህኑ ዔሊ እና በልጆቹ ላይ የእግዚአብሔር ፍርድ ምን ነበር?
6. ከዚህ ታሪክ ምን ተማራችሁ?

## ተግባር፡-

- መምህሩ ልጆች በቤተ ክርስቲያን ሊኖራቸው ስለሚገባቸው ሥነ-ሥርዓት ይንገራቸው፡፡
- ልጆች በቤተ ክርስቲያን የመቅደሱን ጌታ እንዴት እንደምታመልኩ እርስ በርሳችሁ ተወያዩ፡፡
- ልጆች በቤተ ክርስቲያን ዘረኝነት፣ ስርቆት፣ ዝሙት፣ ሐሜት፣ አድማ እና ክፍፍል እንዲሁም ጥልን እና ክርክርን ሰዎች የሚያደርጉት ለምን እንደሆነ ከመምህራችሁ ጋር በመወያየት ከእነዚህ ክፉ ተግባራት ራሳችሁን ጠብቁ፡፡
- ልጆች በእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ በቤተ ክርስቲያን ምን በመስሥት እግዚአብሔርን ደስ ለማሰኘት አስባችኋል? ለመምህራችሁ እና ለጓደኞቻችሁ ንገሩ፡፡

www.zeorthodox.org

# መጥምቁ ዮሐንስ

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ቅዱስ ዮሐንስ እንዴት ለአልግሎት እንደተጠራ መማር፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "ብዙዎችን ወደ ጌታ ወደ አምላካቸው ይመልሳል" ሉቃ ፩÷፲፮

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ሉቃ. ፩÷፫-፳፫፣ ፩÷፴፱-፹፣ ዮሐ. ፩÷፮-፰፣ ፩÷፲፱-፴፰

## መግቢያ፡-

- መምህሩ ያለፈውን ሳምንት ትምህርት ይከልስላቸው፡፡
- ልጆች እግዚአብሔር ሰዎችን ለአገልግሎት የሚመርጠው እንዴት ነው?
- እግዚአብሔር ለአገልግሎት እንደመረጣችሁ በምን ታውቃላችሁ?
- የእውነተኛ አገልጋይ መለያዎች ምንድን ናቸው?

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

እግዚአብሔር በተለያየ ጊዜና ዘመን ሰዎችን ለመንፈሳዊ አገልግሎት መርጧል፡፡ ዛሬ በዚህ ትምህርት መጥምቁ ዮሐንስ እግዚአብሔርን እና ሕዝቡን ለማገልገል እንዴት እንደተመረጠ እንማራለን፡፡ ዮሐንስ የስሙ ትርጉም "እግዚኢብሔር ጸጋ ነው" ማለት ሲሆን በዚህ ስም ብዙ ሰዎች በመጽሐፍ ቅዱስ ተጠርተውበታል፡፡ በይሁዳ ንጉሥ በሄድሮስ ዘመን እግዚአብሔርን እና ሕዝቡን በቤተመቅደስ የሚያገለግል ዘካርያስ የሚባል ካህን ነበር፡፡ ካህኑ ዘካርያስ ከሚስቱ ኤልሳቤጥ ጋር በጌታ ትእዛዝና ሕግጋት ሁሉ ያለ ነቀፋ እየሄደ ነገር ግን ሚስቱ መካን ስለነበረች ልጅ አልነበራቸውም፡፡ ለብዙ ጊዜ እግዚአብሔር ልጅ እንዲሰጣቸው ይጸልዩ ነበር፣ ግን ልጅ ሳይወልዱ ሁለቱም አረጁ፡፡ ከዕለታት አንድ ቀን ካህኑ ዘካርያስ በቤተመቅደስ ዕጣን እያጠነ በእግዚአብሔር ፊት ሲያገለግል የእግዚአብሔር መልአክ በዕጣኑ መሠዊያ ቀኝ ቆሞ ታየው፡፡

www.zeorthodox.org

መልአኩም "ዘካርያስ ሆይ ጸሎትህ ተሰምቷልና አትፍራ ሚስትህ ኤልሳቤጥም ወንድ ልጅ ትዋልድልሃለች ስሙንም ዮሐንስ ትለዋለህ" ብሎ የምሥራቹን ለዘካርያስ ነገረው፡፡ ዮሐንስ በጌታ ፊት ታላቅ እንደሚሆን፣ በእናቱ ማሕጸን መንፈስ ቅዱስ እንደሚሞላበት እና ብዙ ሰዎችን ለጌታ እንደሚያሰናዳ መልአኩ ለዘካርያስ ጨምሮ ነገረው፡፡ ካህኑ ዘካርያስ እና ሚስቱ ኤልሳቤጥ በጣም አርጅተው ስለነበር የጸሎቱን መልስ በእምነት መቀበል አቃተው፡፡ መልአኩም "እኔ በእግዚአብሔር ፊት የምቆመው ገብርኤል ነኝ፣ እንድናገርህም ይህችንም የምሥራች እንድሰብክልህ ተልኬ ነበር እነሆም በጊዜው የሚፈጸመውን ቃሌን ስላላመንህ ይህ ነገር እስከሆን ድረስ ድዳ ትሆናለህ መናገርም አትችልም" ብሎ ዘካርያስን ተናገረው፡፡

እግዚአብሔር በቃሉ የታመነ ስለሆነ አሮጊቷ ኤልሳቤጥ በእርጅናዋ ወንድ ልጅ ፀነሰች፡ ካህኑ ዘካርያስ ዮሐንስ እስኪወለድ

ድረስ ድዳ ሆኖ ኖረ፡፡ ቅዱስ ገብርኤል እንዳለው ዮሐንስ በእናቱ ማሕፀን ሆኖ ኤልሳቤጥ የማርያምን ሰላምታ በሰማች ጊዜ መንፈስ ቅዱስን ተሞልቶ በደስታ ዘለለ፡፡ ኤልሳቤጥ የመውለጃዋ ጊዜ ሲደርስ ወንድ ልጅ ወለደች፡፡ ጎረቤቶችዋም ከዘመዶችዋ ጋር ሆነው እግዚአብሔርን አመሰገኑ፣ ከኤልሳቤጥም ጋር ደስ አላቸው፡፡ መልአኩ እንዳለው ስሙን ዮሐንስ ብለው ጠሩት፡፡ ያን ጊዜ ዘካርያስ አፉ ተከፈተ፣ አንደበቱም ተፈታ እግዚአብሔርንም እየባረከ ስለ ዮሐንስ ትንቢት ተናገረ፡፡ ዮሐንስ የልዑል ነቢዩ፣ የጌታን መንገድ የሚጠርግ እና በጌታ ፊት የሚሄድ አገልጋይ እንደሆነ ካህኑ ዘካርያስ መንፈስ ቅዱስን ተሞልቶ ስለ ዮሐንስ የወደፊት አገልግሎት ተናገረ፡፡ ሕፃኑም አደገ በመንፈስም ጠነከረ ለእስራኤልም እስከታየበት ቀን ድረስ በምድረ በዳ ኖረ፡፡

## ማጠቃለያ፡-

ልጆች እግዚአብሔር መጥምቁ ዮሐንስን ገና ሳይወለድ ለአገልግሎት እንደመረጠው በዚህ ትምህርት አውቃችኋል፡፡ እግዚአብሔር በቃሉ የታመነ አምላክ እንደሆነ እና ፈቃድን ሰው ሊከለከል እንደማይችል በካህኑ ዘካርያስ እና በኤልሳቤጥ ሕይወት አስተውላችኋል፡፡ እግዚአብሔር እንደ ዮሐንስ ሌሎችን ለማገልገል እና ወደ ጌታ ለመመለስ በቃሉ ሲናገራችሁ አሜን ብላችሁ አገልግሉ፡፡

### *ጥያቄዎች፡-*

1. ዮሐንስ ማለት ምን ማለት ነው?
2. ዮሐንስ የማን ልጅ ነው?
3. እግዚአብሔር ዮሐንስን ለአገልግሎት የመረጠው መቼ ነበር?
4. ካህኑ ዘካርያስ የመልአኩን ቃል አሜን ብሎ መቀበል ያቃተው ለምንድነው?
5. ዘካርያስ እስከ መቼ ድረስ ድዳ ሆኖ ኖረ?
6. ዮሐንስ ለአገልግሎት እስኪወጣ ድረስ የት ኖረ?

## ተግባር፡-

- *መምህሩ ልጆች በእግዚአብሔር የተወደደ አገልግሎት እንዴት ማገልገል እንደሚችሉ ያወያያቸው፡፡*

www.zeorthodox.org

# እስራኤል ከነዓንን ሰለሉ

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** እግዚአብሔር በቃሉ ታማኝ ስለሆነ የሰጠንን ተስፋ በእምነት መቀበልን መማር፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "በምትሄድበት ሁሉ አምላክህ እግዚአብሔር ከአንተ ጋር ነውና ጽና፣ አይዞህ፣ አትፍራ፣ አትደንግጥ" ኢያሱ ፩÷፱

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ዘኁ. ፲፫ እና ፲፬፣ ሮሜ. ፬÷፲፯-፳፩፣ ዕብ. ፲፩÷፳፫-፴፩

## መግቢያ፡-

- መምህሩ ያለፈውን ሳምንት ትምህርት ይከልስላቸው፡፡
- ልጆች ስለ ስለላ ምን ያህል ታውቃላችሁ?
- ስለላ ለምን ይጠቅማል?
- ልጆች በሕይወታችሁ ተስፋ የምታደርጉት ነገር ምንድነው?

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

እስራኤል ከግብጽ ወጥተው በምድረበዳ ሳሉ እግዚአብሔር ለሕዝቡ የሚያወርሳቸውን ምድር ከነዓንን የሚሰልሉ ሰዎችን መርጠህ ላክ አለው፡፡ እስራኤል ዐሥራ ሁለት ነገድ ስለ ነበሩ ከእያንዳንዱ ነገድ አንድ አንድ ሰው መርጦ ማርና ወተት የምታፈሰውን የተስፋይቱን ምድር ሰልለው እንዲመጡ ከፋራን ምድረ በዳ ሙሴ ላካቸው፡፡ ዐሥራ ሁለቱ ሰላዮች የተስፋይቱን ምድር ከነዓንን ለአርባ ቀናት በደንብ ከሰለሉ በኋላ ወደ ሙሴ እና ወደ ሕዝቡ ተመልሰው ያዩትን እና የታዘቡትን ተናገሩ፤ የምድሪቱንም ፍሬ ለሕዝቡ አሳዩ፡፡ ሰላዮች እግዚአብሔር ስለምድሪቱ መልካምነት የተናገረው እውነት እንደሆነ ከመሰከሩ በኋላ ነገር ግን በውስጧ የሚኖሩት ሰዎች ኃያላን እና ረጃጅም እንደሆኑ እየተናገሩ ሕዝቡን አሸበሩ፡፡

www.zeorthodox.org

ካሌብ እና ኢያሱ ግን ሕዝቡን በሙሴ ፊት ዝም አሰኝተው አጽናኑ "ማሸነፍ እንችላለንና እንውጣ እንውረሰው" ብለው ሕዝቡን አበራቱ፡፡ ሕዝቡ ግን የዐሥሩን ሰላዮች ወሬ ሰምተው አምነው ስለነበር የኢያሱን እና የካሌብን ቃል ሳይቀበሉ ቀሩ፡፡ በሙሴና በአሮን ላይ አጉረመረሙ፡፡ እግዚአብሔር በሰይፍ እንሞት ዘንድ ለምን ከግብጽ አወጣን ሲሉ በእግዚአብሔር ላይም አጉረመረሙ፡ ወደ ግብጽ ለመመለስም አስበው አለቃ ለመምረጥ ተስማሙ፡፡ ሙሴና አሮን በሕዝቡ ፊት በግንባራቸው መሬት ላይ ወድቀው መጸለይ ጀመሩ፡፡

ኢያሱና ካሌብ ሕዝቡ በእግዚአብሔር ላይ ማጉረምረማቸው አመጽ እንደሆነ ወደ ግብጽ ለመመለስ ማሰባቸውም ስህተት

መሆኑን በድፍረት ተናገሩ፡፡ ሕዝቡ ግን በድንጋይ ሊወግሯቸው ሲማከሩ የእግዚአብሔር ክብር በመገናኛው ድንኳን ተገልጣ እግዚአብሔር ሙሴን "ይህ ሕዝብ እስከ መቼ ይንቀኛል በፊቱስ ባደረግሁት ተአምራት ሁሉ እስከ መቼ አያምንብኝም" ሲል ተናገረው፡፡ ሕዝቡን እንደሚያጠፋቸው እና ለሙሴ ሌላ ሕዝብ እንደሚሰጠውም ጨምሮ ነገረው፡፡ ሙሴ "እባክህ እንደ ምሕረትህ ብዛት የዚህን ሕዝብ ኃጢአት ይቅር በል" ብሎ እግዚአብሔር ሕዝቡን እንዳያጠፋቸው ለመነ፡፡ እግዚአብሔርም የሙሴን ልመና ተቀብሎ ለሕዝቡ ይቅርታና ምሕረት አደረገላቸው፡፡

## ማጠቃለያ

በዚህ ታሪክ እስራኤል የአባቶቻቸው አምላክ ከግብጽ ባርነት በብዙ ተአምራት እና ኃይል በሙሴ አማካኝነት ነፃ ቢያወጣቸውም ደጋግመው በእግዚአብሔርና በአገልጋዮቹ ላይ ያጉረመርሙ ነበር፡፡ ሁል ጊዜ የእነርሱን ጉድለት እንጂ እግዚአብሔር ያደረገላቸውን ብዙ ነገር ማየት እና ማስተዋል ተስኖአቸው ስለነበር እግዚአብሔር የሰጣቸውን ተስፋ በእምነት መቀበልና እንደ ቃሉ መኖር አልቻሉም፡፡ እናንተ ግን እግዚአብሔር በቃሉ ታማኝ መሆኑን በፍጹም ልባችሁ አምናችሁ እንደ ተስፋ ቃሉ መኖርን ተለማመዱ፡፡ ስለ ጉድለታችሁ ሳይሆን እግዚአብሔር ስለ አደረገላችሁ በጎ ነገር አመስግኑ፡፡ በእግዚአብሔርና በአገልጋዮቹ ላይ እንድታጉረመርሙ ከሚያደርጓችሁ ሰዎች ራሳችሁን ጠብቁ፡፡

### *ጥያቄዎች፡-*

1. ሙሴ የተስፋይቱን ምድር እንዲሰልሉ ስንት ሰዎችን ላከ?
2. ሰላዮቹ ከስንት ቀናት በኋላ ተመለሱ?
3. ዐሥሩ ሰላዮች ሕዝቡን እንዴት አሸበሩ?
4. ሕዝቡን ያረጋጉት ሰላዮች እነማን ነበሩ?
5. እግዚአብሔር በሕዝቡ የተቆጣው ለምን ነበር?
6. ሕዝቡ ከእግዚአብሔር ቁጣ እንዴት አመለጡ?

www.zeorthodox.org

## ተግባር፡-

- ልጆች እግዚአብሔር ለክርስቲያኖች የሰጠውን ተስፋ ዘርዝሩ፡፡
- ከጓደኞቻችሁ ጋራ ከዚህ ታሪክ ምን እንደተማራችሁ ተወያዩ፡፡

# የቴሌቪዥንና የኢንተርኔት (የመረጃ መረብ) ተጽእኖ

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ልጆች ራሳቸውን ከቴሌቪዥንና ከመረጃ መረብ ተጽዕኖ እንዲጠብቁ ማስተማር

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "እንዴት እንደምትመላለሱ በጥንቃቄ ተጠበቁ" ኤፌ. ፭፥፲፭

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ኤፌ. ፭፥፲፭-፳፤ ፩ቆሮ. ፮፥፲፪፤ ዘሌ. ፲፩፥፵፬

## መግቢያ፡-

- መምህሩ ያለፈውን ሳምንት ትምህርት ይከልሱላችሁ፡፡
- ልጆች የቴሌቪዥን እና የኢንተርኔት (የመረጃ መረብ) አጠቃቀማችሁ ምን ይመስላል?
- በቀን ምን ያህል ጊዜ ታጠፋላችሁ?
- በእነዚህ ሚዲያዎች (የመገናኛ ብዙሃን) ከሚተላለፉት ፕሮግራሞች የትኛው ይማርካችኋል?
- ልጆች ቴሌቪዥን እና ኢንተርኔት (የመረጃ መረብ) በሕይወታችሁ ተጽዕኖ ያሳድራሉ ብላችሁ ታምናላችሁ? መልሳችሁ አዎን ከሆነ እንዴት?

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

ሃያ አንደኛው መቶ ክፍለ ዘመን የመረጃ ዘመን እየተባለ ዕለት ተዕለት ሲነገር እንሰማለን፡፡ በእያንዳንዳችን ቤት ቴሌቪዥን እና ኢንተርኔት (የመረጃ መረብ) በመኖሩ በየደቂቃው በዓለማችን ላይ እየሆነ ስላለው ነገር ከቤት ሳንወጣ መረጃ በማግኘታችን ይህ ዘመን የመረጃ ዘመን ሊባል ችሏል፡፡ በዚህ ትምህርት ልጆች ቴሌቪዥን እና ኢንተርኔት (የመረጃ መረብ) ጠቀሜታ እንዳላቸው ሁሉ ጉዳትም ስላላቸው እነዚህን ሚዲያዎች (የመገናኛ ብዙሃን) እንዴት መጠቀም እንዳለባቸው ግንዛቤ ለማስጨበጥ ተሞክሯል፡፡

www.zeorthodox.org

## የቴሌቪዥን እና የኢንተርኔት (የመረጃ መረብ) ጠቀሜታ)

ቴሌቪዥን እና ኢንተርኔት (የመረጃ መረብ) ለሰው ልጅ መረጃ በመስጠት እና በአንድ ጊዜ ብዙ ሰዎችን ማገልገል የሚችሉ ሆነው በመዘጋጀታቸው በዚህ ዘመን ተመራጭ የመረጃ ምንጭ ሆነው በማገልገል ላይ ይገኛሉ፡፡ በዚህ የተነሣ በዓለም ላይ ዕለት ዕለት ስለሚከሰቱ ነገሮች መረጃ በመስጠት፣ ዜናዎችን በማቅረብ፣ ስለ አየር ሁኔታ፣ ስለ ንግድ፣ ስለ ጤና በአጠቃላይ ትምህርታዊ እና ልዩ ልዩ አዝናኝ ፕሮግራሞችን በማቅረብ የሰዎችን ግንዛቤ እና ንቃት ኅሊና በማዳበር እንዲሁም በማስፋት ጠቀሜታቸው እጅግ የጎላ ሲሆን ቤተ ክርስቲያንም እነዚህን ሚዲያዎች (የመገናኛ ብዙሃን) በመጠቀም ክርስቲያኖችን የበለጠ ማገልገል ችላለች፡፡

## የቴሌቪዥን እና የኢንተርኔት (መረጃ መረብ) ተጽዕኖዎች

ከላይ በዝርዝር የእነዚህን ሚዲያዎች (የመገናኛ ብዙሃን) ጠቀሜታ የተመለከትን ሲሆን አሁን ደግሞ በየዕለት ተዕለት እንቅስቃሴዎቻችን የሚያሳድሩትን ተጽዕኖ በዝርዝር ለማየት እንሞክራለን፡፡ እነዚህ ሚዲያዎች (የመገናኛ ብዙሃን) በዕለት ተዕለት ኑሮአችን ከሚያሳድሩት ተጽዕኖ መካከል፡-

- ሴሰኝነትን እና አስገድዶ መድፈርን ያበረታታሉ፤
- አስቀያሚ ቃላት ተናግረን ሰዎችን እንድናስቀይም ያደርጉናል፤
- ግብረ ሰዶማዊነትን እና ውርጃን እንደ ጥሩ ተግባር ይሰብካሉ፤
- ለትምህርት ልንሰጠው የሚገባንን ጊዜ ይሻማሉ፤
- በአጠቃላይ በማንነታችን፣ በባህላችን፣ በሃይማኖታችን እና በአለባበሳችን ላይ የሚያሳድሩት ተጽዕኖ ይህ ነው የሚባል አይደለም፡፡

## ራሳችንን ከቴሌቪዥን እና ከኢንተርኔት (የመረጃ መረብ) ተጽዕኖ እንዴት መጠበቅ እንችላለን

- በእነዚህ ሚዲያዎች (የመገናኛ ብዙሃን) የሚተላለፉትን ፕሮግራሞች በመለየት እና በጎ የሆኑትን መርጦ በመጠቀም፤
- ከእነዚህ ሚዲያዎች (የመገናኛ ብዙሃን) የምናገኛቸውን መረጃዎች በሕይወታችን ከመተግበራችን በፊት በእግዚአብሔር ቃል በመመርመር፤
- ትርፍ ጊዜያችንን በአግባቡ በመጠቀም፤
- ራሳችንን በመግዛት፤
- እነዚህን ሚዲያዎች (የመገናኛ ብዙሃን) ለበጎ ነገር በመጠቀም . . . ወዘተ ራሳችንን ከቴሌቪዥን እና ከኢንተርኔት (የመረጃ መረብ) ተጽዕኖ ልንጠብቅ እንችላለን፡፡

www.zeorthodox.org

## ማጠቃለያ፦

ልጆች በዚህ ትምህርት ቴሌቪዥን እና ኢንተርኔት (የመረጃ መረብ) ከፍተኛ ጥቅም እንዳላቸው ሁሉ በሕይወታችን፣ በአስተሳሰባችን እና በጠባያችን ላይ ተጽዕኖ እንደሚያሳድሩም አውቃችኋል፡፡ ብዙ ጊዜ ሲጋራ፣ አልክሆል፣ ዝሙት፣ ጥልና ስርቆት እንደ ሥልጣኔ እና ጥሩ ነገር በእነዚህ ሚዲያዎች (የመገናኛ ብዙሃን) ስለሚቀነቀኑ ብዙ ልጆች ለተለያዩ ወንጀሎች እና ለሥነ-ምግባር ጉድለቶች የተጋለጡ ሲሆን ብዙዎቹ ሱሰኛ በመሆን ትምህርታቸውን ለማቋረጥ ተገደዋል፡፡ ስለዚህ እናንተም ቴሌቪዥን እና ኢንተርኔት (የመረጃ መረብ) ተገንዝባችሁ የምታዩትን፣ የምትሰሙትን እና የምታነቡትን በመምረጥ በጎ ነገር ለመሥራት ትጉ፡፡

## ተግባር፦

- መምህሩ ቴሌቪዥን እና ኢንተርኔት (የመረጃ መረብ) በቀላሉ እንዴት ተጽዕኖ ማሳደር እንደሚችሉ ተግባራዊ ምሳሌ በመስጠት ልጆች የበለጠ ግንዛቤያቸውን እንዲያሰፉ ያድርጋቸው፡፡
- ቴሌቪዥን እና ኢንተርኔት (የመረጃ መረብ) ለወንጀል፣ ለሕገወጥ ሥራ፣ ለሱሰኝነት እና ለሥነ-ምግባር ጉድለት እንዴት እንደሚያጋልጥ ልጆት እንዲወያዩበት ያድርጋቸው፡፡
- ረጅም ጊዜ ቴሌቪዥን በማየት እና ኢንተርኔት (የመረጃ መረብ) በመጠቀም ውድ ጊዜያቸውን የሚያባክኑ ልጆች የጊዜማ አጠቃቀማቸውን እንዲያስተካክሉ ያግዛቸው፡፡

www.zeorthodox.org

# የመጥምቁ ዮሐንስ አገልግሎት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** አገልግሎት የላከንን ማክበር እንደሆነ ከዮሐንስ አገልግሎት መማር፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "እርሱ ሊልቅ እኔ ግን ላንስ ያስፈልጋል" ዮሐ. ፫÷፴፡፡

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ዮሐ. ፩÷፮-፰፣ ፩÷፲፱-፴፯፣ ፫÷፳፫-፴፮፣ ፯÷፲፮-፲፱፣ ማቴ. ፫÷፩-፲፯፣ ፲፬÷፩-፲፪

## መግቢያ፡-

- መምህሩ ያለፈውን ሳምንት ትምህርት ይከልስላቸው፡፡
- አገልጋዮች ማስተማር ያለባቸው ስለ ማን ነው?
- አገልግሎት የሚያስከፍለው ዋጋ ምንድነው?

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

ልጆች ባለፈው ሳምንት መጥምቁ ዮሐንስ ገና ሳይወለድ ለአገልግሎት እንዴት እንደተመረጠ ተምረን ነበር፤ ዛሬ ደግሞ ስለ አገልግሎቱ እንማራለን፡፡ ዮሐንስ ከአደገ እና በመንፈስም ከጠነከረ በኋላ ለእስራኤል እስከ ታየበት ቀን ድረስ ራሱን ለአገልግሎት እያዘጋጀ በምድረ በዳ ኖረ፡፡ ምድረ በዳ ሰው የማይገኝበት ገለልተኛ ቦታን የሚያመለክት ሲሆን ዮሐንስ ናዝራዊ ሆኖ በምድረ በዳ ከኖረ በኋላ "መንግሥተ ሰማያት ቀርባለችና ንስሓ ግቡ" እያለ በይሁዳ ምድረ በዳ እየሰበከ መጣ፡፡ ዮሐንስ ልብሱ የግመል ጠጉር የነበረ ሲሆን በወገቡም ላይ ጠፍር ይታጠቅ ነበር፡፡ ምግቡም የበረሐ ማርና አንበጣ ነበር፡፡ ዮሐንስ ለኃጢአት ስርየት የንስሓን ጥምቀት በዮርዳኖስ ወንዝ አቅራቢያ ሰበከ፡፡ ሰዎች ከአይሁድ አገር ሁሉ እየመጡ ኃጢአታቸውንም እየተናዘዙ በዮርዳኖስ በዮሐንስ እጅ ይጠመቁ ነበር፡፡ ዮሐንስ ከፈሪሳውያንና ከሰዱቃውያን ብዙዎች ወደ ጥምቀቱ ሲመጡ ተመልክቶ ሳይፈራ በድፍረት ስለኃጢአታቸው ወቅሷቸው ለንስሓ የሚገባ ፍሬ እንዲያፈሩም ነገራቸው፡፡ ዮሐንስ እግዚአብሔር በሕዝቡ ላይ ለመፍረድ እንደተዘጋጀ፣ ከእነርሱም በኋላ ሌላ እንደሚመጣ ሰበከ፡፡ ከእርሱ በኋላ የሚመጣው መሲሕ ክርስቶስ በመንፈስ ቅዱስ እንደሚያጠምቅ እና ሕዝቡን እንደሚያነጻ ገለጠ፡፡

www.zeorthodox.org

ዮሐንስ በዮርዳኖስ ወንዝ ዳር "ከእኔ በኋላ የሚመጣው ግን ከእኔ ይልቅ ይበረታል" እያለ ሕዝቡን ሲያስተምር ጌታ ኢየሱስ በዮሐንስ ሊጠመቅ ከገሊላ ወደ ዮርዳኖስ መጣ፡፡ ጌታ ኢየሱስ በዮሐንስ ከተጠመቀ በኋላ ዮሐንስ አገልግሎቱን በመቀጠል "እነሆ የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ የእግዚብሔር በግ" ብሎ ስለ ክርስቶስ መሰከረ፡፡ ሰዎች ክርስቶስን እንደሚከተሉት ሲሰማም በጣም ተደሰተ፡፡ በመጥምቁ ዮሐንስ መሲሕ ክርስቶስን ሕዝቡ እንዲቀበለው የንስሓ ጥምቀት እያጠመቀ የሕዝቡን ልብ ለክርስቶስ ያዘጋጅ ስለነበረ ክርስቶስን ሲያይ "ይመጣል ያልኳችሁ ከእኔ በፊት የነበረ እርሱ ነው" ብሎ ሕዝቡ በክርስቶስ እንዲያምኑ እና እንዲቀበሉት አደረገ፡፡ ሕዝቡን እና ደቀመዛሙርቱን ለክርስቶስ አስረከበ፡፡

በአንድ ወቅት አይሁድ ዮሐንስን "አንተ ማን ነህ" ብለው ሲጠይቁት የመጥምቁ ዮሐንስ ምስክርነት "እኔ ክርስቶስ አይደለሁም፣ የማታውቁት በመካከላችሁ ቆሞአል፣ ከእኔ በኋላ የሚመጣው ከእኔ በፊት ነበረ እኔም አይቻለሁ እርሱም የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ መስክሬአለሁ" የሚል ነበር፡፡ ዮሐንስ ከእግዚአብሔር ስለተላከ የሰውን ሳይሆን የእግዚአብሔርን ያገለግል ነበር፡፡ በዚህ የተነሣ ሳይፈራ ኃጢአተኞችን ንስሓ እንዲገቡ ደፍሮ ይወቅስ ስለነበር የወንድሙን ሚስት አግብቶ የነበረውን ሄሮድስን ዮሐንስ ሳይፈራ ወቀሰው፡፡ ሄሮድስ ኃጢአቱን አምኖ ንስሓ እንደመግባት ዮሐንስን አሳሰረው፤ ይህን አጋጣሚ ተጠቅማ የሄሮድስ ሚስት በልጇ ዘፈን ምክንያት የዮሐንስን ራስ አስቆረጠችው፡፡ ዮሐንስን ደቀመዛሙርቱ ወስደው ቀበሩት፡፡

## ማጠቃለያ፡-

ዮሐንስ የእውነተኛ አገልጋይ ምሳሌ ነው፡፡ ዮሐንስ አንድም ቀን የራሱን ክብር እና ደስታ አልፈለገም፡፡ ዘመኑን ሙሉ በአገልግሎቱ ያከበረው የላከውን ነው ደስታውም ሰዎች በክርስቶስ አምነው ሲከተሉት ማየት ስለነበር ሰዎች ክርስቶስን ሲከተሉት አይቶ በጣም ደስ አለው፡፡ ዮሐንስ እውነተኛ የክርስቶስ ምስክር በመሆኑ ለሕዝቡ ክርስቶስን ከፍ አድርጎ አሳይቷል፡፡ እውነተኛ አገልጋይ ስለነበረም ኃጢአተኛውን ሄሮድስን በእግዚአብሔር ቃል ሳይፈራ በመውቀሱ በእሥር ተንገላቶ በመጨረሻም በሄሮድስ ሚስት አማካኝነት በሰማዕትነት አርፏል፡፡ ስለዚህ ልጆች እናንተም የመጥምቁ ዮሐንስን አርአያነት በመከተል በአገልግሎታችሁ እንደ ዮሐንስ የላካችሁን አክብሩ እንጂ የራሳችሁን እውቅና እንዲሁም ክብር አትፈልጉ፡፡

www.zeorthodox.org

***ጥያቄዎች፡-***

1. ዮሐንስ ለአገልግሎት ራሱን ያዘጋጀበት ስፍራ ምን ይባላል?
2. ዮሐንስ አገልግሎቱን እንዴት ጀመረ?
3. ዮሐንስ ወደ እርሱ ሊጠመቁ የሚመጡትን ምን ብሎ ወቀሳቸው?
4. ዮሐንስ ክርስቶስ ከእኔ በፊት ነበረ ማለቱ ምንን ያመለክታል?
5. ዮሐንስ ክርስቶስ ከተጠመቀ በኋላ ስለ ክርስቶስ ምን ብሎ መሰከረ?

## ተግባር፡-

- መምህሩ ልጆች ራሳቸውን እንዴት ለአገልግሎት ማዘጋጀት እንዳለባቸው እና ዝግጅት መች እንደሚጀምር ያብራራላቸው፡፡
- የምድረ በዳን መንፈሳዊ ትርጉም ልጆች ተረድተው ከእግዚአብሔር ጋር የጽሞና ጊዜ እንዲኖራቸው ንገሯቸው፡፡
- ልጆች የአገልግሎት ፈተናዎችን እንዴት ማለፍ እንደምትችሉ ከጓደኞቻችሁ ጋር ተመካከሩ፡፡

www.zeorthodox.org

# ወዳጅነት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ልጆች ወዳጃቸውን እንዴት መምረጥ እንዳለባቸው ማስተማር፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "ወዳጅ በዘመኑ ሁሉ ይወዳል፡፡" ምሳ. ፲፯÷፲፯

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ፩ሳሙ. ፲፰÷፩-፫፣ ዘጸ.፳÷፲፫-፲፯፣ ዘሌ. ፲፱÷፲፯-፲፰፣ ምሳ. ፲፬÷፳፩፣ ፲፰÷፳፬፣ ማቴ. ፲፱÷፲፱፣ ፲፰÷፲፭-፲፯፣ ሉቃ. ፲÷፳፭-፴፯፣ ፩ዮሐ. ፫÷፲፰፣ ፲፭÷፲፫፣

## መግቢያ፡-

- መምህሩ ያለፈውን ሳምንት ትምህርት ይከልስላቸው፡፡
- ልጆች ወዳጅ ወይም ጓደኛ ማለት ምን ማለት ነው?
- ጓደኞቻችሁን ስትመርጡ መመዘኛችሁ ምንድነው?
- ጓደኛ ያስፈለጋችሁ ለምንድነው?

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚመሰክረው ሰው የተፈጠረው ከሰው ጋር ለመኖር ነው፡፡ ሰው ሰው የሚሆነውም ከሰው ጋር ሲኖር ነው፡፡ ሰው ከሰዎች ጋር በሰላም፣ በፍቅር፣ በመከባበር እና በመረዳዳት እንዲኖር የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው፡፡ ከዐሥሩ ትእዛዛት ውስጥ ከስድስተኛው እስከ ዓሥረኛው ድረስ ያለው ሰው ለባልንጀራው ያለበትን ግዴታ እና ሓላፊነት የሚያስረዳ ነው፡፡ ባልንጀራችንን መውደድ እንዳለብን ብሉይ ኪዳን እና አዲስ ኪዳን የሚያዙን ሲሆን በተለይ ክርስቶስ ለሰዎች ሁሉ ስለ ቤተ ክርስቲያን ሰውን ሁሉ እንድንወድ ያዘናል፡፡ እያንዳንዳችን ወዳጅ እና ጓደኛ እንዲኖረን የእግዚአብሔር ፈቃድ መሆንን ልንገነዘብ ያስፈልጋል፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ የመልካም ጓደኝነት ተምሳሌት ሆነው ዘወትር የምናስታውሳቸው ዳዊትና ዮናታን ናቸው፡፡ ዳዊት የበጎች እረኛ ነው፣ ዮናታን ደግሞ የንጉሥ ሳኦል ልጅ ነበር፡፡

www.zeorthodox.org

ነገር ግን ፍቅር ድንበር ስለሌለው ዮናታን እና ዳዊት በጣም የሚዋደዱ ጓኛሞች ሆኑ፡፡ በአንድ ወቅት የዳዊት ጓደኛ አባት ንጉሥ ሳኦል ዳዊትን አገልጋዮቹ እንዲገድሉት ትእዛዝ ሰጠ፡፡ ዮናታን የአባቱን ምክር እንደሰማ ዳዊትን በጣም ይወደው ስለነበር እንዲሸሽና እንዲያመልጥ ነገረው፤ ዳዊትም ከሳኦል እና ከገዳዮቹ ፊት ሸሸ፡፡ የአባቱ የንጉሥ ሳኦል ቁጣ ሲበርድ ዮናታን አባቱን ስለ ዳዊት ንጽሕና መስክሮ ማሳመን ስለቻለ ሳኦል በዳዊት ላይ ያወጀውን ዓዋጅ ቀየረ፡፡ ዳዊትና ዮናታንም እስከ ዘመናቸው መጨረሻ በጣም የሚዋደዱ ጓደኞሞች ነበሩ፡፡ በዚህ የተነሳ ዳዊትና ዮናታን የጥሩ ጓደኞሞች ተምሳሌት ሆነው ሁል ጊዜ ይተረካሉ፡፡

## መልካም ጓደኛ መሆን የሚቻለው እንዴት ነው?

ሐዋርያት ቅዱስ ጳውሎስ ለሰዎች እንዴት መልካም ጓደኛ መሆን እንደሚገባን በቈላስይስ መልእክቱ እንደሚከተለው መክሮናል፡- (ቆላ. ፫÷፲፪-፲፫)

- ምሕረትን በማድረግ
- ትዕግሥተኛ በመሆን
- ርኅሩኅ በመሆን
- ይቅር ባይ በመሆን
- ትሑት በመሆን
- ደስ ካላቸው ጋር ደስተኛ በመሆን
- ራስ ወዳድ ባለመሆን
- ካዘኑት ጋር በማዘን

በአጠቃላይ በብሉይና በሐዲስ ኪዳን የተሰጡትን ትእዛዛት በመጠበቅ እና በየዕለት ተዕለት ሕይወታችን በመተግበር ለሌሎች ጥሩ ወዳጅ መሆን እንችላለን፡፡

## ጓደኞቼን እንዴት ልምረጥ?

መጽሐፍ ቅዱስ ጓደኝነት ሓላፊነት እና ተጠያቂነት ያለበት የጠበቀ ግንኙነት በመሆኑ ወዳጆቻችንን ስንመርጥ ጥንቃቄ እንድናደርግ ይመክረናል፡፡ ይህ ጥንቃቄ ያስፈለገበት ምክንያት እኛም በሌሎች እንዳንጎዳ ሌሎችም በእኛ እንዳይጎዱ እና እንዳያዝኑ አስቀድሞ ለመከላከል ሲባል ነው፡፡ ስለዚህ ወዳጆቻችንን በምንመርጥበት ጊዜ ትክክለኛ ሚዛን ሊኖረን ይገባል፡፡ የሚከተሉት መመዘኛዎች ትክክለኛ ምርጫ እንድንመርጥ የሚያግዙን ስለሆኑ እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

- በእግዚአብሔር የሚታመኑ፣
- ከእኛ ዓላማና ራእይ ጋር የሚሄዱ፣
- በጎ ነገሮች የበዙላቸው፣
- የሐሳብ ልዩነትን የሚያከብሩ እና የሚያዳምጡ፣
- በተለያዩ ሱሶች ያልተያዙ፣
- ለትምህርታቸው እና ለሥራቸው ታማኝ የሆኑ ቤተሰቦቻቸውን የሚያከብሩና የሚታዘዙ፣
- የእግዚአብሔርን ቃል ለመማር የሚተጉ እና ለመንፈሳዊ ሕይወታቸው ቅድሚያ የሚሰጡ . . . ወዘተ፡፡

www.zeorthodox.org

## ማጠቃለያ፡-

ልጆች በዚህ ትምህርት ጓደኝነት ትልቅ ኃላፊነት ያለበት ግንኙነት እንደሆነ እናንተም ለጓደኞቻችሁ ምን እንዳለባችሁ እና ወዳጆቻችሁን ስትመርጡ ምን ዓይነት መመዘኛ ሊኖራችሁ እንደሚገባ በሚገባ ተምራችኋል፡፡ ስለዚህ እግዚአብሔር መልካም ጓደኛ እንዲሰጣችሁ ራሳችሁን በጸሎት በማዘጋጀት ጠብቁ፡፡ እናንተም ለሌሎች መልካም ጓደኛ ለመሆን ተዘጋጁ፡፡

## ተግባር፡-

- መምህሩ ልጆች የጓደኝነት ሕይወታቸውን እንዲያካፍሉ ፈቃደኛ የሆኑትን ይጋብዛቸው፡፡
- ልጆች ስንት ጓደኛ እንዳላችሁ እና ጓደኝነታችሁ ምን እንደሚመስል እቤት ሄዳችሁ በጽሞና አስቡ፡፡
- ከጓኞቻችሁ ጋር ያላችሁ ግንኙነት የበለጠ እንዲጠነክር ምን ታስባላችሁ?

www.zeorthodox.org

# አባትህንና እናትህን አክብር

**የትምህርቱ ዓላማ፡- ልጆች ወላጆቻቸውን እንዲያከብሩ** እና እንዲታዘዙ ማስተማር፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "**አባትህንና እናትህን አክብር** እግዚአብሔር አምላክህ በሚሰጥህ ምድር ዕድሜህ እንዲረዝም" ዘጸ.፳ ፥ ፲፪፡፡

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ዘጸ. ፳÷፲፪-፲፯፤ ፳፩÷፲፭፤ ዘሌ ፳÷፱፤ ምሳ.፴÷፲፯፤ ፲÷፩፤ ፲፭÷፳፤ ዘዳ. ፭÷፲፮፤ ፩ጢሞ ፭÷፰፡፡

## መግቢያ፡-

- መምህሩ ያለፈውን ሳምንት ትምህርት ይከልስላቸው፡፡
- ልጆች ከዐሠርቱ ትእዛዛት ስንቱን ታስታውሳላችሁ?
- ወላጆቻችሁን የምታከብሩት እንዴት ነው?
- እግዚአብሔር ወላጆቻችንን እንድናከብር ያዘዘን ለምንድነው?

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

በመጽሐፍ ቅዱስ አባት የሚለው ቃል፡- የወለደ፣ በሥርዓት ኮትኩቶ ያሳደገ፣ በሥጋና በመንፈስ የአባትነትን አሳቦች ያመለክታል፡፡

አባት፡-

www.zeorthodox.org

- በሥጋ ወላጅ የሆነ ሰውን፤
- በትውልድ ሐረግ የሚገኝ የቅርብ ወይም የሩቅ ወላጅ፤
- በሃይማኖት የመጀመሪያ ተጠሪ ሰውን፤
- ሰውን ወደ እምነት ያመጣ (ያደረሰ) ሰው፤
- የአንድ ነገር ምንጭና ምክንያት አባት ተብሎ ይጠራል፡፡

ልክ እንደ አባት እናት የሚለው ቃል የወለደች፣ ተንከባክባና መግባ ያሳደገች በአጠቃላይ በሥጋና በመንፈስ የእናትነትን ሥራ የፈጸመችን ሴት የሚያመለክት ቃል ነው፡፡ ልጅ የሚለውም ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ የሚከተሉትን ነገሮች ያመለክታል፡፡

ልጅ፡-

- ከብዙ ዘመን በኋላ በትውልድ ሐረግ የሚገኝን ሰው፤
- የአንድ ሥራ ወይም የትምህርት ተከታይን፤
- በሃይማኖት የተወለደ ሰውን፤
- በዕድሜ የበታች የሆነ ሰውን፤
- በሌላ አሳዳጊ ሥር ያለ ሰውን፤
- በአጠቃላይ የአገር ወይም የአካባቢ.........ወ.ዘ.ተ ተወላጅን የሚያመለክት ቃል ነው፡፡

መጽሐፍ ቅዱስ ወላጆች ከልጆቻቸው ጋር ሊኖራቸው ስለሚገባ ግንኙነትም በሰፊው ይናገራል፡፡

1.**የወላጆች ተግባር፡-**

- ልጆቻቸውን በጥበብ ማሳደግ፡፡ ምሳ. ፩÷፰
- ልጆቻቸው በተገቢው ሥርዓት እንዲያድጉ መጠበቅ፡፡
- ልጆች ሲያጠፉ መቅጣት፡፡ ምሳ.፲፫÷፳፬
- የሃይማኖትን ትምህርት ማስተማር፡፡ ዘጸ. ፲፫÷፰
- በአጠቃላይ ልጆችን በሚያስፈልጋቸው ሁሉ ተንከባክቦ የማሳደግ ኃላፊነት የወላጆች ነው፡፡
- ለወላጆቻቸው መታዘዝ፤
- ወላጆቻቸው ሲሸመግሉ እነርሱን መርዳት እና መንከባከብ፡፡

በአጠቃላይ የወላጆቻቸውን ምክር በመስማት እና እነርሱን ደስ የሚያሰኛቸውን ነገር ሁሉ በማድረግ እንዲያገለግሏቸው መጽሐፍ ቅዱስ ያስተምራል፡፡ ሐዋርያት ልጆች ለወላጆቻቸው በጌታ እንዲታዘዙ አስተምረዋል፡፡ (ኤፌ.፮÷፩-፫፣ ፩ጢሞ.፭÷፬፣ ፪ጢሞ.፫÷፪) ልጆች ወላጆቻቸውን በማክበራቸው እግዚአብሔር በዕድሜና በጤና እንደሚባርካቸው ቃል የገባላቸው ሲሆን በረከቱም ይህን ሕግ ለሚፈጽሙ ሁሉ ነው፡፡

www.zeorthodox.org

## ማጠቃለያ፡-

ልጆች በዚህ ትምህርት «አባትህንና እናትህን አክብር» የሚለው የእግዚአብሔር ሕግ ወላጅ አባት እና እናታችንን ብቻ ሳይሆን በሃይማኖት፣ በትምህርት በአጠቃላይ በሥጋና በመንፈስ የወለዱንን ሁሉ ማክበርና መንከባከብ እንደሚገባ በሚገባ አውቃችኋል፡፡ ስለዚህ እናንተም አግዚአብሔር በረጅም ዕድሜና ጤና እንዲባርካችሁ በሥጋና በመንፈስ የወለዷችሁን፣ ታላላቆቻችሁን እና እርስ በርሳችሁ በመከባበር የእግዚአብሔርን ሕግ ፈጽሙ፡፡

***ጥያቄዎች፡-***

1. አባትህንና እናትህን አክብር ብሎ ያዘዘ ማን ነው?
2. አባት የሚለው ቃል ምንን ያመለክታል?
3. እናት የሚለው ቃል ምንን ያመለክታል?
4. ልጅ የሚለው ቃል ምንን ያመለክታል?
5. ልጆች እንዴት ወላጆቻቸውን ያከብራሉ?

## ተግባር፡-

- ልጆች ወላጆቻችሁ ያደረጉላችሁን ነገሮች በዝርዝር ጻፏቸው፡፡
- ዘወትር እግዚአብሔር የሚንከባከቡአችሁ ወላጆችን ስለሰጣችሁ አመስግኑት፡፡
- የአባትና የእናት ቀን ሲከበር ለቤተሰቦቻችሁ «አመሰግናለሁ!» የሚል ካርድና ስጦታዎችን በመስጠት ለእነርሱ ያላችሁን ፍቅርና ክብር ግለጹላቸው፡፡

www.zeorthodox.org

# የጠፋው ልጅ

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ልጆች የእግዚአብሔርን ምሕረት እና ይቅርታ ከጠፋው ልጅ ታሪክ እንዲማሩ መርዳት፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** «አባቱ አየውና አዘነለት ሮጦም አንገቱን አቀፈውና ሳመው» ሉቃ.፲፭÷፳

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ሉቃ.፲፭÷፲፩-፴፪፣ ፳፫÷፵፫፣ ዮሐ.፲፭÷፭-፯፣ ሆሴ.፲፬÷፳፭፣ ኤፌ.፮÷፩-፭፣ መዝ. ፶(፶፩)÷፩-፯

## መግቢያ፡-

- መምህሩ ያለፈውን ሳምንት ትምህርት ይከልስላቸው፡፡
- ልጆች ከቤተሰባችሁ ጋር በመኖራችሁ ደስተኛ ናችሁ? ለምን?
- ልጆች ለቤተሰቦቻችሁ ምክር ታዛዥ ናችሁ?
- ልጆች ከቤት የሚኮበልሉት ለምንድነው?
- የወላጆቻችሁን ምክርና ማስጠንቀቂያ ባለማክበራችሁ ያጋጠማችሁ ክፉ ነገር ምንድነው?

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

ልጆች ከቤተሰባቸው ጋር እንዲኖሩ የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው፡፡ ወላጆች ልጆቻቸውን ተንከባክበው እንዲያሳድጉ መንፈሳዊ ግዴታቸው ሲሆን ልጆች ደግሞ እናት እና አባታቸውን እንዲያከብሩ በእግዚአብሔር ታዘዋል፡፡ ብዙ ጊዜ ግን ግዴታቸውን የማይወጡ ወላጆችን እና ቤተሰባቸውን የማያከብሩ ልጆችን ማየት የተለመደ ሆኗል፡፡ ይህ ለምን ሆነ? ብለን ብንጠይቅ ብዙ ምክንያቶች ሊኖሩ ስለሚችሉ ዛሬ በዚህ ትምህርት ስለ ጠፋው ልጅ ታሪክ እናጠናለን፡፡ አንድ ሰው ሁለት ልጆች ነበሩት፡፡ ይህ ሰው ልጆቹን እጅግ በጣም የሚወድና የሚንከባከብ መልካም አባት የነበረ ቢሆንም አንድ ቀን ትንሹ ልጅ «አባቴ ሆይ ከገንዘብህ የሚደርሰኝን አካፍለኝ» ሲል ለአባቱ ጥያቄ አቀረበ፡፡ አባቱም ለትንሹ ልጅ የሚደርሰውን ገንዘብ ሰጠው፡፡ ትንሹ ልጅ ጥቂት ቀን ከተቀመጠ በኋላ ገንዘቡን ይዞ ወደ ሩቅ ሀገር ሔደ፡፡ በዚያም ገንዘቡን እያባከነ በተነ፡፡ በመጨረሻም ከቤት ይዞት የሄደውን ብር ሁሉ ከጨረሰ እና ከከሰረ በኋላ በዚያ ሀገር ረሀብ ሆነ፡፡ ትንሹ ልጅ ገንዘብ ስላልነበረው በጣም ይጨነቅ ጀመር፡፡ ጥቂት ጊዜ ከቤት ይዞ የወጣውን ልብሱን እና ጌጣጌጡን እየሸጠ ለመኖር ታገለ፣ ነገርግን ስላልቻለ ከሌላ ሰው ጋር ተዳበለ፡፡ ያም ሰው እሪያ (አሳማ) እንዲጠብቅ ወደ ሜዳ ሰደደው፡፡

www.zeorthodox.org

ትንሹ ከረሀቡ ጽናት የተነሣ አሳማዎቹ ከሚበሉት ምግብ ለመመገብ ፈለገ፣ ነገር ግን የሚሰጠው አልነበረም፡፡ ከእነዚህ ሁሉ ነገሮች በኋላ የጠፋው ልጅ ወደ ልቡ ተመልሶ በአባቱ ቤት የነበረውን ነፃነት፣ ክብር፣ ምቾት እና እንክብካቤ……. ወ.ዘ.ተ

ማስተዋል ጀመረ፡፡ በመጨረሻም ጥፋተኛ መሆኑን አምኖ አባቱን ይቅርታ ሊጠይቅ ወደ ቤት ለመመለስ ወሰነ፡፡ ትንሹ ልጅ የበደለውን በደልና ያጠፋውን ጥፋት ከፍተኛ ስለነበር አባቱን ይቅርታ ጠይቆ እንደ ልጅ ሳይሆን ከአገልጋዮቹ እንደ አንዱ እንዲኖር እንደ ሚለምነው አስቦ ተነሥቶ ወደ አባቱ መጣ፡፡ ታናሹ ወደ አባቱ ሲመጣ ሰውነቱ በረሀብ ከስቶ እና ጠውልጎ፣ አሮጌ ልብስ እና የተቀደደ ጫማ አድርጎ ነበር፡፡ አባቱ ትንሹን ልጅ ከሩቅ አየውና አዘነለት ሮጦም አንገቱን አቀፈውና ሳመው፡፡ ትንሹ ልጅ አባቱ እንዲህ ይቀበለኛል ብሎ ስላልጠበቀ በጣም ደንግጦ በፍጥነት ጥፋቱን መናገር ጀመረ «አባቴ ሆይ በሰማይና በፊትህ በደልኩህ ወደ ፊትም ልጅህ ልባል አይገባኝም» አለ፡፡ የአባቱ ምላሽ ግን አሁንም ትንሹ ልጅ ከጠበቀው በላይ ነበር «ፈጥናችሁ ከሁሉ የተሻለ ልብስ አምጡና አልብሱት ለእጁ ቀለበት ለእግሩም ጫማ ስጡ፣ የሰባውን ፊሪዳ አምጥታችሁ እረዱት እንብላም ደስም ይበለን ይህ ልጄ ሞቶ ነበርና ደግሞም ሕያው ሆኖአል ጠፍቶም ነበር ተገኝቶአልም" ከዚህ በኋላ ሁሉም የጠፋው ልጅ ስለተገኘ ደስ ይላቸው ጀመር፡፡

## ማጠቃለያ፡-

ልጆች ከዚህ ትምህርት የጠፋው ልጅ ከአባቱ ተለይቶ ሩቅ ሀገር በመሔዱ የደረሰበትን ክፉ ነገር አይታችኋል፡፡ የጠፋው ልጅ ጥፋተኛ መሆኑን ማስተዋል በመቻሉ በመጨረሻ አባቱን ይቅርታ ሊጠይቅ ወደ እቤት ተመለሰ፣ አባቱም ይቅር አለው፡፡ የጠፋው ልጅ ሁለት ጥፋት ነው ያጠፋው፡፡ አንደኛው አባትህን እና እናትህን አክብር የሚለውን የፈጣሪን ትእዛዝ አላከበረም፣ ሁለተኛው የራሱ ያልሆነውን አባቱ የደከመበትን ገንዘብ ወስዶ በማባከኑና በመበተኑ ትልቅ ጥፋት አጥፍቶአል፡፡ ይህ ከአባታችን እግዚአብሔር ተለይተን የምንኖረውን የኃጢአት ኑሮ የሚያስተምር ምሳሌ ሲሆን ኃጢአት ዋጋ እንደሚያስከፍል ተገንዝበን በንስሐ ወደ እግዚአብሔር ስንመለስ እግዚአብሔር ሁሌም እኛን ለመቀበል የምሕረት እጁን ዘርግቶ እንደሚጠብቀን፣ በእኛ መመለስ እርሱ እና የሰማይ መላእክት ደስ እንደሚላቸው የሚያስረዳ ምሳሌ ነው፡፡ ስለዚህ ልጆች ወላጆቻችሁን እያከበራችሁ ከቤተሰቦቻችሁ ጋር በሰላምና በፍቅ ኑሩ፣ የወላጆቻችሁን ምክር ስሙ፡፡ ከእግዚአብሔርና ከቤተሰቦቻችሁ ፈቃድ ወጥታችሁ ለሠራችሁት ክፉ ነገር ወይም ኃጢአት እግዚአብሔርን እና ወላጆቻችሁን ይቅርታ ጠይቁ፡፡

www.zeorthodox.org

***ጥያቄዎች፡-***

1. ልጆች የቤተሰባቸውን ገንዘብ እንዲካፈሉ የሚፈቀደው መቼ ነው?
2. ልጆች ከቤተሰብ ተለይተው መኖር ያለባቸው መቼ ነው?
3. የጠፋው ልጅ ከአባቱ ተለይቶ በመሄዱ ምን አገኘው?
4. የጠፋው ልጅ ከአባቱ ቤት የነበረውን ምቾት ማስተዋል የቻለው መቼ ነበር?
5. የጠፋው ልጅ አባቱ እንዴት ተቀበለው?
6. ከዚህ ታሪክ ምን ተማራችሁ?
7. ምክርን መስማት እና ይቅርታ ማድረግ ያላቸውን ጠቀሜታ ተናገሩ?

## ተግባር፡-

- መምህሩ ከቤተሰብ ጋር በመኖር የሚገኘውን ከፍተኛ ደስታ ልጆች እንዲገነዘቡና አመስጋኞች እንዲሆኑ ያድርጋቸው፡፡
- ልጆች ከቤተሰባቸው ተለይተው ወጥተው በሚኖሩ ልጆች ላይ እየደረሰ ያለውን ክፉ ነገር ለጓደኞቻችሁ በማካፈል ተወያዩበት፡፡
- የቤተሰባቸውን ገንዘብ ያለ አግባብ ስለሚያባክኑ ልጆች ምን ትላላችሁ? ተወያዩበት፡፡

www.zeorthodox.org

# የፋሲካው በግ

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ለልጆች የፋሲካውን በግ ኢየሱስ ክርስቶስን ማስተዋወቅ፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ" ዮሐ. ፩÷፳፱

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ዘፍ.፳፪÷፩-፲፱፣ ፬÷፪፣ ዘጸ.፲፪÷፫-፳፣ ፲፬÷፫-፬፣ ዘሌ.፳፪÷፲፱፣ ት/ኢሳ. ፶፫÷፩-፲፪፣ ራእ. ፭÷፮፣ ዕብ. ፲፩÷፳፰

## መግቢያ፡-

- መምህሩ ያለፈውን ሳምንት ትምህርት ይከልሰላቸው፡፡
- ልጆች ስለ በግ የምታውቁት ለመምህራችሁ ንገሩ፡፡
- በመጽሐፍ ቅዱስ በግ የምን ምሳሌ ነው?

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

በግ ሥጋው ለመሥዋዕትና ለምግብ፣ ጠጉሩና ቆዳው ደግሞ ለልብስ የሚሆን የዋህ የቤት እንስሳ ሲሆን በራሱ የመከላከል ኃይል ሰለሌለው እረኛ አስፈልጎታል፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚነግረን በጎችን ለመሥዋዕት ማቅረብ ከጥንት ጀምሮ የተለመደ ተግባር ነበር፡፡ አቤል ለእግዚአብሔር ያቀረበው መሥዋዕት በግ ነበር፡፡ አብርሃም በልጁ በይስሐቅ ፈንታ ለእግዚአብሔር ያቀረበው መሥዋዕት እግዚአብሔር ያዘጋጀውን በግ ነው፡፡ በተለይ በእስራኤል በግ ለፋሲካ በዓል መሥዋዕት ሆኖ ይታረድ ነበር፡፡ ፋሲካ የሚለው ቃል በዕብራይስጥ "ፓባሕ" ማለት ሲሆን አለፈ፣ ተሻገረ፣ አመለጠ የሚሉ ትርጉሞችን ያመለክታል፡፡ የእስራኤል ልጆች በግብጽ አገር አርደው ደሙን በደጃፋቸው በመርጨት ከእግዚአብሔር ቁጣ አምልጠው ነበር፡፡

www.zeorthodox.org

የእግዚአብሔር መልአክ በዚያች ሌሊት ግብጻውያንን ሲቀሥፍ፣ ደም በነበረበት ቤት አልፎ ስላልገደለ ወይም ደም የተረጨበትን ቤት ስላለፈ ያ ቀን ፋሲካ ተባለ፡፡ በዚህ የተነሳ ለፋሲካ በዓል የሚታረደው በግ የፋሲካ በግ ተብሎ መጠራት ጀመረ፡፡ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ እስራኤል በበጉ ደም ከሞት ያመለጠቡትን ቀን በማስታወስ በየአመቱ የፋሲካን በዓል በግ እያረዱ ያከብሩ ነበር፡፡ እነዚህ ሁሉ ምሳሌዎች ለእውነተኛው የእግዚአብሔር በግ ለኢየሱስ ክርስቶስ ምልክት ነበሩ፡፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሰው ልጆችን ለማዳን ስለ ሰው ልጆች ኃጢአት የተሰቀለው የፋሲካ ሳምንት ነበር፡፡ ክርስቶስ ንጹሕ የእግዚአብሔር በግ ሆኖ ደሙን ስላፈሰሰልን "ፋሲካችን ክርስቶስ" ተባለ፡፡ (፩ቆሮ. ፭÷፯፣ ፩ጴጥ. ፩÷፲፰-፲፱)

ስለሁላችን ኃጢአት እና በደል እንዲሁም መተላለፍ የቆሰለ፣ ስድባችንን የተሰደበ፣ ውርደታችንን የተዋረደ እና ሞታችንን የሞተ በደሙ ከኃጢአታችን ያነጻን እና ከሞት ያስመለጠን ክርስቶስ ስለሆነ የክርስቶስ ትንሣኤ በዓል ፋሲካ ተብሎ ይጠራል፡፡

በክርስቶስ የሚያምኑ ሁሉ በበጉ ደም የተረጩ፣ የታጠቡና የታተሙ በመሆናቸው ትንሣኤ አላቸው፡፡ ስለዚህ በሐዲስ ኪዳን ክርስቲያኖች እረኛቸውን ክርስቶስን የሚከተሉ በጎች በፍርድ ቀን በክርስቶስ ቀኝ የሚቆሙ ሆነው ተመስለዋል፡፡ በግ ንጹሕና የማይጎዳ የዋህ እንስሳ ስለሆነ ሐሰተኞች የዋህ ለመምሰል የበግ ለምድ እንደሚለብሱ ጌታ ተናግሯል፡፡ (ማቴ. ፯÷፲፭)

## ማጠቃለያ፡-

ልጆች በዚህ ትምህርት ስለ ሰው ልጆች ኃጢአትና በደል ራሱን አሳልፎ ስለሰጠው የፋሲካው በግ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ አውቃችኋል፡፡ ስለዚህ የፋሲካን በዓል ስታከብሩ ክርስቶስ ስለ ሰው ልጆች ያስከፈለውን ዋጋ እያስታወሳችሁ አክብሩ፡፡

### *ጥያቄዎች፡-*

1. በመጽሐፍ ቅዱስ በግ የምን ምሳሌ እንደሆነ ዘርዝሩ?
2. ፋሲካ ማለት ምን ማለት ነው?
3. የፋሲካ በዓልን ማክር መቼ ነው የተጀመረው?
4. ክርስቶስ ፋሲካችን ነው የተባለው ለምንድነው?
5. የሐዲስ ኪዳን መሥዋዕት ማን ነው?

## ተግባር፡-

- ልጆች በይስሐቅ ፈንታ የሞተው በግ እንዴት ከክርስቶስ ጋር እንደሚመሳሰል ከጓኞቻችሁ ጋር ተወያዩ፡፡
- እስራኤል ያከብሩት የነበረው የፋሲካ በዓል አሁን እኛ ከምናከብረው ጋር እንዴት እንደሚመሳሰል እና እንደሚለያይ ለመምህራችሁ ንገሩ፡፡

www.zeorthodox.org

# ንዕማን ተፈወሰ

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ለሚያምን ሰው ሁሉ ነገር እንደሚቻል ለልጆች ማስተማር፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** “ሂድ በዮርዳኖስም ሰባት ጊዜ ታጠብ ሥጋህም ይፈወሳል አንተም ንጹሕ ትሆናለህ” ፬ነገ. ፭÷፲፡፡

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ሉቃ. ፬÷፳፯-፳፰፣ ፬ነገ. ፭÷፩-፲፯፣ ዮሐ. ፭÷፩-፱፡፡

## መግቢያ፡-

- መምህሩ ያለፈውን ሳምንት ትምህርት ይከልስላቸው፡፡
- መምህሩ እግዚአብሔር ለፈውስ እጁን የሚዘረጋላቸው በብዙ መንገዶች እንዳሉት ለልጆች ይንገራቸው፡፡
- ልጆች ጸበል የምትጠመቁት እና የምትጠጡት ለምንድነው?
- በጸበል ስለዳነ ሰው ሰምታችሁ ታውቃላችሁ?
- ልጆች ስለ ለምጽ በሽታ ታውቃላችሁ?

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

የሶርያ ንጉሥ የሠራዊት አለቃ ንዕማን የሚባል ሰው ነበር፡፡ ንዕማን በንጉሡ ዘንድ እጅግ የሚወደድ እና የሚከበር ሲሆን በለምጽ በሽታ ብዙ ጊዜ ይሰቃይ ነበር፡፡ በሠራዊት አለቃው በንዕማን ቤት በሶሪያ አደጋ ጣዮች ተማርካ የመጣች አንዲት ሴት የንዕማንን ሚስት ታገለግል ስለነበር ለሚስቱ ንዕማን በሰማሪያ ወደ ሚኖረው ወደ እግዚአብሔር ነቢይ ወደ ኤልሳዕ ቢሔድ ከበሽታው እንደሚድን ነገረቻት፡፡ የንዕማን ሚስት ለባሏ ከአገልጋይዋ የሰማችውን ነገር ነገረችው፡፡ በማግስቱ ንዕማን ለሶሪያው ንጉሥ ወደ እስራኤል ሀገር መሄድ እንደሚፈልገ ሲነግረው ንጉሡ በንዕማን ሀሳብ ተስማምቶ ለእስራኤል ንጉሥ ደብዳቤ ጽፎ ንዕማን እንዲሔድ ፈቀደለት፡፡ ደብዳቤው የእስራኤል ንጉሥ ንዕማንን ተቀብሎ በደንብ እንዲያስተናግደው የሚናገር ስለነበር የእስራኤል ንጉሥ ንዕማንን ተቀበለው፡፡ ነገር ግን ደብዳቤው ንዕማንን በእንግድነት መቀበል ብቻ ሳይሆን ከበሽታው አድነው የሚል ቃልም ሰለነበረበት ንጉሡ በጣም ተጨነቀ፡፡ የሶሪያ ንጉሥ ነገር ፍለጎ ሆን ብሎ ከባድ ጥያቄ እንደጠየቀው አስቦ በጣም ተጨነቀ፡፡

የዚህን ጊዜ ንጉሡ እንደተጨነቀ የእግዚአብሔር ነቢይ ኤልሳዕ ሰምቶ ንዕማንን ወደ እርሱ እንዲልከው መልእክት ላከበት፡፡ ንዕማን ወደ ነቢዩ ኤልሳዕ መጣ፡፡ ኤልሳዕ ንዕማንን ሄዶ በዮርዳኖስ ወንዝ እንዲታጠብ ከበሽታውም እንደሚድን ነገረው፡፡ ንዕማን ግን እንዴት ከሩቅ ሀገር መጥቼ፣ የአምላኩን ስም ጠርቶ በእጁ ዳስሶ ያድነኛል ብዬ ሳስብ እንዴት በዮርዳኖስ ወንዝ ታጠብ ይለኛል ብሎ በጣም ተናደደ፡፡ “የደማስቆ ወንዞች አባናና ፋርፋ ከእስራኤል ወንዞች ሁሉ አይሻሉምን? በእነርሱስ ውስጥ መታጠብና መንጻት አይቻለኝ ኖሮአልን?” በሎ ተመልሶ መሄድ ጀመረ፡፡ ነገር ግን አገልጋዮቹ ንዕማን ነቢዩ ኤልሳዕ ያዘዘውን እንዲያደርግ ስለለመኑት

የእግዚአብሔር ሰው ኤልሳዕ እንደ ተናገረው በዮርዳኖስ ወንዝ ተጠመቀ፣ ሥጋው እንደ ትንሽ ብላቴና ሥጋ ተመለሰ ከለምጽም ነጻ፡፡ ወደ ኤልሳዕ ተመልሶ ከእስራኤል አምላክ ከእግዚአብሔር በቀር በምድር ላይ አምላክ እንደሌለ መሰከረ በኤልሳዕ አምላክም አመነ፡፡ ንዕማን ከዚህ በኋላ ከእግዚአብሔር በቀር ሌሎች አማልእክትን እንደማያመልክ ተናግሮ የእግዚአብሔር ሰው ኤልሳዕ ከማሰሪያ አፈር እንዲወስድ እንዲፈቅድለት ለመነው፡፡ ነቢዩ ኤልሳዕም ንዕማን አፈሩን እንዲወስድ ፈቀደለት፡፡ ንዕማን ወደ ሀገሩ ተመልሶ ሄደ በሶሪያም ከእግኢብሔር በቀር አምላክ እንደሌለ በመመስከሩ ብዙ ሰዎች በእግዚአብሔር አመኑ፡፡

## ማጠቃለያ፡-

ልጆች በዚህ ትምህርት የሶሪያ ንጉሥ የሠራዊት አለቃ ንዕማን ከእስራኤል ሀገር ተማርካ በመጣች አንዲት ሴት አማካኝነት ወደ እግዚአብሔር ሰው ወደ ኤልሳዕ ወጥቶ እግዚአብሔር እንዴት ከበሽታው እንደፈወሰው፣ ሌሎች አማልክትን ትቶ በእግዚአብሔር እንዳመነ፣ ወደ ሀገሩም ተመልሶ እግዚአብሔር ያደረገለትን በመመስከሩ ብዙዎች እንዳመኑ ተምራችኋል፡፡ ስለዚህ እናንተ በእያንዳንዱ እንቅስቃሴያችሁ እንደ ምርኮኛዋ ሴት የእግዚአብሔር ምስክሮች በመሆን ለሌሎች መዳን ምክንያት ሁኑ፡፡

### *ጥያቄዎች፡-*

1. የሶርያ ንጉሥ የሠራዊት አለቃ ማን ይባላል?
2. የሠራዊት አለቃው በምን ዓይነት በሽታ ይሰቃይ ነበር?
3. ንዕማን ወደ እስራኤል እንዲሔድ ምክንያት የሆነችው ማን ነበረች?
4. የእግዜብሔር ሰው ኤልሳዕ ንዕማን ምን እንዲያደርግ አዘዘው?
5. ንዕማን ለምን በዮርዳኖስ ወንዝ አልጠመቅም አለ?
6. ንዕማን ከበሽታው ከዳነ በኋላ ምን አደረገ?

## ተግባር፡-

- ልጆች ከዚህ ታሪክ ምን እንደተማራችሁ ከጓኞቻችሁ ጋር ተወያዩ፡፡
- በቤተ ክርስቲያን ያለው የጸበል አገልግሎት መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት እንዳለው ምሳሌዎችን በመጥቀስ መምህሩ ልጆች እንዲወያዩበት ያድርግ፡፡

www.zeorthodox.org

# ቤተ ክርስቲያን

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ለልጆች የቤተ ክርስቲያንን ምንነት ማስተማር

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** “በዚችም ዕለት ላይ ቤተ ክርስቲያኔን እሠራለሁ” ማቴ. ፲፮÷፲፰

**ተስጨማሪ ምንባባት፡-** ፪ቆሮ. ፫÷፲-፲፯፣ ማቴ. ፲፮÷፲፮-፳፣ ሐዋ. ፲፮÷፲፫፣ ሮሜ. ፲፮÷፶፩፣ ፩ቆሮ. ፲፬÷፲፬፣ ኤፌ. ፩÷፳፫፣ ፭÷፳፩-፴፫፣ ፩ጢሞ. ፫÷፲፭፣ ገላ.፬÷፳፮

## መግቢያ፡-

- *መምህሩ ያለፈውን ሳምንት ትምህርት ይከልሱላችሁ፡፡*
- ልጆች ቤተ ክርስቲያን ማለት ምን ማለት ነው?
- የቤተ ክርስቲያን *መሥራች* ማን ነው?
- አብያተ ክርስቲያናት ለምን በተለያየ ስም ይጠራሉ?

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

ቤተ ክርስቲያን የሚለው መጠሪያ ስም በመጀመሪያ የተተረጎመው “አቅሌስያ” ከሚለው የግሪክ ቃል ነው፡፡ በግሪክ አቅሌስያ ማለት ማኅበር ወይም ጉባኤ ማለት ሲሆን ቤተ ክርስቲያን የሚለው መጠሪያ በነጠላ ትርጉሙ የክርስቲያኖች ቤት ማለት ነው፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ቤተ ክርስቲያን የሚለው ቃል በአብዛኛው የሚያመለክተው ሰዎችን ሲሆን ቃሉ ሦስት ትርጓሜዎችን ጠቅሎ የያዘ ነው፡፡ ቤተ ክርስቲያን የክርስቲያኖችን ልብ፣ የክርስቲያኖችን ስብስብ (ማኅበር) እና የክርስቲያኖችን የአምልኮ ቤት (ስፍራ) ያመለክታል፡፡ የሐዋርያትን አገልግሎት ስንመለከት በመጀመሪያ በሰው ቤት፣ በትምህርት ቤት፣ በአይሁድ ቤተመቅደስ፣ በወንዝ ዳር፣ በሚመቻቸው ቦታ ለጸሎትና ለአምልኮ ይሰበሰቡ ነበር፡፡ ቤተ ክርስቲያን ትልቅ ማኅበር ስለሆነች በማኅበሩ የሚገኙት ደግሞ የክርስቶስ ተከታዮች ክርስቲያኖች ስለሆኑ ቤተ ክርስቲያን የቅዱሳን ማኅበር ናት፡፡ የቤተ ክርስቲያን መሥራች ክርስቶስ ራሱ ነው፡፡ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንን የመሠረተው በአማኞች ልብ ላይ ሲሆን “አንተ ክርስቶስ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ ነህ” የሚለው የጴጥሮስ እምነት እና ምስክርነት የቤተ ክርስቲያን መሠረት ነው፡፡ በአጠቃላይ በመጽሐፍ ቅዱስ ቤተ ክርስቲያን በአማኞች (በምዕመናን) አካል፣ በቤተመቅደስ፣ በሚስት፣ በዓምድና በመሠረት እንዲሁም በኢየሩሳሌም ሰማያዊት ትመሰላለች፡፡ ቤተ ክርስቲያን በነቢያት ትንቢት በሐዋርያት ስብከት መሠረት ላይ የታነጸች ማዕዘኗም የሕግና የነቢያት ፍጻሜ የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡ ስለዚህ ቤተ ክርስቲያን ከስደት እና ከብዙ መከራ በኋላ ነፃነት እያገኘች ስትመጣ ክርስቲያኖች በአንድነት ክርስቶስን የሚያመልኩበትን ቤት ማነጽ ጀመሩ፤ ክርስቲናትም በማኅበር ይሰበሰቡበት ስለነበር የክርስቲያኖች ቤት እየተባለ መጠራት የተለመደ ሆነ፡፡ ስለ ወንጌል እና ስለ ክርስቶስ መከራ የተቀበሉ ቅዱሳን፣ ጻድቃን፣ ሰማዕታት የክርስትና አርበኞች ስለሆኑ እነርሱን ለማስታወስ

www.zeorthodox.org

ቤተ ክርስቲያን በስማቸው መሠራት እና መጠራት ተጀመረ፡፡

## ማጠቃለያ፡-

ልጆች በዚህ ትምህርት ስለቤተ ክርስቲያን ምንነት በዝርዝር በሚገባ አውቃችኋል፡፡ ቤተ ክርስቲያን መሥራቿ፣ ራሷ እና ባለቤቷ ክርስቶስ ስለሆነ የሁላችንም ቤት ናት፡፡ ቤተ ክርስቲያን የጸሎት፣ የአምልኮ፣ የምስጋና እና የእግዚአብሔርን ቃል መማሪያ ሥፍራ ስለሆነች ልጆች ቤተ ክርስቲያንን አክብሩ፣ እንደ ቅዱስ ዳዊት ወደ ቤተክርስትያን ወደ እግዚአብሔር ቤት ስትመጡ እና እንሂድ ስትባሉም ደስ ይበላችሁ፡፡

### *ጥያቄዎች፡-*

1. ቤተ ክርስቲያን የሚለው ቃል ምንን ያመለክታል?
2. ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንን በምን ላይ መሠረታት?
3. በመጽሐፍ ቅዱስ የቤተ ክርስቲያን ምሳሌዎች ምንድናቸው?
4. ሐዋርያት ክርስቶስን የት ያመልኩ ነበር?
5. በይፋ ቤተ ክርስቲያንን መሥራት መቼ ተጀመረ?

## ተግባር፡-

- መምህሩ ለልጆች የቤተ ክርስቲያንን ባሕርያት ይንገራቸው፡፡
- ልጆች ቤተ ክርስቲያንን እንዴት ለማገልገል እንዳሰባችሁ ከጓኞቻችሁ ጋር ተወያዩ፡፡

www.zeorthodox.org

# የጌታ ቀን

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ልጆች በጌታ ቀን በዕለተ ሰንበት መልካም ነገሮችን እየሠሩ እንዲያከብሩ ማስተማር፣

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "በጌታ ቀን በመንፈስ ነበርሁ፡፡" ራእ.፩÷፲

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ዘጸ. ፳÷፰-፲፩፣ ፴፩÷፲፯፣ ዘኁ. ፲፭÷፴፪-፴፮፣ ዘፍ.፪÷፪-፫

## መግቢያ፡-

- መምህሩ ያለፈውን ሳምንት ትምህርት ይከልስላቸው፡፡
- ልጆች የሰንበት ዕለት ምን በመሥራት ነው የምታሳልፉት?
- የክርስቲያኖች ሰንበት የሚባለው የትኛው ቀን ነው? ለምን ተባለ?
- ሰንበትን እንዴት ማክበር አለብን ብላችሁ ታስባላችሁ?

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

ሰንበት የሚለው ቃል በዕብራይስጥ ማቆም ወይም መተው ማለት ሲሆን እስራኤል ሰባተኛውን ቀን ቀዳሚትን ለእግኢዚአብሔር እንዲቀድሱት በዓሠርቱ ቃላት ታዘው ነበር፡፡ ከዚህም በላይ ሰንበት በእግዚአብሔርና በእስራኤል መካከል የቃል ኪዳን ምልክትም ነበር፡፡ በዚህ ምክንያት ሰንበትን ያላከበረ ሰው ከባድ ቅጣት ይከተለው ነበር፡፡ እግዚአብሔር በመጀመሪያ ስድስት ቀን ሠርቶ ሰባተኛውን ቀን እንዳረፈ ሰንበትን በማክበር የእግዚአብሔርን ሥራ እናስታውሳለን፡፡ እግዚአብሔር ሰው ስድስት ቀን ሠርቶ ዕረፍት እንደሚያስፈልገው ስላወቀ ሰባተኛውን ቀን እንዲያርፍበት ትእዛዝ ሰጠው፡፡ ሰንበት ሰው በዚህ ዓለም ሠርቶ ወደ ዘለዓለም ዕረፍት እንደሚገባ የዘላለም ማረፊያው እግዚአብሔር እንደሆነ ያመለክታል፡፡

www.zeorthodox.org

እስራኤል የሰንበትን ቀን እንዲቀድሱ እና በሚገባ እንዲያከብሩ በእግዚአብሔር ቢታዘዙም እንዴት ማክበር እንዳለባቸው ግን አልተረዱም ነበር፡፡ በተለይ ፈሪሳውያን የራሳቸውን ሕግና ወግ በማዘጋጀት የሰንበትን አከባበር አክብደውት ስለነበር ጌታ ኢየሱስ ሰንበትን ቢያከብርም የፈሪሳውያንን አከባበር ግን ልክ አለመሆኑን አስተምሯል፡፡ ፈሪሳውያን ሰንበት ለሰው ማረፊያ እንደተሠራ ማስተዋል ተስኖአቸው ሰው ለሰንበት የተፈጠረ እስኪመስል ድረስ በሰንበት ዕለት እግርና እጃቸውን አጣምረው ከቤት ሳይወጡ በጎ ሥራ ሳይሠሩ ይውሉ ስለነበር እና ጭንቀታቸው ቀኑ እንዲከበር ብቻ ስለነበር እሸት ከመቅጠፍ፣ ድውይ ከመፈወስ እስኪከለከሉ ድረስ ብዙ ሕግና ወግ ደንግገው ሕዝቡን ግራ ያጋቡ ነበር፡፡ በዚህ የተነሣ ብዙ ጊዜ ክርስቶስ በሰንበት ሕሙማንን ሲያድን ተቃውመውታል፤ በሰንበት በሽተኞችን አዳነ ብለውም ሲከሱት ነበር፡፡ ክርስቶስ ግን ከሰው ወግና ሥርዓት ምሕረት እንደሚበልጥ፣ ራሱም የሰንበት ጌታ መሆኑን፣ በሰንበት ቀንም በጎ ነገር መሥራት እንደተፈቀደ አስተማረ፡፡ (ማቴ. ፲፪÷፩-፲፬)

ከሳምንቱ በመጀመሪያው ቀን በዕለተ ሰንበት (እሑድ ቀን) ክርስቶስ ሞትን ድል አድርጎ ስለተነሣ ደቀመዛሙርቱ በዚህ ቀን

እየተሰበሰቡ እግዚአብሔርን ማምለክና ማመስገን ጀመሩ፡፡ አይሁድና ክርስቲያኖች እየተራራቁ፣ ወንጌልም በአሕዛብ ዘንድ እየተስፋፋ ሲሄድ ክርስቲያኖች የእግዚአብሔርን ቀን በሳምንቱ በመጀመሪያው ቀን አከበሩ፣ ቀኑም የጌታ ቀን ተባለ፡፡ (ሉቃ. ፳፬÷፩፣ ሐዋ. ፳÷፯፣ ፩ቆሮ. ፲፮÷፪፣ ራእ.፩÷፲) ከዚህ ጊዜ ጀምሮ እሑድ ዕለትን ቤተ ክርስቲያን የጌታ ቀን እያለች በማክበር ላይ ትገኛለች፡፡ በእናት ቤተ ክርስቲያናችን በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንም እሑድ ዕለት በታላቅ ድምቀት በቅዳሴ፣ በዝማሬና በምብሥጋና ካህናት እና ምእመናን ያከብሩታል፡፡

## ማጠቃለያ፡-

ልጆች በጌታ ቀን በዕለተ ሰንበት ቤተ ክርስቲያን በመሄድ በቅዳሴና በቁርባን እግዚአብሔርን ማምለክ፣ ሳምንቱን ሙሉ በሥራችሁ ስለ አገዛችሁ እና ከክፉ ነገሮች ሁሉ ስለጠበቃችሁ እርሱን ማመስገን አለባችሁ፡፡ ብዙ ልጆች ቅዳሜ ማታ ሲዝናኑ እና ፊልም ሲያዩ ያመሹና እሑድ ጠዋት ቤተ ክርስቲያን ለመሄድ ሲነሱ ይስተዋላል፡፡ ነገር ግን ይህ በእናንተ ሕይወት መሆን የለበትም፡፡ እሑድ ለጌታ የተለየ ቀን ነው፡፡ ቤተ ክርስቲያን ሄዳችሁ የእግዚአብሔር ቃሉ የምትሰሙበት፣ ቅዳሴ የምታስቀድሱበት፣ ቅዱስ ቁርባንን የምትቀበሉበት እና ከቤተሰባችሁ ጋር እግዚአብሔርን እያመሰገናችሁ በጋራ የምታሳልፉበት ቀን መሆን አለበት፡፡ በተለይ በጌታ ቀን የታመሙትን በመጠየቅ፣ የተራቡትን በማብላት፣ ያዘኑትን በማጽናናት እና ደካሞችን በመርዳት በአጠቃላይ በጎ ነገሮችን በመሥራት ማሳለፍ እንዳለባችሁ አትዘንጉ፡፡

### *ጥያቄዎች፡-*

1. እግዚአብሔር ፍጥረታትን ፈጥሮ በስንተኛው ቀን ዐረፈ?
2. እስራኤል የሰንበትን ዕለት እንዲያከብሩ የታዘዙት ለምን ነበር?
3. ክርስቶስ የፈሪሳውያንን የሰንበት አከባበር የነቀፈው ለምንድነው?
4. ክርስቲያኖች እሑድ ቀን የጌታ ቀን ብለው ማክበር የጀመሩት መቼ ነው?
5. ሰንበትን እንዴት እንድናከብር ነው የታዘዝነው?

www.zeorthodox.org

## ተግባር፡-

- ልጆች ከቤተሰባችሁ እና ከጓኞቻችሁ ጋር በመሆን በሰንበት ዕለት አረጋውያንን፣ ወላጅ አልባ ሕፃናትን፣ በየሆስፒታሉ የተኙ ሕመምተኞችን እና እሥረኞችን በተራ በተራ የመጎብኘት ዐቅድ አውጥታችሁ በጎ ነገር ማድረግን ተለማመዱ፡፡

# ነቢዩ ሐጌ

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ልጆች በሕይወታቸው እግዚአብሔርን በነገር ሁሉ ማስቀደምን እንዲለማመዱ መርዳት፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "አስቀድማችሁ የእግዚአብሔርን መንግሥት ጽድቁንም ፈልጉ ይህም ሁሉ ይጨምርላችኋል፡፡" ማቴ.፮÷፴፫

**ተጨማሪ ምንባብ፡-** ትንቢት ሐጌ ምዕራፍ ፩ እና ፪፡፡

## መግቢያ፡-

- መምህሩ ያለፈውን ሳምንት ትምህርት ይከልስላቸው፡፡
- ልጆች በሕይወታችሁ ቅድሚያ የምትሰጡት ነግር ምንድነው?
- ፍላጎታችሁን ለይታችሁ ታውቃላችሁ?
- የምትፈልጉትን ነገር ለማግኘት የእናንተ ድርሻ እስከምን ድረስ ነው?

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

እስራኤል በባቢሎን ሀገር በምርኮ ሲኖር ሐጌ በባቢሎን ተወለደ፡፡ በዘሩባቤል ዘመነ መንግሥት ከባቢሎን ወደ ኢየሩሳሌም ከተመለሱት እስራኤላውያን ጋር ተምልሶ በዚያ መኖር ጀመረ፡፡ ሐጌ እግዚአብሔር ነቢይ ሆኖ ሕዝቡን እንዲያገለግል ስለመረጠው በሰባ አምስት ዓመቱ ትንቢት ተናገረ፡፡

www.zeorthodox.org

እስራኤል ከስደት ከተመለሱ በኋላ የእግዚአብሔርን መቅደስ መሥራት ጀምረው ነበር፤ ነገር ግን በሕዝብ መንፈሳዊ ዝለት እና በግል ሥራቸው መጠመድ እንዲሁም ከሳምራውያን በደረሰባቸው ተቃውሞ የቤተመቅደሱ ሥራ ተቋረጠ፡፡ በዚህ ጊዜ ነበር እግዚአብሔር ነቢዩ ሐጌን ሕዝቡ የጀመሩትን የቤተመቅደሱን ሥራ እንዲፈጽሙ ያረጋቸው ዘንድ የላከው፡፡ ሐጌ ነቢይ ሆኖ በእስራእል ላይ የተላከበት ዘመን እስራኤል የእግዚአብሔርን ቤት መሥራት ትተው የራሳቸውን ቤት በማሳመር የተጠመዱበት ዘመን ስለነበር ለሕዝቡ የጀመሩትን ቤተመቅደስ እንዲያጠናቅቁ እግዚአብሔርን በማክበራቸው ስለሚቀበሉት በረከት እንዲሁም ወደፊት እግዚአብሔር ስለሚያደርግላቸው በጎ ነገር ሁሉ በግልጽ አስተምሯል፡፡

## ማጠቃለያ፡-

ምንጊዜም ቢሆን በመንፈሳዊ ሕይወታችን መቅደም ያለበት እግዚአብሔር ብቻ ነው፡፡ እስራኤል የሚቀድሙውን እና የሚበልጠውን ትተው በሚከተለው ነገር ላይ ሲባዝኑ ነቢዩ ሐጌ እግዚአብሔርን እና መቅደሱን መሥራትን እንዲያስቀድሙ መከራቸው፡፡ እስራኤልም የነቢዩ ሐጌን ምክር ሰምተው እግዚአብሔርን እና መቅደሱን መሥራትን ስለ አስቀደሙ እግዚአብሔር በብዙ በረከት ባርኳቸዋል፡፡ እናንተም እግዚአብሔርን እና ፈቃዱን በሕይወታችሁ ስታስቀድሙ እግዚአብሔር የእናንተን ፍላጎት ያሟላል፡፡ እናንተ የእርሱን መቅደስ ስትሡሩ እርሱ ደግሞ የእናንተን ሕይወት ይሠራል፡፡

### *ጥያቄዎች፡-*

1. ነቢዩ ሐጌ የት ተወለደ?
2. ሐጌ ወደ ኢየሩሳሌም እንዴት መጣ?
3. ሐጌ ለእስራኤል ትንቢት የተናገረው የስንት ዓመት ሰው ሆኖ ነው?
4. እስራኤል የእግዚአብሔርን ቤት ከመሥራት የዘገዩት ለምንድ ነው?
5. የነቢዩ ሐጌ መልእክት ምን ነበር?

## ተግባር፡-

- ልጆች ከዚህ ትምህርት በኋላ ወደ ቤት ስትመለሱ የነቢዩ ሐጌን መጽሐፍ አንብቡ፡፡
- ልጆች በሕይወት ቅድሚያ ሊሰጣቸው የሚገቡ ነገሮችን ከዘረዘራችሁ በኋላ እነርሱን አለማስቀደም የሚያስከፍለውን ዋጋ ከጓኞቻችሁ ጋር ተወያዩ፡፡

www.zeorthodox.org

# ማርያም

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ልጆች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ማርያም በሚል መጠሪያ ስም ስንት ሴቶች እንደተጠሩ እንዲያውቁ እና ከእነርሱ ሕይወት እንዲማሩ ማስተማር፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "ስምህ እንደሚፈስ ዘይት ነው ስለዚህ ደናግል ወደዱህ፡፡" መኃ.፩÷፫

**ተጨማሪ ምንባባት፡-**

## መግቢያ፡-

- መምህሩ ያለፈውን ሳምንት ትምህርት ይከልስላቸው፡፡
- ልጆች ማርያም በሚል የሚጠሩ ስንት ሴቶች ታስታውሳላችሁ? ለመምህራችሁ ንገሩ፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ማርያም በሚል መጠሪያ ስም የተጠሩ ብዙ ሴቶች ሲሆኑ በዚህ ትምህርት የእያንዳንዳቸውን ሕይወት እና አገልግሎት በቅደም ተከተል እናጠናለን፡፡

### የሙሴ እኅት ማርያም

የሙሴ እኅት ማርያም በግብጽ በፈርዖን ዘመን ሙሴ በወንዝ ላይ በተጣለ ጊዜ በእርሱ ላይ የሚሆነውን ለማወቅ ትመለከት እና ትጠብቅ የነበረች ሴት ናት፡፡ በጥበብም የፈርዖንን ልጅ በማናገር ሙሴ የእናቱን ጡት እየጠባ እንዲያድግ ማድረግ ችላም ነበር፡፡ (ዘጸ. ፪÷፬-፰) የሙሴ እኅት ማርያም ትንቢትን የመናገር እና የዝማሬ ጸጋ ስለነበራት እስራኤላውያን የኤርትራን ባሕር ከተሻገሩ በኋላ ነቢይት ሆና ሴቶችን በመዝሙርና በምስጋና መራች፡፡ (ዘፍ. ፲፭÷፳-፳፩) ወንድሟን ሙሴን ለምን ኢትዮጵያቷን አገባ ብላ ስለአማችው እግዚአብሔር በለምጽ ቀጣት፡፡ (ዘኅ. ፩፪፤ ዘዳ. ፳፬÷፱) እስራኤል ወደ ከነዓን እየተጓዙ ገና በጉዞ ላይ እያሉ ሞተች በቃዴስም ተቀበረች፡፡ (ዘኍ. ፳÷፩)

**ማርያም የዮቴር ልጅ፡-** የዕዝራ የልጅ ልጅ ናት፡፡ (፩ዜና.መ. ፬÷፲፯)

### የአልዓዛር እኅት ማርያም፡-

ከኢየሩሳሌም አጠገብ ባለው ቢታንያ በተባለው መንደር ከእኅቷ ማርታ እና ከወንድሟ አልዓዛር ጋር ትኖር ነበር፡፡ (ዮሐ.

www.zeorthodox.org

፲፩÷፩) ቤተሰቡ ሁሉ የጌታ ወዳጆች ስለነበሩ ጌታ ኢየሱስ በቤታቸው ተገኝቶ ተስተናግዷል፡፡ ማርያም በጌታ እግር ሥር ቁጭ ብላ ቃሉን ስለሰማች ክርስቶስ አመስግኖአታል፡፡ (ሉቃ. ፲÷፴፱-፵፪) ጌታ ኢየሱስ ወንድሟን አልዓዛርን ከሞት ሲያስነሣ በዚያ ነበረች፡፡ ጌታ ኢየሱስም እንደሚሞት ተረድታ ስለነበር በናርዶስ ሽቱ እግሩን ቀባችው፡፡ (ዮሐ. ፲፪÷፩-፰)

## ማርያም መግደላዊት

ከገሊላ ከተማ ከመጌዶል መጥታ ክርስቶስ ሰባት አጋንንት አወጣላት፡፡ (ማቴ. ፲፭÷፴፱፣ ሉቃ. ፰÷፪፣ ማር. ፲፭÷፵-፵፩) ማርያም ለክርስቶስ መስቀልና መቀበሩ ምስክር ነበረች፡፡ ከክርስቶስ ትንሣኤ በኋላ በአታክልት ስፍራ ለብቻዋ ክርስቶስ ታያት፡፡ (ዮሐ.፳÷፩-፲፰፣ ማቴ. ፳፯÷፶፯-፷፩) በኋላም የክርስቶስን ትንሣኤ ከሌሎች ሴቶች ጋር ሆና መሰከረች፡፡

**የቀሊዮጳ ሚስት ማርያም፡-** የቀሊዮጳ ሚስት ማርያም ጌታ በተሰቀለ ጊዜ ከመስቀሉ አጠገብ ቆማ ነበር፡፡ (ዮሐ. ፲፱-፳፭)

**ማርያም የታናሹ ያዕቆብ እና የዮሳም እናት፡-** የክርስቶስ ስቅለት እና መቃብር ምስክር የነበረች ሴት ናት (ማር. ፲፭÷፵-፵፯፣ ሉቃ. ፳፬÷፲)

### የማርቆስ እናት ማርያም፡-

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በቤቷ የፋሲካ በዓልን ከደቀመዛሙርቱ ጋር አክብሯል፡፡ ደቀመዛሙርቱ በእርሱ ቤት ሆነው ሲጸልዩ መንፈስ ቅዱስን ተቀብለዋል፡፡ የማርያም ቤት የመጀመሪያዋ ቤተ ክርስቲያን እየተባለ ይጠራል፡፡ (የሐዋ/ሥራ. ፲፪÷፲፪)

### እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም፡-

ከሴቶች ሁሉ መካከል ተለይታ የኢየሱስ ክርስቶስ እናት ለመሆን የተመረጠች ሴት ናት፡፡ (ሉቃ. ፩÷፳፮-፴፰) የመልአኩ የቅዱስ ገብርኤልን ቃል አሜን እያለች ያመነች ብፅዕት ሴት ስትሆን ክርስቶስን ወልዳ ተንከባክባ አሳድጋዋለች፡፡ ከክርስቶስ ጋር ወደ ግብጽ ሀገር ተሰዳለች፤ ብዙ መከራንም በሕይወቷ ተቀብላለች፡፡ በቃና ዘገሊላ ሰርግ ቤት በልጇ ፊት በአማላጅነት ቆማለች፡፡ የልጇን የመስቀል መከራ ከብዙ ዕንባ እና ሐዘን ጋር ተቀብላለች፡፡ ጌታችን ከተሰቀለ በኋላ እስከ ዕረፍትዋ ድረስ ቅዱስ ዮሐንስ ተንከባክቦ በቤቱ አኑሮአታል፡፡ (ዮሐ. ፲፱÷፳፮-፳፯) ከልጇ ትንሣኤ በኋላ ከሐዋርያት ጋር በጸሎት ትተጋም ነበር፡፡ (ሐዋ. ፩÷፲፬) እመቤታችን ሁለንተናዋን ለእግዚአብሔር የሰጠች፣ ዘመኗን ሙሉ እግዚአብሔር እና ቃሉን አሜን ብላ ያገለገለች ሴት ናት፡፡

www.zeorthodox.org

## ማጠቃለያ፡-

ልጆች በዚህ ትምህርት በመጽሐፍ ቅዱስ ስንት ሴቶች "ማርያም" በሚለው የመጠሪያ ስም እንደተጠሩ እና አገልግሎታቸው ምን እንደነበር ተምራችኋል፡፡ የሙሴ እኅትም የሐሜትን ጉዳት የተማርንባት ሴት ናት፡፡ በመንፈሳዊ ሕይወታችን ክርስቶስን እና ቃሉን መማርን የተማርንባት ሴት ደግሞ የአልዓዛር እኅት ማርያም ስትሆን ቤቷን ለመንፈሳዊ አገልግሎት የሰጠችው ማርያም የማርቆስ እናት ደግሞ ለክርስቶስ ወንጌል የነበራትን በጎ ልብ የተማርንባት ሴት ናት፡፡ የእናታችን የድንግል ማርያም የአገልግሎት

ሕይወት እንዲሁ አስተማሪ ነው፡፡ ከድንግል ማርያም ሕይወት እምነትን፣ መታዘዝን፣ ትሕትናን፣ ጽናትን እና ትዕግሥትን እንማራለን፡፡ ስለዚህ ልጆች እናንተም ከእነዚህ ሴቶች ሕይወት ያገኛችሁትን ቁም ነገር በመያዝ በመንፈሳዊ ሕይወታችሁ እነርሱን በእምነትና በምግባር ምሰሏቸው፡፡

## ተግባር፡-

- ልጆች ከዚህ ትምህርት ምን እንደተረዳችሁ ለመምህራችሁ ንገሩ፡፡
- ከእነዚህ ሴቶች ሕይወት ምን የተለየ ነገር እንዳገኛችሁ ከጓደኞቻችሁ ጋር ተወያዩበት፡፡

www.zeorthodox.org

# ዋቢ መጻሕፍት


- ሃብተማርያም ወርቅነህ (ሊቀ ሥልጣናት)፣ ጥንታዊ የኢትዮጵያ ሥርዓተ ትምህርት፣ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ቀ.ኃ.ሥ ማተሚያ ቤት፣ 1963 ዓ.ም
- ሃይማኖተ አበው፣ አዲስ አበባ፣ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፣ 1986 ዓ.ም
- አባ መልከ ጼደቅ (ሊቀ ጳጳስ)፣ ትምህርተ ክርስትና፣ አዲስ አበባ፣ ትንሣኤ ዘጉባዔ ማተሚያ ቤት፣ 1984 ዓ.ም፡፡
- አባ ጎርጎርዮስ (ሊቀ ጳጳስ)፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ታሪክ፣ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1974 ዓ.ም፡፡
- ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳትና ሊቃውንት ቤተክርስቲያን (አዘጋጆች)፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን እምነት፣ ሥርዓት አምልኮና የውጭ ግኙኙነት፣ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት፣ 1988 ዓ.ም.
- ሊቃውንት ቤተክርስቲያን (አዘጋጆች)፣ የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ትናንትና ዛሬ፣ አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ቤት፣ 1990 ዓ.ም.
- ሉሌ መልአኩ (መምህር)፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ታሪክ፣ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1997 ዓ.ም፡፡
- መሐሪ ትርፌ (ሊቀ ሊቃውንት)፣ መጽሐፈ ሐዲሳት ሠለስቱ ንባቡና ትርጓሜው፣ አዲስ አበባ፣ አርትስቲክ ማተሚያ ቤት፣ 1989 ዓ.ም፡፡
- መጽሐፈ ስንክሳር፣ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1983 ዓ.ም
- መጽሐፈ ቅዳሴ ንባቡና ትርጓሜው፣ አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት፣ 1988 ዓ.ም፡፡
- መጽሐፈ ስንክሳር፣ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1983 ዓ.ም
- መጽሐፈ ቅዳሴ ንባቡና ትርጓሜው፣ አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት፣ 1988 ዓ.ም
- ወንጌል ቅዱስ ንባቡና ትርጓሜው፣ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1988 ዓ.ም
- ዳኛቸው ካሳሁን (መልአከ ሰላም)፣ ክርስቲያናዊ ሥነ-ምግባር፣ አዲስ አበባ፣ ማኅበረ ቅዱሳን፣ 2003 ዓ.ም
- ደረጀ ጅማ (መጋቤ አእላፍ)፣ ምን ያስጨንቃችኋል ክፍል ፪፣ አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት፣ 2002 ዓ.ም፡፡
- መጽሐፍ ቅዱስ፣ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1980 ዓ.ም
- ሐረገ ወይን ቸርነት፣ ሴትና አህያ፣ አዲስ አበባ፣ 2005 ዓ.ም፡፡
- ምክረ ሥላሴ ገብረ አማኑኤል (ዶ/ር)፣ ጠቅላላ የቤተክርስቲያን ታሪክ፣ አዲስ አበባ፣ 2000 ዓ.ም
- ኀሩይ ኤርምያስ (መምህር)፣ መዝገበ ታሪክ፣ አዲስ አበባ፣ 2002 ዓ.ም


www.zeorthodox.org

- የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት፣ አዲስ አበባ፣ የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር፣ 1996 ዓ.ም፡፡
- ቸርነት አበበ (መምህሩ)፣ የመጽሐፍ ቅድስ ጥናት፣ አዲስ አበባ፣ 2003 ዓ.ም
- H.G. Bishop Moussa@ The Characteristics of Orthodox Teaching@ Bishopric of Youth@ Harmony Press, 2007.
- H.G. Bishop Mouusa, An Introduction to the New Testament, Bishopric of youth, Dar EL Geel Press, 2001.
- H.G. Bishop Raphail, The Meaning of Miracles, Bishopirc of Youth, 2010.
- Sunday School Curriculum, Grade 1 to Grade 12. The Coptic Orthodox Diocese of The Southern USA.
- Sunday School Lessons, Class 1 to Class 10, E.O.T.C Latin America Diocese.
- በጠቅላይ ቤተ ክህነት፡፡ 2000 ዓ.ም፡፡ የኢትዮ. ኦርቶ.ተዋ. ቤ.ክ ታሪክ ከልደተ ክርስቶስ እስከ ፳፻ ዓ.ም፡፡ አዲስ አበባ ፣ ሜጋ ማተሚያ ቤት
- ምክረ ሥላሴ ገብረ አማኑኤል (ቀሲስ ፤ ዶ/ር )፡፡ 2000፡፡ በኢትዮጵያ የመጀመሪያው የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም በግዕዝ ቋንቋ ፡፡ አዲስ አበባ፡፡ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ
- የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር፡፡ 1996 ዓ.ም፡፡ የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት፡፡ አዲስ አበባ፡፡ ንግድ ማተሚያ ቤት፡፡
- ጎርጎርዮስ(ብፁዕ አቡነ)፡፡ 1996 ዓ.ም፡፡ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ በዓለም መድረክ፡፡ አዲስ አበባ፡፡ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፡፡
- መሐሪ ትርፌ (በሊቀ ሊቃውንት)፡፡ 19 ዓ.ም፡፡ የጳውሎስ መጽሐፍ ንባቡና ትርጓሜው፡፡ አዲስ አበባ፡፡
- ዳንኤል ተሾመ፡፡ 19 ዓ.ም፡፡ ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ሊታወቁ የሚገባቸው መሠረታዊ ጉዳዮችና የትርጉም ስልቶች፡፡ አ.አ
- Pulpet ; 19 A.D; Bible commentary The Epistle of paul to the ROMAN;
-
- Tadros Yakob Malaty (Father); 2007-2008 A.D; The Epistle of Saint Paul to the Romans; Alexandria,Egypt.
- መብራቱ ኪሮስ (ዲያቆን)፡፡ አጠቃላይ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ፡፡ የቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ ያልታተመ መማሪያ፡፡


www.zeorthodox.org

- ጎርጎርዮስ (በብፁዕ አቡነ):: 1981 ዓ.ም:: የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ:: አዲስ አበባ::
- ምክረ ሥላሴ ገብረ አማኑኤል (ቀሲስ ፤ ዶ/ር ):: 2001:: የእግዚአብሔር መንግሥት ታሪክ 1ኛ እና 2ኛ:: አዲስ አበባ::
- Lule Melaku (Asst. Professor); 2010; History of the Ethi. Orthodox Tewahido Church; A.A ; Elleni p.p.plc.
- ሰሎሞን መላኩ(ዲያቆን):: 2001ዓ.ም:: የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ወርቃማ ዘመናት:: አዲስ አበባ:: ባናዊ ማተሚያ::
- Syrian Sunday school curriculum.
- Introduction to Coptic orthodox Church ; Father Tadros Y Malaty
- Ian Gillman,Hans-Joachim Klimkeit ; Christian in asia before 1500 ;
- ዜና ሐዋርያት
- ገድለ ቅድስት አርሴማ
- ሺኖዳ(ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ) ቅንዓት
- የኢትዮፕያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤ.ክ ፤ ስንክሳር ፤ በትንሳኤ ዘጉባዔ ማተሚያ
- ያረጋል አበጋዝ (ዲ/ን):: ቅዱስ ዩሐንስ አፈወርቅ ሕይወቱና ትምህርቱ ፤ አዲስ አበባ
- በጌታቸው ኃይሌ(ፕሮፌሰር):: 1997 ዓ.ም:: የአባ ባሕርይ ድርሰቶች
- ዳንኤል ክብረት(ዲ/ን):: 1998ዓ.ም:: የቤተ ክርስቲያን መረጃዎች:: አዲስ አበባ:: ሜጋ ማተሚያ ቤት::
- ………:: አዋልድ መጻሕፍት:: ሐመረ ተዋሕዶ::
- Douglas J.D and Tenney M.c (1987) New International BIBLE DICTIONARY. ZONDERVAN'S.Grand Rapids,MICHIGAN USA
- Holy Trinity College.(2004) Patrology፡ Holy Trinity College module/ unpublished./
- Malaty T.Y( Father)Patrology ;


www.zeorthodox.org

- Malaty T.Y( Father).(199). Tradition and Orthodoxy. Alexandria .Egypt.
- ማኅበረ ቅዱሳን፡፡ 2004 ዓ.ም፡፡ ቤተ ክርስቲያንህን እወቅ፡፡ አዲስ አበባ፡፡ የማዕረግ ቃል ማተሚያ ቤት፡፡
- ነገረ ማርያም
- Shenoda - Pope (1999). The Holy virgin Saint Mary. Cairo,Egypt.
- ትንሣኤ ማሳተሚያ ድርጅት፡፡ (1988) ወንጌል ቅዱስ ትርጓሜ፡፡ አዲስ አበባ፡፡ ብሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት
- የግብጽ ቤተ ክርስቲያን ሰንበት ትምህርት ቤት መማሪያ ፤ ካናዳ
- ሺኖዳ ሰው ምንድነው ፤ በብጹዕ ወቅዱስ ፤
- ክርስቲያን አንትሮፖሎጂ
- ሺኖዳ (ብጹዕ ወቅዱስ ፤ አቡነ)፡፡ መንፈሳዊው ሰው
- John Mark (Father). 19 . Ascending the heights ; A lay man guide to the ladder of divine ascent
- አበራ (በሊቀ ጉባዔ ፤ አባ)፡፡ 1996 ዓ.ም፡፡ ትምህርተ ሃይማኖትና ክርስቲያናዊ ሕይወት፡፡ አዲስ አበባ፡፡ ማኅበረ ቅዱሳን፡፡
- ሰሎሞን ሙሉጌታ (ቀሲስ)፡፡ 200 ዓ.ም፡፡ መሽኮርመምና ማሽኮርመም፡፡ በቦሌ ደብረ ሳሌም የረቡዕ ጉባዔ የተሠጠ ስብከት በzeorthodox.org የተለቀቀ ጽሑፍ፡፡ አዲስ አበባ
- ሰሎሞን ሙሉጌታ (ቀሲስ)፡፡ 2000 ዓ.ም፡፡ ቅድመ ጋብቻ፡፡ በቦሌ ደብረ ሳሌም የረቡዕ ጉባዔ የተሠጠ ስብከት በzeorthodox.org የተለቀቀ ጽሑፍ፡፡ አዲስ አበባ
- ተስፉ ገብረ ሥላሴ፡፡ 1988፡፡ መጽሕፍተ መነኮሳት፡፡ አዲስ አበባ
- ኪዳነ ወልድ ክፍሌ፡፡ መጽሐፈ ሰዋስው ወግስ ወመዝገበ ቃላት፡፡
- ጥዑመ ልሳን፡፡() ያሬድና ዜማው፡፡ አዲስ አበባ፡፡
- ሙሳ (ሊቀ ጳጳስ)፡፡ ወጣትነትና የቅድስና ኑሮ፡፡ በመምህር ወንድወሰን ሶርሳ የተተረጎመ፡፡


www.zeorthodox.org